

# በቢቱዋሕ ሌኡሚ ውስጥ ያሉህ መብቶች 2016

ሀቢቱዋሕ ሀሌኡሚ

በሕይወትህ ወሳኝ ወቅቶች ከጐንህ ነው

*6050•www.btl.gov.il



# ሀቢ.ቱዋሕ ሀሌኡሚ ላንተ አገልግሎት

## ውድ ዜጎች፣

የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ የሥራ ድርሻ ለእያንዳንዱ ዜጋ በተለያየ የሕይወት ዑደቱ ጊዜ የዋስትና መረብ መስጠት ነው። የ"ረቫሐ"ና የማኅበራዊ አገልግሎቶች ሚኒስትር እንደመሆኔ መጠን የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ኀላፊም ነኝ። በመሆኑም የምታገኟቸውን አገልግሎቶች የሚያስጠብቁ እንደዚሁም መብቶቻችሁን ተግባራዊ እንድታደርጉ የሚረዱ ሕጎችና ማሻሻያዎች አወጣለሁ።
ሥራዬን እንደጀመርኩ ለእስራኤል ዜጎች የሚሰጡት አገልግሎቶች እንደተሻሻሉ ላበስራችሁ እወዳለሁ። በሰሜን እስራኤል የሚገኙ የሕክምና ይግባኝ ኮሚቴዎች ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ውጪ እንዲሆኑ አድርገናል። ይህም በተገልጋዮች የአካል ስንኩልነት መጠን ላይ የሚደረገው ውይይት በሌላ ነገር ላይ ጥገኝነት የሌለው እንዲሆን ያስችላል። ቤርሼቫና ሐይፋ ለሚገኙት የሕክምና ኮሚቴዎች ምክርና አመራር በነጻ የሚሰጡ "ያድ መከቬኔት" የተሰኙ ቅርንጫፎችን አቋቁመናል። በ2016 ዓ.ም. ቅርንጫፎቹን በቴል አቪቭና ኢየሩሳሌም አካባቢ ለማስፋፋት ዕቅድ አለን። የዕዳና ቅጣቶች መጠራቀምን ለመከላከል የቆዩ ዕዳዎችን ለመሠረዝ የሚያስችልና አዳዲስ ዕዳዎች እንዳይፈጠሩ የሚያደርግ አሠራር ዘርግተናል። ይህንም ለማድረግ አሠሪዎች ሪፖርታቸውን በኢንቴርኔት አማካይነት እንዲያስተላልፉ የሚያደርግ አስገዳጅ ሕግ ያወጣን ሲሆን ይህም ከሥራ በሚገኝ ደመወዝና በቅድመ-ጡረታ ገንዘብ ላይ ተአማኒነት ያለው መረጃ በፎርምበት እንዲተላለፍ ያደርጋል።
ለሕዝቡ መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑና ቢሮክራሲያዊ ሂደቶች አጠር ያሉ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ የኢንቴርኔት ድረ ገጻችንን አሻሽለናል። በመሆኑም ካሁን ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰነዶችን በኢንቴርኔት አማካይነት ማቅረብ የሚቻል ሲሆን ይህም ወደ ቢሮአችን መምጣትንና በሰልፍ ተራ ይዞ መቆምን ያስቀራል። ይህም ማንኛቸውንም ዓይነት ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ሆኖ ከሚገኘው የስልክ አገልግሎታችን በተጨማሪ ነው።
ሽማግሌዎና ባልቴቶች በጐ አገልግሎት እንዲያገኙ ካለን ታላቅ ግዴታ የተነሣ ለሽማግሌዎችና ባል ለሞተባቸው ሴቶች የገቢ ማሟያ ጭማሪ አድርገናል። እንደዚሁም በሶሮካና ሺባ ሆስፒታሎች በሕክምና ኮሚቴዎች ውስጥ ጉዳዮችን በቶሎ የሚያይ ሂደት ፈጥረናል። ይህም ለምሳሌ ከበድ ያለ የጤና ችግር ያለበት ባለዋስትና የአካለ ስንኩልነት መጠን እንዲወሰንለት የግድ ወደኮሚቴው መምጣት ሳያስፈልገው እሱ በሌለበት ይወሰንለታል ማለት ነው። እንደዚሁም ዕድሜያቸው የገፋ ሰዎች የማገገሚያ መደጐሚያ የሚቀበሉበትን ጊዜ ቀደም እንዲል አድርገናል። ይህም ባለመብትነት በተወሰነ በሳምንቱ ውስጥ ገንዘቡ እንዲተላለፍ ለማድረግ ነው። በሰሞኑ ቀናት የማገገሚያ መደጐሚያ ለመቀበል የሚያስችለው ፈተና ቀለል ያለ ይሆን ዘንድ እንደዚሁም ለድጐማው ባለመብት የሚሆኑ ሰዎች ቁጥር እንዲጨምር እየሠራን ነው።
ለሕዝቡ ለምንሰጠው አገልግሎት ጥራት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ሲሆን ዓላማዬ ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚን ችግሮችን የሚሰማ፣ ለሕዝቡ አቤቱታዎች ተደራሽ እንዲሁም ስኬቱ የሚለካ አካል እንዲሆን ማድረግ ነው። ቢሮክራሲያዊ ሂደቶችን እንደዚሁም አስተያየቶችን ለመቀበል የመጠባበቂያ ጊዜን ማሳጠራችንን የምቀጥል ሲሆን ዋናው ዓላማዬ ባለመብትነት የሚገባው ግለሰብ መብቶቹን በተቻለ ፍጥነት እንዲያገኝ ማድረግ ነው።

ከቡራኬ ጋር፣

**የክኔሴት አባል ሐይም ካትስ**

የ"ረቫሐ"ና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሚኒስትር

## ውድ ዜጎች፣

የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ተቋም የሀገሪቱን ዜጎች ማኅበራዊ ዋስትና ሙያዊ በሆነ መንገድ በመምራት ላይ የሚገኝ አካል ነው። ዋና ተግባሩ በሕጉ መሠረት ለሚመለከታቸው ሰዎች ልዩ ተቆራጮችን ("ኪጽባኦት") መስጠት ነው። ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ለሰፊው የማኅበረሰብ ክፍሎች የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ መከላከያ መረብ ይዘረጋል። ይህም ልጆች ላላቸው ቤተሰቦች፣ ለሽማግሌዎች፣ ባል ለሞተባቸውና ወላጅ ለሌላቸው ልጆች፣ እንደዚሁም ዋስትና ላላቸው በግል ችግር ጊዜ እንደ ሞት፣ አካለ ስንኩልነት እና በሥራ ላይ መጎዳትን ለመሳሰሉት ነው። ለሰፊው ሕዝብ በተቆራጭ አማካይነት የሚከፈለው በዓመት 75 ሚሊያርድ ሼቄል ነው። እንደዚሁም የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት በማገገሚያ ክፍልና በአምስቱ "ክራኖት" አማካይነት ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰቡ ክፍሎች ሙያዊ የማገገሚያ ፕሮግራሞችንና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያንቀሳቅሳል።
ማኅበራዊ ሕግ እንዲደነገገግ መጣር እና ዋስትና ላላቸው ዜጎችና ለደካማው የኅብረተሰቡ ክፍሎች መጨነቅ የጥረታችን አንዱ ትኩረት ነው። ይህንንም የምናከናውነው ከሰፊው ሕዝብ ጋር የማያቋርጥ መስተጋብር በመፍጠር ሲሆን የርስ በርስ ዋስትና የሚለውንም ዕሴት ተግባራዊ ለማድረግ እንጥራለን። ይህም "ሁሉም እያንዳንዱ ባልንጀራውን ይረዳው ነበር፣ ወንድሙንም፡ - አይዞህ ይለው ነበር" በሚለው ጥቅስ መሠረት ነው (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 41፣ ቁጥር 6)።
የኛ ማዕከላዊ ዓላማዎች ዜጐች በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ያሏቸውን መብቶች እንዲጠቀሙ ማድረግና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ነው። ይህንንም የምናደርገው ወደ እኛ የሚያመለክቱ ሰዎችን ስሜት በመጠበቅ ነው። በየቅርንጫፎች የሚሰጠው አገልግሎት እንዲሻሻል ዘወትር የምንሠራ ሲሆን በዳር አገር ተጨማሪ የአገልግሎት ማዕከሎችን እየከፈትን ነው። በተጨማሪም አገልግሎትንና ሰፊውን ሕዝብ ለማቀራረብ ባለን ፍላጐት ወደ ወደ ቅርንጫፎች የመሄድን ሁኔታ የሚቀንሱ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ያለማቋረጥ እንሠራለን።
ለባለዋስትናዎች አገልግሎት የሚውል አገር አቀፍ የስልክ ማዕከል አቋቁመናል፣ እንደዚሁም ለግል አገልግሎት የሚውሉ "ኮምፒይተራይዝድ" ቦታዎች ("ዔምዶት") እያንቀሳቀስን ነው። በኢንተርኔት አማካይነት በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ የሚሰጠውን አገልግሎት አስፋፍተናል፦ ማለትም ከቤታችሁ ሆናችሁ አገልግሎት እንድታገኙ የሚያስችላችሁን ለምሳሌ የክፍያ ድረ ገጽ እና ለግል አገልግሎት የሚውል ድረ ገጽ የመሳሰሉትን።
በዚህ መጽሔት ውስጥ የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ልዩ ክፍያዎችን የምታገኙበትን መስፈርት፣ ለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ እና ለጤና አገልግሎት ስለምትከፍሉት ግዴታዊ ክፍያ፣ እንዲሁም በቅርንጫፎችና በሌሎች የአገልግሎት ዘርፎች ስለሚሰጠው አገልግሎት ጠቅለል ያሉ ማብራሪያዎችን ልታገኙ ትችላላችሁ። ይሄ መረጃ በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ያላችሁን መብት እንድታስከብሩ፣ እንዲሁም ውጤታማ እና ፈጣን አገልግሎት እንድታገኙ እንደሚረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

ከቡራኬ ጋር

**ፕሮፌሴር ሽሎሞ ሞር ዮሴፍ**

አጠቃላይ ሥራ አስኪያጅ

# ማውጫ


- የእናትነት ዋስትና – የወሊድ ስጦታ/ክፍያ (“ማዓናክ ለይዳ”)፣ የወሊድ ክፍያ (“ድሜ ለይዳ”)፣ የእርግዝና መንከባከቢያ ክፍያ ........ 4
- የልጆች ዋስትና ........ 6
- በተጠባባቂ ውትድርና (“ሚሉኢም”) ለሚያገለግሉ ሰዎች የሚደረጉ ድጎማዎች ("ታግሙሊም") ........ 7
- በተመረጠ (“ሙአዴፊት”) ሥራ ለሚሠራ ከአገልግሎት ለተሰናበተ ወታደር የሚሰጥ ክፍያ ........ 8
- የሥራ አጥነት (“አቭታላ”) ዋስትና ........ 9
- በኪሳራ እና በድርጅት መፍረስ ምክንያት ሠራተኞች ያላቸው መብት ........ 10
- የበጎ አድራጊዎች (“ሚትናድቪም”) መብቶች ........ 10
- በጠላት እኩይ ተግባራት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ ........ 11
- የሥራ ላይ ጉዳት ዋስትና ........ 12
- የአካል ጉዳተኛ ዋስትና – ሙሉ ጉዳት፣ ልዩ አገልግሎቶች፣ አካሉ የጎደለ ልጅ ........ 14
- የመንቀሳቀሻ ክፍያ (“ጊምላት ናያዱት”) ........ 16
- በአደጋ የተጎዱ ሰዎች ዋስትና ........ 18
- በቤተሰብ ውስጥ በሚከሰት የኃይል መጠቀም ወላጁን ላጣ ልጅ የሚከፈል ካሳ ........ 18
- በባለሞያ የተደገፈ ማገገም ........ 19
- የገቢ ዋስትና (“ሃፍታሃት ሃክናሳ”) ክፍያ ........ 20
- የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ ክፍያ (“ድሜይ ሜዞኖት”) ........ 22
- ለጽዮን እስረኞች እና ለሰማዕታት የሚሰጥ ካሳ ........ 23
- ይሁዳውያንን ከሞት ላተረፉ የዓለም ጻድቃን (“ሐሲዴይ ዖላም”) የሚሰጥ ካሳ ........ 23
- ለ“ሻኢሪም” የሚሰጥ ዋስትና ........ 24
- የእርጅና ዋስትና ........ 26
- የአቅመ ደካማ (“ሲዑድ”) ዋስትና ........ 28
- ለሽማግሌዎችና/ባልቴቶች የሚሰጥ የምክር አገልግሎት ........ 29
- በቢቱዋሕ ሌኡሚ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ........ 30
- የቢቱዋሕ ሌኡሚ “ክራኖት” ........ 31
- ለቢቱዋሕ ሌኡሚ እና ለጤና ዋስትና የሚከፈል ክፍያ ........ 32
- በቢቱዋሕ ሌኡሚ ያሉ የአገልግሎት መሥመሮች ........ 36
- በማኅበራዊ ዋስትና መስክ ያሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ........ 38
- የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፎች ........ 40


በመጽሔቱ ውስጥ አጠቃላይ ማብራሪያዎች ይቀርባሉ፣ ነገር ግን እንደሙሉ ትርጉም እና እንደሕግ ማረጋገጫ ሊታዩ አይገባም።
በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተባእታይ ጾታ የተጻፈው ሁሉ ለአንስታይ ጾታም ያገለግላል።

# የቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቋም

የቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቋም የሰዎችን ማኅበራዊ ዋስትና ለማስጠበቅ በሕጉ መሥረት የሚሠራ መንግሥታዊ ተቋም ነው።

ዋናው ሥራውም ሠርተው መተዳደር ለማይችሉት የእስራኤል ዜጎች ለመኖር የሚያስችላቸውን ዋስትና ማስገኘት ነው።

ቢቱዋሕ ሌኡሚ ከእያንዳንዱ ኗሪ እንደ ገቢው መጠንና እንደ ደረጃው፣ የዋስትና ክፍያ የሚሰበስብ ሲሆን ለባለመብቶች ተቆራጮችን እና ድጐማ በሕጉ መሠረት ይከፍላል። ቢቱዋሕ ሌኡሚ በሕጉ መሠረት የጤና ዋስትናን ከባለዋስትናው በማውረድ ለ“ኩፖት ሆሊሞች” የማስተላለፍ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

የቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቋም ተቆራጭና ድጐማ የሚከፍለው ለሥራ አጦች፣ በወሊድ ፈቃድ ላይ ለሚገኙ ሴቶች፣ ለአካለ ስንኩላን፣ መንቀሳቀስ ለማይችሉ፣ በሥራ ቦታ አደጋ ለደረሰባቸው፣ በተጠባባቂ ውትድርና ለሚያገለግሉ፣ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች፣ ለሽማግሌዎች፣ ባል ለሞተባቸውና ወላጅ ለሞተባቸው ልጆች፣ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆነ፣ ኪሳራ የደረሰባቸው አሠሪዎች ለሚያሠሯቸው ሠራተኞች፣ በበጎ ፈቃድ ለሚሠሩና ለመሳሰሉት ይከፍላል።

የተቆራጭ ክፍያ ዓላማው ኗሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ከጊዜያዊ ወይም ቀጣይነት ካለው የኤኮኖሚ ችግር ለመጠበቅ ሲባል ነው።

የዋስትና ክፍያውን ከአንድ ወገን ሰብስቦ ወደሌላው ማስተላለፍ ማለት ጠንካራ የኢኮኖሚ ዓቅም ካላቸው የሚገኘው ገንዘብ ወደ ደካማው የኅብረተሰብ ክፍል ይተላለፋል ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ቢቱዋሕ ሌኡሚ በእስራኤል ሀገር ውስጥ ገቢ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲከፋፈልና የድኅነት መጠን እንዲቀንስ አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለት ነው።

በገንዘብ ከሚሰጠው ተቆራጭ በተጨማሪ፣ ቢቱዋሕ ሌኡሚ፣ የማገገሚያና የሙያ ትምህርት ለአካለ ስንኩላና ባል ለሞተባቸው የሚሰጥ ሲሆን የእንክብካቤና የምክር አገልግሎት ለሽማግሌዎች ይሰጣል።

ቢቱዋሕ ሌኡሚ"፣ በሚያንቀሳቅሳቸው አምስት “ክራኖት” አማካኝነት ኅብረተሰቡን ለማገልገል ቃል ለገቡ ፕሮጀክቶችና ልዩ ችግር ያለባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚንከባከቡ ተቋሞች ጋር በጋራ ይሠራል።

ፕሮጀክቶቹ እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሕዝቡ ጋር እንዲቀላቀሉና ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚረዱ ናቸው። “ክራኖት” የሚሰጡት ገንዘብ አካለ ስንኩላንን፣ ሥራ መሥራት የማይችሉትን፣ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ሽማግሌዎችን፣ የተገለሉ ወጣቶችን፣ አደጋ ላይ ያሉ ወጣቶችንና የመሳሰሉትን ለመርዳት በሚያገለግሉ ፕሮጀክቶች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል።

ለባለዋስትናዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል ቢቱዋሕ ሌኡሚ በኮምፒዩተር የሚታገዝ አሠራር አስፋፍቷል። ይህም አሠራር በቀላሉ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ይረዳል። ለምሳሌ በኢንተርኔት ድረ ገጽ አማካይነት አጠቃላይና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን፣ ግላዊ መረጃና አገልግሎት ማግኘት ስንችል ራሳችን ልንጠቀም የምንችልበት ቦታዎች (ዔምዶት")፣ አሉ። እንደዚሁም የቴሌፎን ማዕከል፣ ቀጥታ በመደወል የምታገኞቸው የተለያዩ አገልግሎቶች፣ ለእጅ ስልክ የሚያገለግሉ "አፕሊኬሽኖች"፣ እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ። እነዚህ እርምጃዎች አገልግሎቶችን ራሳችን እንድንቀበልና ክፍያዎችን እንድንፈጽም የሚያስችሉ ሲሆን ባለዋስትናው ቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ድረስ በመምጣት እንዳይቸገር ይረዱታል።


**ውድ ዜጋ፣** በፊትህ የሚገኘው መጽሔት አጠቃላይ የሆነ፣ ስለ ተቆራጭ እና በቢቱዋሕ ሌኡሚ ስለሚገኙ አገልግሎቶች መረጃ፣ እያንዳንዳችን በሕይወታችን ስለሚነኩንና በሕይወታችን አንዱ ነጥብ ላይ ሊያጋጥመን ስለሚችል ነገር መረጃ የያዘ ነው።

ይህ ጠቃሚ መረጃ በ“ቢቱዋኽ ሌኡሚ” ያለውን መብትህ እንድትጠቀም ይረዳሃል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

**ቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቆራጭ የሚከፍልባቸው ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያየሩ ይችላሉ። በመሆኑም መብትህን ተግባራዊ ለማድረግ በምትመጣበት ጊዜ መብቶችህን ከአንዱ በሚከተለው መንገድ ማጣራት ትችላለህ። ለሞኬድ ስልክ ቁጥር *6050 በመደወል ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በመሄድ፣ አጠቃላይና የተሻሻለ መረጃዎች ወደያዘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ www.btl.gov.il በመግባት በማንበብ። እንደዚሁም በመኖሪያ አካባቢህ ወደሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ በመሔድም ዝርዝር መረጃዎችን መቀበል ትችላለህ።**

# የእናትነት ዋስትና

የእናትነት "ቢቱዋኽ" የታለመው ለወላዷ እና ለሚወለደው ሕጻን መሠረታዊ የሆኑ ጥቅሞችን ለማስከበር እና ወላዷ በእርግዝና እና በመውለዷ ምክንያት ለሚመጣው የገቢ መቋረጥ ካሳ መስጠት ነው።



## የሆስፒታል መተኛ ክፍያ

ቢቱዋሕ ሌኡሚ ለወላዷ ማስተኛ ለሆስፒታሉ የሚከፍለው ወጪዎች ለሆስፒታል የሚከፈል ገንዘብ ባለመብት የሚሆኑት ውጭ አገር ሄደው ማኅጸን በመከራየት ልጅ የተወለደላቸው ወላጆች ጭምር ናቸው።

## የወሊድ ስጦታ/ክፍያ

በወሊድ ምክንያት ለምትከፍላቸው የመጀመሪያዎቹ ወጪዎች ላይ ለመሳተፍ ሲባል ለወላዷ የሚከፈላት ገንዘብ ነው። ክፍያው በአንድ ወር ውስጥ የልጆች ክፍያ ለሚከፈልበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር የሚተላለፍ ሲሆን የመጀመሪያዋ ወሊድ ከሆነ ግን በወለደችበት ሆስፒታል ለሰጠችው የሒሳብ ቁጥር ይከፈላታል።

### ለሆስፒታል መተኛ ክፍያ እና ለወሊድ ስጦታ/ክፍያ (እንደዚሁም ለልጆች ክፍያ) ማመልከት

ወሊድ በተካሄደበት ሆስፒታል አማካኝነት ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ይቀርባል። ለዚህም ሲባል ወላዷ የራሷን እና የባለቤቷን መታወቂያ ማምጣት እንዲሁም የራሷን የባንክ ሒሳብ ቁጥር (ወይም የእሷን እና የባለቤቷን የጋራ የሒሳብ ቁጥር) ለሆስፒታሉ ማቅረብ አለባት።

### በጥር 2016 የነበረው የወሊድ ስጦታ/ክፍያ መጠን፡

**ለቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ 1,751 ሼቄል**
**ለቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ 788 ሼቄል**
**ለሦስተኛ ልጅ ወይም ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ልጅ 525 ሼቄል**
**ለመንትዮች 8,757 ሼቄል**
**በአንዴ ለተወለዱ ሦስት ሕጻናት 13,136 ሼቄል**

## የወሊድ ክፍያ

የወሊድ ክፍያ የሚከፈለው ለወሊድ እረፍት ለወጣች የምትሠራ ሴት ሲሆን በዕረፍቷ ወቅት በወላዷ የሒሳብ ቁጥር አንድ ጊዜ ይከፈላል። ይህ ክፍያ የሚከፈለው ወላዷ በእርግዝና እና በመውለዷ ምክንያት ገቢዋን በማጣቷ ለመካስ ሲባል ነው።

### ለወሊድ ክፍያ መብት ያለው ማን ነው?

- እስራኤል ሀገር ውስጥ የምትሠራ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ (የእስራኤል ሀገር ኗሪ ባትሆንም)።
- ከእስራኤል ሀገር ውጭ የምትሠራ ተቀጣሪ ሠራተኛ – በልዩ ሁኔታዎች።
- 18 እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላት በሞያ ሥልጠና ትምህርት ወይም በሞያ ማሻሻያ ትምህርት ላይ ያለች ሴት – በልዩ ሁኔታዎች።

### የወሊድ ክፍያ መሥፈርቶች

- ለወላዷ "ከሚወሰነው ቀን" ቀድሞ (ሥራዋን አቁማ በወሊድ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ) ከ14 ወራት ውስጥ የ10 ወራት ወይም ከ22 ወራት ውስጥ የ15 ወራት የ"ቢቱህ ሌኡሚ" ክፍያ ለወላዷ ተከፍሎላት ከሆነ – የ14 ሳምንታት የወሊድ ክፍያ መብት አላት።
- ለወላዷ "ከሚወሰነው ቀን" ቀድሞ (ሥራዋን አቁማ በወሊድ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ) ከ14 ወራት ውስጥ የ6 ወራት የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ ለወላዷ ተከፍሎላት ከሆነ – የ7 ሳምንታት የወሊድ ክፍያ መብት አላት።

### እነዚህ ወራት "ከሚወሰነው ቀን" ቀድመው ያሉ ከሆኑ የዋስትና ክፍያዎች እንደተከፈለባቸው ወራት ይቆጠራሉ፡

- ሴትየዋ ሠርታ ከአሠሪዋ ደሞዝ የተቀበለችባቸው ወራት (የሕመም ክፍያን እና የዕረፍት ክፍያን ጨምሮ) ወይም የግል ሥራ ኗሯት ከገቢዋ ላይ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ የከፈለችባቸው ወራት።
- ሴትየዋ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ "ድሜይ ለይዳ" (ለቀደመው ወሊድ) ወይም የሥራ ላይ ጉዳት ክፍያ ወይም የሥራ አጥ ክፍያ ወይም የአደጋ ክፍያ ወይም የእርግዝና መንከባከብ ክፍያ ወይም የሥራ የ100% የአካል መጉደል ክፍያ የተከፈለባቸው ወራት።
- ሴትየዋ የሕመም ክፍያ ወይም ከ"ኩፖት ጊሜል" የዓመት ፈቃድ የወሰደችባቸው ወራት።
- የያለክፍያ ዕረፍት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት (ለእነዚህ ወራት አሠሪዋ የቢቱዋሕ ሌኡሚን ክፍያ ሊከፍል ይገባዋል)።
- ሴትየዋ በሞያ ማሰልጠኛ የተማረችባቸው ወራት እና "ከወሳኙ ቀን" በፊት ቢያንስ ለ30 ተከታታይ ቀናት ከሠራች።
- የውትድርና አገልግሎት ወራት – የውትድርና አገልግሎቷን አቋርጣ መሥራት ለጀመረች – በተወሰኑ መስፈርቶች።

> ከወሩ ቀናት በከፊሎቹ ከተሠራ ሙሉውን ወር እንደተሠራ ይቆጠራል።

### የወሊድ ክፍያ መጠን

**"ቢቱዋሕ" የሚከፈልበት 100% ደሞዝ ሆኖ "ማስ ሃክናሳ"፣ የቢቱዋሕ ሌኡሚና የጤና ክፍያ ከተቀነሱ በኋላ እስከ ከፍተኛ የወሊድ ክፍያ**
**በጥር 2014 ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ በቀን 1,459.50 ሼቄል ነው።**

> ለወሊድ ክፍያ ባለመብት መሆናችሁን ለማጣራትና እንደዚሁም የወሊድ ክፍያውን መጠን ለማወቅ "ቢቱዋሕ ሌኡሚ" ድረ ገጽ ላይ የሚገኘውን **የወሊድ ክፍያ ስሌት መኪናን** ተጠቀሙ።

### የወሊድ ዕረፍትን ማራዘም

አንዲት ወላድ በአንድ ጊዜ ከአንድ ሕጻን በላይ በመውለዷ ምክንያት ወይም ሆስፒታል እሷ ወይም የተወለደው ሕጻን በሆስፒታል ውስጥ ቢያንስ ለ15 ቀን በመተኛታቸው ምክንያት የወሊድ ዕረፍቷን የማራዘም ወይም የመከፋፈል መብት አላት። ስለ ዕረፍቱ መራዘም ወይም ስለመከፋፈሉ በተቻለ ቅድሚያ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ማሳወቅ የወላዷ ፋንታ ነው። ተጨማሪ መረጃ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

### የወሊድ ክፍያን እንዴት መቀበል ይቻላል?

የወሊድ ክፍያ መጠየቂያ ፎርም የሆነውን 355/7ב መሙላት እና በመኖሪያ አካባቢ ለሚገኝ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ መስጠት።

ፎርሙን ከማንኛውም የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ። ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነች ፎርሙን ከአሠሪዋ መውሰድ ትችላለች።

> **አዲስ!** ማመልከቻውን ወደ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ገብቶ በመሙላት ሁሉንም ማስረጃዎች አያይዞ ወደ ቅርንጫፉ "ኦንላይን " ላይ ሆኖ መላክ ይቻላል።

> የግል ሠራተኛ ወይም ተቀጥራ የምትሠራ ሠራተኛ አሠሪው የወሊድ ክፍያን "አውቶማቲክ" በሆነ መንገድ ለመክፈል ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ጋር ስምምነት ካለው፣ ለወሊድ ክፍያ ማመልከቻ ማስገባት የለባቸውም።
>
> ከመውለዷ አንድ ወር አስቀድሞ "ድሜ አሽታላ" የተቀበለች ወላድ እና እንደዚሁም ከመውለዷ ከአንድ ሳምንት በፊት እርግዝናውን ለመጠበቅ ለማለት መደጐሚያ ("ጊምላ") የተቀበለች ወላድ ከሆነች ሁለቱም ዓይነት ወላዶች የወሊድ ክፍያን ወዲያውኑ ስለሚቀበሉ ማመልከቻ ማስገባት የለባቸውም።

ፎርሙን ሥራ ባቆሙበት ወቅት ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ማስረከብ ይቻላል። ነገር ግን ከመውለጃው ቀን ከ9 ሳምንታት ቀድሞ መሆን የለበትም። (ከመውለዷ በፊት ፎርሙን የምታስገባ ወላድ ከሚንከባከባት ሐኪም በፎርሙ ውስጥ በግምት የምትወልድበትን ቀን እንዲጽፍ መጠየቅ ይኖርባታል)።
የቅጹ የመጨረሻው ማስረከቢያ ቀን ወላዷ የወሊድ ክፍያ ባለመብትነቷ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ 12 ወራት ነው።

> በወሊድ እረፍቷ ጊዜ የምትሠራ ወላድ የወሊድ ክፍያ መብቷን ታጣለች።

## የወሊድ ክፍያ ለአባት

እሱና ባለቤቱ የወሊድ ክፍያ መብት የሚያስገኘውን የዋስትና ወቅት አጠራቅመው ከሆነ፤ ቢያንስ ለ21 ተከታታይ ቀናት ከወሊዱ በኋላ 6 ሳምንታት ካለፉ አባት ባለቤቱን የመቀየር መብት አለው።

360/7ב የተሰኘውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል።
አንዲት እናት በጤና ማጣት ምክንያት ሕጻኗን መንከባከብ የማትችል ከሆነ በማንኛውም የወሊድ ዕረፍት ጊዜ ደረጃ ጊዜ ባለቤትዋ ሊቀይራት ይችላል። ይህም የሚሆነው እሱም የባለመብትነት ("ዛካኡት") ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ ነው።

ወላጅ አባት ሚስቱ አብራው የማትኖር ከሆነ በተወሰኑ መስፈርቶች የወሊድ ክፍያ መጠየቅ ይችላል።

## የዕረፍት ክፍያ ("ድሚይ ሁፍሻ") የማደጎ ልጅ ለሚያሳድጉ ወላጆች

የማደጎ ልጅ የሚያሳድጉ ወይም ማኅጸን ተከራይተው ልጅ በውጭጫገር አስውልደው ያመጡ የቅጥር ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ በዚህ ሂደት ምክንያት ወይም በሕጻኑ መወለድ ምክንያት ሥራቸውን አቋርጠው ከሆነ። ይህ ሊሆን የሚችለው የዕረፍት ክፍያ መብት የሚያስገኝላቸውን የዋስትና ጊዜ ካሟሉ ነው። ተጨማሪ መረጃ እና 356/7ב የተሰኘውን የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል።

## ጊዜያዊ እንክብካቤ ለሚያደርግ ("ኦሜኔት") ቤተሰብ የዕረፍት ክፍያ

6 ወራት በላይ ለሆነ ጊዜ እስከ 10 ዓመት የሆነን ልጅ ለመንከባከብ ዓላማ በቤትዋ የተቀበለች ወይም የተቀበለ የቅጥር ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ በመንከባከቡ ምክንያት ሥራቸውን አቋርጠው ከሆነ እና የዕረፍት ክፍያ መብት የሚያስገኝላቸውን የዋስትና ጊዜ ከሞሉ ይከፈላቸዋል። ተጨማሪ መረጃ እና 356/7ב የተሰኘውን የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል።

## የወሊድ ተቆራጭ ("ኪጽባት ለይዳ")

በአንድ ጊዜ ሦስት ልጅ እና ከዚያን በላይ የወለደች ወላድ ወይንም አንድ ቤተሰብ 3 ልጆች በጣም ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ከተወለዱለት – ከአንድ ወሊድ እስከሚቀጥለው ወሊድ ያለው የ98 ቀን ልዩነት ከሆነ – (ይህም በማኅጸን ኪራይ ልጅ የምታስወልደውንም ወላድ ይመለከታል) እና እንደዚሁም ሦስቱን ልጆች ከወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ሦስቱም ቢያንስ ለ30 ቀናት በሕይወት ከቆዩ። ወላዷ የወሊድ ተቆራጭ ባለመብት የምትሆነው ተኝቶ ለመታከምና ለወሊድ ስጦታ ባለመብት ከሆነች ነው።

የወሊድ ተቆራጭ (በወሊድ ስጦታ/ክፍያ በተጨማሪ) ከወሊዱ በኋላ በወሩ 1ኛ ቀን ጀምሮ ለ20 ወራት ያህል ይከፈላል። ከወሊዱ በኋላ ያለው የመጀመሪያው ወር ክፍያ ከወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ለ30 ቀናት በሕይወት በነበሩት ልጆች ቁጥር መሠረት ነው። በባለመብትነት ወቅት የተቆራጩ ("ቂጽባ") መጠን እየቀነሰ ይሄዳል። የተቆራጩን ክፍያ መጠን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል።

› ተቆራጩ የልጆች ተቆራጭ በሚከፈለው የባንክ ሒሳብ ቁጥር "አውቶማቲክ" በሆነ መንገድ የሚከፈል ሲሆን ማመልከቻ ማቅረብም አያስፈልም።

## እናቱ የሞተችበት የተወለደ ሕጻን ክፍያ

ወላዷ በወሊዱ ሰዓት ወይም ከተወለደ በአንድ ዓመት ውስጥ ሞታ ከሆነ እና ወላዷ የሆስፒታል መተኛ ክፍያ መብት ወይም የወሊድ ስጦታ/ክፍያ መብት ወይም የወሊድ ተቆራጭ መብት ካላት ለሕጻኑ ልዩ ክፍያ ይከፈለዋል።
ወላድ እናቱ ከሞተችበት የተወለደው ሕጻን ሁለት ዓይነት ክፍያዎች ይከፈሉታል፡

### ልዩ ተቆራጭ

በዚያን ጊዜ ለተወለደ እያንዳንዱ ልጅ እና እስራኤል ውስጥ ላለ ሕጻን ለሟቿ ባለቤት ወይም ለሕጻኑ ሕጋዊ ተወካይ ("አፖትሮፑስ") ይከፈላል። ልዩው ተቆራጭ ለ24 ወራት የሚከፈል ሲሆን የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ ወይም የጥገኝነት ተቆራጭ ለሕጻኑ ለ12 ወራት ይከፈላል። በጥር 2016 የአንድ ሕጻን ተቆራጭ በወር 2,839 ሼቄል ነው።

### ልዩ ድጐማ ("ታግሙል")

ወላዷ በመሞቷ ሕጻኑን ለመንከባከብ ሲል ባለቤቷ ሥራውን አቋርጦ ከሆነ ለወላዷ ባለቤት ይከፈላል። **የድጐማው መጠን ባለቤቷ ሥራውን ከማቆሙ 3 ወር በፊት የነበረው ደመወዝ 100% ይሆናል።** ድጐማው ከሰባት ቀን ሐዘን በኋላ ቢበዛ ለ14 ሳምንታት ያህል ይከፈላል፣ ይኸውም ደሞዙ በቀን ከሚከፈለው ልዩ ተቆራጭ የሚበልጥ ከሆነ ነው። ይህ ድጐማ እየተከፈለ እያለ ልዩ ተቆራጭ አይከፈልም።

### ለልዩ ተቆራጭ እና ለልዩ ድጐማ ጥያቄ አቀራረብ

ለቢቱዋሕ ሌኡሚ በፎርም 380/7ב ማቅረብ። ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል።

## ልጇን መንከባከብ ለማትችል አካለ ስንኩል ወላድ የሚከፈል ክፍያ

### ልዩ ድጐማ

የሚከፈለው ለአካለ ስንኩል ወላድ ባለቤት ሲሆን ይህም ደመወዝ ከሌላትና ሕጻኑን መንከባከብ የማትችል ከሆነ ነው። እንደዚሁም እሱ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኝ ሠራተኛ ከሆነና ሥራውን ሕጻኑን ለመንከባከብ ሲል የሚያቆም ከሆነ ነው። **የድጐማው መጠን የሚሰላው ባለቤቷ ሥራውን ከማቆሙ 3 ወር በፊት በነበረው ገቢ ላይ ተመርኩዞ ነው።** ድጐማውን ለመቀበል 361/7ב የተሰኘውንና ከኢንቴርኔት ላይ ሊወርድ የሚችለውን ፎርም መሙላት ያስፈልጋል።

### ልዩ ተቆራጭ

የሚከፈለው ልጅ ለብቻ ለምታሳድግ አካለ ስንኩል ወላድ ሲሆን ለወሊድ ክፍያ ባለመብት ካልሆነችና ልጇን ለመንከባከብ የማትችል ከሆነ ነው። **የተቆራጩ መጠን 2,839 ሼቄል** ሲሆን ለወላዷ የሚከፈለው ከወለደችበት ጊዜ አንስቶ ለ3 ወር ነው (ከአካለ ስንኩልነት ተቆራጭ በተጨማሪ)። ድጐማውን ለመቀበል 362/7ב የተሰኘውንና ከኢንቴርኔት ላይ ሊወርድ የሚችለውን ፎርም መሙላት ያስፈልጋል።

## ወላዷን በአምቡላንስ ለማጓጓዝ በወጪዎች መሳተፍ

ቢቱዋሕ ሌኡሚ ወላዷ በ"ማጌን ዳቪድ" አምቡላንስ ወደ ሆስፒታል በምትጓጓዝበት ወጪ ይሳተፋል። ዝርዝሩ በቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ።

## እርግዝናን ለመንከባከብ ("ሽሚራ") የሚከፈል ክፍያ

የምትሠራ ሴት በእርግዝናው ምክንያት ለራሷ እና ለጽንሱ የጤና ችግር የሚደርስ ከሆነ ያን ለማስቀረት ሥራዋን ካቆመች፣ ወይም የሥራዋ ቦታ የእሷን ወይም የጽንሱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ሆኖ አሠሪዋ ተለዋጭ ሥራ ያላገኘላት ከሆነ የእርግዝና እንክብካቤ ክፍያ ይከፈላል። ድጐማው የታቀደው ሴትየዋ በእርግዝና እንክብካቤ ጊዜ ለምታጣው ደሞዝ ካሳ ይሆን ዘንድ ነው።

### የክፍያው መጠን

ከእርግዝናው እንክብካቤ የቀደሙት ሦስት ወራት የሴትየዋ ደሞዝ አማካይ መጠን ሆኖ **በቀን ከ291.90 መብለጥ አይኖርበትም (ለጥር 2016)።**

### የዚህ ክፍያ ባለመብትነት መስፈርት

- የእስራኤል ኗሪ የሆነች ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ "ከወሳኙ ቀን" (የእርግዝና እንክብካቤውን ለመጀመር ሥራ ካቆመችበት) ቀደም ብሎ ካሉት 14 ወራት ውስጥ ቢያንስ የ6 ወራት የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ ለወላዷ ተከፍሎላት ከሆነ። **የ"ቢቱሀ ሌኡሚ" ክፍያ እንደተከፈለባቸው የሚቆጠሩት ወራት "ድሜ ለይዳ"ን ተመልከቺ።**
- የሴቶች እና የወሊድ በሽታ ልዩ ሐኪም እርግዝና እንክብካቤ ላይ እንደነበረች በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት – ቢያንስ ቢያንስ 30 ተከታታይ ቀናት። ለሌላ ተጨማሪ የእርግዝና እንክብካቤ ካስፈለጋት በእያንዳንዱ ተጨማሪ ወቅት ቢያንስ 14 ተከታታይ ቀናት።
- የቢቱዋሕ ሌኡሚ ልዩ ሐኪም ለእርግዝና እንክብካቤ ማመልከቻዋ ፈቃድ ከሰጠ።
- በእርግዝናው እንክብካቤ ምክንያት ከሌላ አካል ክፍያ የማትቀበል ከሆነ።

### ለእርግዝና እንክብካቤ ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ

በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የእርግዝና እንክብካቤ ፎርም 330/7ב ማቅረብ። ፎርሙን ከማንኛውም የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል። ከቅጹ ጋር የሴቶች ሐኪም ወይም የወሊድ በሽታ ባለሞያ የሞላው የሕክምና ማስረጃ መያያዝ አለበት።


› ከሕክምና ማስረጃው ጋር የሚቀርበው ፎርም የመጨረሻ ወቅት የእርግዝና እንክብካቤው ከጀመረ ከ12 ወራት በኋላ ነው።

## የልዩነት ክፍያ ለወሊድ ክፍያ፣ ለእርግዝና እንክብካቤ፣ የማደጎ ክፍያ

የወሊድ ክፍያ፣ የእርግዝና እንክብካቤ ክፍያ ወይም የማደጎ ክፍያ ያገኙ ቅጥር ሠራተኛ የወሊድ ክፍያ፣ የእርግዝና እንክብካቤ ክፍያ ወይም የማደጎ ክፍያ መብቷ ከተከበረ ጀምሮ በ11 ወራት ውስጥ ከአሠሪዋ ተጨማሪ ክፍያ፦ እንደ "ድሜ ሃቭራአ"፣ "ድሜ ቢጉድ"፣ ወይም "ቦነስ" ካገኙች እና ከመደበኛ ደሞዟ ሩብ በላይ ከሆነ ወይም ከእርግዝናዋ ዕረፍት ከቀደመው ጊዜ የነበረ የደሞዝ ልዩነት ከተቀበለች ያገኙችውን ክፍያ ልዩነት የማግኘት መብት ይኖራታል። ለወሊድ ዕረፍት የወጣም አባት የክፍያውን ልዩነት የማግኘት መብት አለው።

የባለመብትነቱን ምርመራ ለማድረግ ወላዷ በመኖሪያ አካባቢዋ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የእናቶች ክፍል የተከፈላትን ተጨማሪ ክፍያ የሚያሳየውን የደሞዝ መቀበያ "ትሉሽ" አያይዛ ጥያቄዋን ማቅረብ አለባት። ጥያቄውን የወሊድ ክፍያ መብቷ ከተከበረ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በ12 ወራት ውስጥ መላክ ያስፈልጋል።

# የልጆች ዋስትና



**የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ለእስራኤል አገር ኗሪ ሁሉ ለእያንዳንዱ 18 ዓመት ላልሞላው ልጁ የልጆች ተቆራጭ ያደርጋል።**

## የልጆች ተቆራጭ

ይህ የወር ተቆራጭ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የሚከፈል ሲሆን በእናትየዋ የባንክ ሒሳብ ወይም በእናትየዋ እና በባለቤቷ የጋራ ሒሳብ ይከፈላል። ተቆራጩ የሚከፈለው በቤተሰቡ የልጆች ብዛት መሠረት ነው።

### የልጆች ተቆራጭ መብት ያለው ማን ነው?

- የእስራኤል አገር ኗሪ የሆነ ባለዋስትና (በልዩ ሕጎች መሠረት እስራኤል ውስጥ የሚኖር)፣ አንድ ልጅ እና ከዚያን በላይ ያለው።
- ብቻውን ያለወላጅ ወደ እስራኤል አገር የገባ ልጅ።
- የራሱ ያልሆነ ልጅ የያዘ፣ እንደ ሞግዚት ("አፖትሮፑስ") ወይም እንደ ተቆራጭ ተቀባይ የተወከለ።

### የልጆች ተቆራጭ መብት መስፈርት

እስራኤል አገር ለሚኖር 18 ዓመት ላልሞላው ልጅ ተቆራጩ ይከፈላል። ውጪ አገር ለሚቀመጥ ልጅ ለመጀመሪያዎቹ 3 ውጪ የሚቀመጥባቸው ወራት ይከፈላል። ከ3 ወር በኋላ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቆራጩ ይከፈላል፦ ከወላጆቹ አንዱ በእስራኤላዊ አሠሪ ለሥራ ወደ ውጪ ከተላከ ወይም በ"ሻባቶን" ዓመት ላይ ከሆነ ወይም እሰራኤላዊ አሠሪ ጋ ውጪ አገር የሚሠራ ከሆነ፣ ከቤተሰቡ አንዱ ታሞ አገር ውስጥ ሊቀበሉት ካልቻሉ እና ለሕክምናው ሲባል ቤተሰቡ ውጪ ካለ።

የራሱ ያልሆነ ልጅ የያዘ፣ እንደ ሞግዚት ወይም እንደ ተቆራጭ ተቀባይ የተወከለ እና ልጁን ቢያንስ ባለፉት 12 ወራት እሱ የሚንከባከበው (የሚያኖረው) ከሆነ።

### የባለመብትነት ወቅት

ወር በገባ እስከ 15ኛው ቀን ድረስ የተወለደ ወይም ወደ እስራኤል አገር ለገባ ልጅ ለዚያ ወር ተቆራጩ ይከፈላል። ከ16ኛው ቀን ጀምሮ የተወለደ ወይም ወደ እስራኤል አገር ለገባ ልጅ ከሚቀጥለው ወር 1 ላይ ተቆራጩ ይከፈላል። የተቆራጩ ባለመብትነት 18 ዓመት በሞላው ወር ላይ ያቆማል።

### ለልጆች ተቆራጭ ጥያቄ አቀራረብ

በመጀመሪያው ልጅ ጥያቄው ልጁ በተወለደበት ሆስፒታል በኩል ይቀርባል። ስለዚህም ወላዷ የራሷን እና የባለቤቷን መታወቂያ ማምጣት እንዲሁም የራሷን የባንክ ሒሳብ ቁጥር ማምጣት ይኖርባታል። በሁለተኛው ወሊድ እና ከዚያን በላይ መረጃው ከሆስፒታሉ ቀጥታ ይተላለፋል። ወሊዱ ሆስፒታል ካልሆነ ወይም ከልጆቹ ጋር የተመለሰ ኗሪ ("ቶሻቭ ሆዜር") ለልጆች ተቆራጭ ጥያቄ በፎርም 5025 /ב ማቅረብ ያስፈልጋል።

ለባለዋስትናው ወይም ተቆራጭ ተቀባዩ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ዕዳ ካለበት ቢቱዋሕ ሌኡሚ ዕዳው በሙሉ እስኪከፈል ድረስ ከሚገኘው ተቆራጭ ሊቀንስ መብት አለው።

### በጥር 2014 የልጆች አጠቃላይ ተቆራጭ በሼቄል

- ከ1/6/2003 ጀምሮና ከዚያ በኋላ ለተወለዱ ልጆች፦

| በቤተሰቡ ውስጥ የልጁ ቦታ | የተቆራጩ መጠን |
|---|---|
| አንደኛ | 150 ₪ |
| ሁለተኛ | 188 ₪ |
| ሦስተኛ | 188 ₪ |
| አራተኛ | 188 ₪ |
| አምስተኛ እና ከዚያን በላይ | 150 ₪ |

- እስከ 31.5.2003 ድረስ ለተወለዱ ልጆች

| በቤተሰቡ ውስጥ የልጁ ቦታ | የተቆራጩ መጠን |
|---|---|
| አንደኛ | 150 ₪ |
| ሁለተኛ | 188 ₪ |
| ሦስተኛ | 188 ₪ |
| አራተኛ | 336 ₪ |
| አምስተኛ እና ከዚያን በላይ | 354 ₪ |

- "ሃፍታሃት ሃክናሳ"፣ ምግብ፣ የእርጅና ከገቢ ማሟያ ጋር፣ "ሽአሪም" ከገቢ ማሟያ ጋር የሚቀበሉት

ለሦስተኛው እና ለአራተኛው ልጅ ተጨማሪ ያገኛሉ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ **የ98 ሼቄል ተጨማሪ።**

> የሚደርሳችሁን የልጆች ተቆራጭ መጠን ለማወቅ – በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ወደሚገኘው **የልጆች ተቆራጭ ማስሊያ** ግቡ።

### ዘግይቶ የቀረበ ጥያቄ

ለልጆች ተቆራጭ በጊዘው ጥያቄ ካላቀረብክ፣ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ጥያቄው ከቀረበበት ሰዓት ጀምሮ ከዓመት በላይ ውዝፋን ያለመክፈል እና ጥያቄውን ባቀረብክበት ወቅት የማጽደቅ መብት አለው። ከሐምሌ 1/2003 በኋላ የተወለደ ልጅ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ በሕዝብ ቆጠራ ክፍል ካልተመዘገበ ዘግይቶ ቢመዘገብ የ3 ወራት ውዝፍ ብቻ ይከፈላል።

## የትምህርት ክፍያ

የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ቤተሰቦች በዓመት አንድ ጊዜ በነሐሴ ወር የልጆች ተቆራጭ ለሚቀበሉ ይከፍላል። ክፍያው/ስጦታው ከ6-14 ዓመት ዕድሜ ለሆኑ ልጆች ነው። ከባልና ሚስቱ አንዱ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የገቢ ዋስትና፣ ምግብ፣ የሙሉ አካለ ጎደሎነት ክፍያ፣ የእርጅና ወይም "ሽአሪም" ሆነው 4 ልጆች እና ከዚያን በላይ ያላቸውም ቤተሰቦች መብት አላቸው።

> በተደረገው የሕግ ማሻሻያ ከነሐሴ 2016 ጀምሮ () ስጦታው ዕድሜያቸው ከ6 – 18 ለሆኑ ልጆች ይከፈላል። የስጦታው መጠንም ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ ዓይነት ሲሆን መጥኑም 1,003 ሼቄል ነው።

እስከ ነሐሴ 2015 (ו"תשע የትምህርት ዘመን) ከ6-14 ዕድሜ ለሚገኙ ልጆች ስጦታው በሚከተለው መጠን ተከፍሏል። ከ6-11 ዓመት ለሆነው ልጅ፥ 1,557 ሼቄል እና ከ11-14 ዓመት ለሆነው ልጅ፥ 865 ሼቄል

> የሚደርሳችሁን የስጦታ ገንዘብ መጠን ለማወቅ – በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ የሚገኘውን የትምህርት ስጦታ ስሌት መኪና ተጠቀሙ።

ለክፍያው መብት ያላቸው ቤተሰቦች፦ የተፋታ/የተፋታች፣ ባል/ሚስት የሞተባት/በት፣ ያላገባ/ያላገባች፣ ከትዳር ጓደኛ ተነጥሎ/ተነጥል "ሃፍታሃት ሃክናሳ" የሚቀበል/የምትቀበል፣ "አጉና"፣ ከልጅ አባት/እናት በተለየ፣ በተወሰነ መስፈርት ከባልዋ/ሚስቱ ተለይቶ የሚኖር/ምትኖር፣ በባሎቻቸው በተደበደቡ ሴቶች መጠለያ የምትገኝ።

4 እና ከዚያ በላይ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ለትምህርት ክፍያ ባለመብት ይሆናሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው ከወላጆች ውስጥ አንዱ በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ በሐምሌ ወይም ነሐሴ ወር ላይ ከሚከተሉት ተቆራጮች ውስጥ አንዱን የሚቀበል ከሆነ ነው፥ "ሃብታሃት ሃክናሳ"፣ የልጆች ማሳደጊያ፣ የአካለ ስንኩልነት ክፍያ፣ የእርጅና ወይም "ሽአሪም" ክፍያ። "ሃብታሃት ሃክናሳ" የሚቀበሉ ወላጅ አልባ የሆኑ ወይም ዝም ብለው የተተው ልጆችም የትምህርት ክፍያ መብት አላቸው። እንደዚሁም ሁለቱም ወላጆች የሞቱባቸው፣ ያለ ወላጅ ወደ እስራኤል የገቡ ልጆች፣ ከዓመት በላይ እና ከሁለት ዓመት በታች እስራኤል ውስጥ የቆየ አዲስ ገቢ፣ ባልዋ/ሚስቱ ወደ እስራኤል ያልመጣና የማይኖር ባለ መብት ናቸው።

ስለክፍያው ተጨማሪ ዝርዝር እና የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል።

# በተጠባባቂ ውትድርና ("ምሉኢም") ለሚያገለግሉ የሚሰጥ ክፍያ



**በደኅንነት አገልግሎት ሕግ መሠረት እንዲሁም በሥራ አገልግሎት ሕግ መሠረት ለሥልጠና ለአስቸኳይ ግዳጅ ("ለሸዓት ሂሩም") ለሚጠራ ሁሉ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የ“ሚሉኢም” ክፍያ ይከፍላል።**

በደኅንነት አገልግሎት ሕግ መሠረት ወይም በሥራ አገልግሎት ሕግ መሠረት ለሥልጠና ለአስቸኳይ ግዳጅ ("ለሸዓት ሂሩም") የተጠራ፣ እያንዳንዱ ለሚሉኢም አገልግሎት የተጠራ ሁሉ የሚሉኢም ክፍያ ባለ መብት ነው።

ክፍያውን ለማግኘት ስለ አገልግሎት ቀናት ከእስራኤል መከላከያ ኃይል ማስረጃ ማምጣት ያስፈልጋል – የፎርም ቁጥር 3010።

## የ"ሚሉኢም" ክፍያ

- **ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ** – የ"ሚሉኢም" አገልግሎቱን ከጀመሩበት ወር ቀድመው የነበሩት የሦስት ወራት አጠቃላይ ደመወዝን ለ90 ማካፈል። በልዩ ሁኔታዎች/ምክንያቶች በ"ሚሉኢም" የሚያገለግል ሰው በሌሎች ወራት መሠረት ሒሳብ ይደረግለት ዘንድ መብት አለው። ዋጋው ከዝቅተኛው በታች ዝቅ አይልም፣ ከከፍተኛው በላይም ከፍ አይልም (ቀጥሎ ያለውን ተመልከት)።
- **ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ የሚኖረው ከፍተኛ ዋጋ ጥር 2016 – በቀን ሼቄል 1,441.33 ሲሆን በወር 43,240 ሼቄል ነው።**
- **ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ የሚኖረው ዝቅተኛ ዋጋ ጥር 2016 – በቀን 196.02 ሼቄል ሲሆን በወር 5,881 ሼቄል ነው።**

› የሚደርስህን የድጐማ ገንዘብ መጠን ለማጣራት በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ወደሚገኘው **የ"ሚሉኢም" ማስሊያ** ግባ።

## የ"ሚሉኢም" ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ

በጠያቂው ምርጫ መሠረት በአንዱ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ አገልግሎቱ እንዳለቀ የመከላከያውን ማስረጃ አያይዞ በፎርም ቁጥር 3010 የ"ሚሉኢም" ክፍያውን መጠየቅ ይቻላል። የመጠየቂያውንም ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

- **በወር ደሞዝ የሠራ ሠራተኛ እንዲሁም ያለ ወር ደሞዝም የሠራ ሠራተኛ**፣ አንድ አሠሪ ዘንድ ወይም አንድ መሥሪያ ቤት ከ"ሚሉኢሙ" አገልግሎት በፊት የነበሩትን ሦስት ወራት ቢያንስ 75 ቀናት ከሠሩ ዋጋውን ከአሠሪያቸው ይጠይቃሉ።
- **የግል ሠራተኛ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ፣ ከሥራ የወጣ እና ሥራ የማይሠራ** ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ይጠይቃሉ።
- **“ድሜ አቭታላ” የሚቀበሉ** – “ድሜ አቭታላ” በሚቀበልበት ወቅት ለተጠባባቂ ውትድርና ከወጣ ክፍያው ወዲያውኑ የሚከፈል ሲሆን ማመልከቻ ማቅረብ አይጠበቅበትም።

## የግል ጥያቄዎች አቀራረብ በኢንተርኔት

በቢቱዋሕ ሌኡሚ እንደ ግል ሠራተኛ የተመዘገቡና በተጠባባቂ ውትድርና የሚያገለግሉ፣ ሥራ የማይሠሩ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች፣ የየሺቫ ተማሪዎች ለ“ታግሙሌ ሚሉኢም” **የግል አገልግሎት በሚሰጥ ድረ ገጽ** አማካይነት ማቅረብ ይችላሉ።

ይህ አገልግሎት የሚሰጠው በኮድና “ፓስወርድ” አማካይነት ሲሆን ይህንንም በድረ-ገጹ አማካይነት ወይም ከመኖሪያ አካባቢኢ ከሚገኝ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍም መቀበል ይቻላል።

## የ“ሚሉኢም” ጉዳዮችን አስመልክቶ የመረጃ ማዕከል ስልክ 02-6463010 ነው

ቢቱዋሕ ሌኡሚ ማመልከቻቸውን በግላቸው ለሚያቀርቡ ተጠባባቂ ወታደሮችና ሠራተኞቻቸው በተጠባባቂ ውትድርና አገልግሎት ላይ ላሉ አሠሪዎች አውቶማቲክ የሆነ የስልክ ማዕከል አለው።

በማዕከሉ ስለመብቶችና ግዴታዎች አጠቃላይ መረጃ፣ ማመልከቻ የሚቀርብባቸው ቅጾች፣ የተቆራጭ ማስሊያ “ሲሙሌተር”፣ ወዘተ. ይገኛሉ።



# ግዴታውን ጨርሶ ለተሰናበተና ተመራጭ ("ሙዕዴፌት") ሥራ ለሚሠራ ወታደር የሚሰጥ ስጦታ



**ግዴታውን ጨርሶ ለተሰናበተ ወታደር ወይም ብሔራዊ አገልግሎት ለጨረሰና ለኢኮኖሚው ጠቃሚ ነው ተብሎ በሚገመቱ ሥራዎች ላይ ለተሰማራ የሚሰጥ ስጦታ ነው።**

## ለተመራጭ ሥራ ("ለአቮዳ ሙዕዴፌት") የሚሰጥ ስጦታ

በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ መሠረት ከአስገዳጅ ውትድርና የተሰናበቱና ለ24 ወራት በብሔራዊ አገልግሎት ("ሼሩት ሌኡሚ") ያገለገሉ ወታደሮች በሕጉ መሠረት እንደ ተመራጭ ("ሙዕዴፊት") የሚቆጠር ሥራ ከሠሩ የአንድ ጊዜ ስጦታ ይከፈላቸዋል። እነዚህ ሥራዎች በማምረቻ ፋብሪካዎች፣ "በወርክ ሾፖች"፣ በግንባታ ማዕከሎች፣ በነዳጅ ማደያዎች፣ በሆቴሎች፣ በግብርና ቦታዎች፣ በማሸጊያ ቤቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች የግል እርዳታ እንክብካቤ ናቸው። በእነዚህ መስኮች በጸሐፊነት ከሚሠሩት ውጪ ማለት ነው።

**ስጦታ የሚያስገኙ ሥራዎችን ዝርዝር በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።**

> በ"ኪቡጽ" ወይም በጋራ ሰፈራዎች ("ሞሻቪም") ውስጥ "ተመራጭ ሥራ" የሠሩ የ"ኪቡጽ" ወይም የጋራ ሰፈራዎች "ሞሻቪም" አባላት የሆኑ የተሰናበቱ ወታደሮች የዚህ ስጦታ ባለመብት ናቸው።

## ማነው የስጦታው ባለመብት?

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ስጦታው ይከፈለዋል፣

- በተፈላጊ ሥራ ቢያንስ 6 ሙሉ ወራት የሠራ፣ በተከታታይም ላይሆን ይችላል። ከግዳጅ አገልግሎት ከተሰናበተ ጀምሮ በ24 ወራት ውስጥ።
  ሥራው እንደ ሥራው ቦታ ባህሪይ ሆኖ የሙሉ ጊዜ ሥራ መሆን አለበት።

  በግብርና መስክ ቢያንስ 4 ወራት ብቻ መሥራት እና ስጦታውን በከፊል መውሰድ ይቻላል።

  **የዕረፍት ቀናት፣ የበሽታ ቀናትና የውትድርና አገልግሎት ቀናት እንደ ሥራ ቀናት አይታዩም፤** ለእነዚህ ቀናት ክፍያ ከአሠሪ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ብትቀበልም። ከግዳጅ ውትድርና ተለቅቀህ በሁለት ዓመታት ውስጥ በተጠባባቂ ውትድርና አገልግለህ ከሆነ፣ አስፈላጊ ሥራ ("ዓቮዳ ኒድረሽት") የምትሠራበት ጊዜ ይራዘምልሃል። ይህም ከሚጠራቀመው የተጠባባቂ ውትድርና አግልግሎት ጊዜ ተመሳሳይ ነው።

  በሥራ ቦታህ ላይ የሳምንቱ ሥራ 5 ቀናት ቢሆንና በሳምንት 5 ቀን ብትሠራ፣ የሥራ ቀናትን ለማጠራቀም በሳምንት 6 ቀን እንደሠራህ ይቆጠራል።

- የሥራው መጀመሪያ – ከመሰናበቻው ቀን ጀምሮ በ12 ወራት ውስጥ ወይም በሁለተኛው ዓመት – ለሥራ አጥ ክፍያ መብት ከነበረው በሥራ መጀመሪያው ቀን

> የስጦታው ባለመብትነት በሥራ አጥነት ክፍያ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ እንደዚሁም ከውትድርና ግዳጅ በተለቀቅህበት የመጀመሪያው ዓመት ላይ ለሥራ አጥነት ክፍያ ባለመብት በመሆንህ – ከውትድርና እንደተለቀቅክ በመጀመሪያው ዓመት ላይ "አስፈላጊ ሥራ" እንድትሠራ ትመከራለህ።

## የስጦታው መጠን

**በጥር 2016 እና ከዚያ በኋላ እሙሉ ስጦታውን መጠን 9,550 ሼቄል ነው።**
**ለእርሻ የሚከፈለው ከፊል ክፍያ 6,367 ሼቄል ነው።**

"ዓቮዳ ኒድረሽት" ከመጀመሩ አስቀድሞ ባሉት 11 ወራት ውስጥ የሥራ አጥ ክፍያ የተቀበለ ሰው የወሰደው የሥራ አጥ ክፍያ ከሚሰጠው ስጦታ ይቀነሳል።
በተወሰኑ ሁኔታዎች ወታደሩ ለከፊል ስጦታ ብቻ ባለመብት ይሆናል።

## የስጦታው ጥያቄ አቀራረብ

የስጦታውን ጥያቄ ቢያንስ ከ6 ሙሉ ወራት ሥራ በኋላ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ማቅረብ ነው፣ እና ከመደበኛ የውትድርና አገልግሎት ከተሰናበትክበት ቀን ጀምሮ ከ42 ወራት በላይ መዘግየት የለበትም።

ጥያቄው ላይ የሥራውን ቦታ ማስረጃዎች፦ የሥራውን ዓይነት እና የሥራውን ወቅት እንዲሁም በእያንዳንዱ ወር ያለውን የሥራ ቀናት ብዛት የተጠቀሰበት ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

የመጠየቂያ ፎርም የሆነውን 1521/ל2 ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ በማውረድ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

> **አዲስ!** ማመልከቻውን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ በመሙላት ከሁሉም ሰነዶች ጋር ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት "ኦንላይን" ላይ ሆኖ መላክ ይቻላል።

## ጠቃሚ ምክር

ውትድርና ለጨረሰው ሥራ ተገኝቶለት ከሆነና፣ ሥራው ደግሞ በ"ዓቮዶት ኒድራሾት" ዝርዝር ውስጥ ከሌለ፣ ወይም ደግሞ ሥራው "ዓቮዳ ኒድሬሼት" ለመሆኑ ጥርጣሬ ካለው፣ በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ በሚገኝ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ እንዲያጣራ ይመከራል።

- **የደኅንነት ሠራተኞች፣ የጥበቃ ሠራተኞችና የጽዳት ሠራተኞች** በ"ዓቮዳ ኒድሬሼት" እንደሚሠሩ የሚቆጠሩት በሚከተሉ ቦታዎች የሠሩ እንደሆነ ነው፣ የግንባታ ቦታዎች፣ ፋብሪካዎች፣ የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች፣ የእርሻ ቦታዎች፣ የማሸጊያ ቦታዎችና ሆቴሎች።

- **በፋብሪካ የሚሠራ ሞያተኛ** (የ"ሐይቴክ" ኢንዱስትሪዎችን ይጨምራል)፣ በእጁ የሙያ ምስክር ወረቀት ካለው፣ በሠለጠነው ሙያ የሚሠራ ከሆነ፣ ስጦታውን ለመቀበል ባለመብት አይሆንም። ይህም የማያጠቃልለው ሙያዊ ባልሆነ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ያለን ወይም "በባለመብት ሥራዎች ዝርዝር" ውስጥ ከተዘረዘሩት ሙያዊ ሥራዎች ውስጥ አንዱን የሚሠራ ከሆነ ነው።

በሁሉም የሥራ ቅርንጫፎች ሆነ በሌሎች ዝርዝር የሥራ ዓይነቶች – **የቢሮ/የጽሕፈት ሥራ የሚሠራ ስጦታ አያስገኝም።** ለምሳሌ ያህል፣ ጸሐፊነት፣ ታይፒስትነት፣ የሒሳብ አያያዝ፣ የቤተ መዘክር ሥራ፣ የሆጠል አስተናጋጆች፣ በቴለፎን ማእከል የሚሠሩ፣ ወዘተ.

# የሥራ አጥ ዋስትና



**የሥራ አጥ ("አብታላ") ዋስትና የታቀደው ከሥራ የተሰናበተው ለተወሰነ ጊዜ የደመወዝ አማራጭ እንዲኖረው ለማድረግና የሚስማማውን ሥራ ለመፈለግ ይችል ዘንድ ነው።**

## የሥራ አጥ ክፍያ

### የሥራ አጥ ክፍያ ዋስትና ያለው ማን ነው?

የእስራኤል አገር ኗሪ ወይም ለጊዜው እስራኤል አገር የሚኖር ከ18 ዓመት ጀምሮ እስከ 67 ዓመት ዕድሜ ድረስ ፣ በተቀጣሪነት የሠራ ወይም ከመደበኛ ("ሳዲር") አገልግሎቱ ለመሰናበት የመጀመሪያ ዓመት ላይ ያለ ወታደር።

### የሥራ አጥ ክፍያ መስፈርቶች

1. **ዕድሜ**- 20 ዓመት ሞልቶህ ገና 67 ዓመት አልሞላህም፣ በተወሰኑ መስፈርቶች ከ18-20 ዓመት ዕድሜ ያሉም።
2. **ለሥራ አጥ ክፍያ የተገቢነት ወቅት ("ትኩፋት አክሻራ") ማሟላት**

- ከሥራ ለመሰናበት ("ለአብታላ") ከቀደሙት 18 ወራት ውስጥ ለ12 ወራት ከቢቱዋሕ ሌኡሚ" ክፍያ የተከፈሉለት ሰው።
- ግዳጇን ጨርሶ የተሰናበተ ወታደር፣ በብሔራዊ አገልግሎት ("ሺሩት ሌኡሚ") ወይም በሲቪል ብሔራዊ አገልግሎት 24 ወራት ያገለገለ። እነሱም፣ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ እንደማኛውም ሥራ አጥ የተገቢነት ወቅት ("ትኩፋት አክሻራ") ማጠራቀም አለባቸው። ሆኖም ግን እንደተገቢነት ወቅት የሚታሰቡት በመደበኛው ውትድርና፣ በብሔራዊ አገልግሎት ወይም በብሔራዊ የሲቪል አገልግሎት ያገለገልክባቸው 6 ወሮች ናቸው።

  በ"ሼሩት ታዓሱካ" አማካይነት ወደ ሙያዊ ሥልጠና ተልከው ከሆነ፣ ከውትድርና ወይም አገልግሎት በተለቀቁበት መጀመሪያ ዓመት ላይ "ተገቢ ወቅት" ከሚባለው መስፈርት ነጻ ይሆናሉ።

3. **ሥራ አጥ ነህ**– በ"ታዓሱካ" አገልግሎት ጽ/ቤት ተመዝግበህ ከሆነ፣ በሙያህ ወይም ሌላ ተስማሚ ሥራ ውስጥ ተሠማርተህ ለመሥራት ዝግጁ ከሆንክና መሥራት የምትችል ከሆነና የ"ታዓሱካ" አገልግሎት ጽ/ቤት ሥራ ካላቀረበልህ።

### ለሥራ አጥነት ክፍያ ከፍተኛው የባለመብትነት ጊዜ

- የሥራ አጥ ("አብታላ") ክፍያ 45 ዓመት ለሞላው ወይም 35 ዓመት ለሞላው እና አብሮት ቢያንስ 3 ጥገኞች* ላሉት ከሥራ የተሰናበተ ቢበዛ የ175 ቀናት፣
- 35 ዓመት ለሞላው ወይም ገና 35 ዓመት ያልሞላው እና አብሮት ቢያንስ 3 ጥገኞች* ላሉት ከሥራ የተሰናበተ ቢበዛ የ138 ቀናት፣
- 28 ዓመት ለሞላው ገና 35 ዓመት ያልሞላው እና አብሮት 3 ጥገኞች* የሌሉት ከሥራ የተሰናበተ ቢበዛ የ100 ቀናት፣
- 25 ዓመት ለሞላው ገና 28 ዓመት ያልሞላው እና አብሮት 3 ጥገኞች* የሌሉት ከሥራ የተሰናበተ ቢበዛ የ67 ቀናት፣
- ገና 25 ዓመት ያልሞላው እና አብሮት 3 ጥገኞች* የሌሉት ከሥራ የተሰናበተ ቢበዛ የ50 ቀናት፣
- ግዳጇን ጨርሶ የተሰናበተ ወታደር፣ በብሔራዊ አገልግሎት ("ሺሩት ሌኡሚ") ወይም በሲቪል ብሔራዊ አገልግሎት 24 ወራት ያገለገለ ቢበዛ 70 ቀናት።

* ጥገኞች የሚባሉት የማይሠራ ባል ወይም የማትሠራ ሚስት እና 18 ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው።

### የሥራ አጥ ክፍያ መጠን

- **በቀን የሚታሰበው የሥራ አጥ ("አብታላ") ክፍያ መጠን ሥራ አጥነቱ ከጀመረበት ወር 1 በፊት ያሉት የ6 ወራት ደሞዝ አማካይ ሒሳብ ነው።**
- **በመጀመሪያዎቹ 125 ቀናት በቀን የሚታሰበው የሥራ አጥ ክፍያ መጠን ከአገሪቱ አማካይ የቀን ደሞዝ ክፍያ በላይ አይወጣም። (በጥር 2016 – በቀን 378.56 ሼቄል ነው።)፣ ከ126ኛው ቀን ጀምሮ ከአገሪቱ አማካይ የቀን ደሞዝ ሁለት ሦስተኛ በላይ አይወጣም። (በጥር 2016 – በቀን 252.37 ሼቄል ነው።)**

ለእያንዳንዱ የመጀመሪያ 5 የሥራ አጥነት ቀናት በያንዳንዱ 4 ተከታታይ ወራት የሥራ አጥ ክፍያ አይከፈልባቸውም።

> የሥራ አጥነት ክፍያ ይደርስህ እንደሆነ ለማወቅና የሚደርስህን የሥራ አጥነት ክፍያ መጠን ለማወቅ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ወደሚገኘው **የሥራ አጥነት ክፍያ ማስሊያ** ግባ።

### በሥራ አጥነት ወቅት የምታገኛቸው ገቢዎች

ሥራ አጥ የሆነ ሰው በሥራ አጥነቱ ወቅት ከቅጥር ሥራ፣ ከግል ሥራ ወይም ከጡረታ ገቢ ካለው ከሚደርሰው የሥራ አጥነት ገቢ ላይ እነዚህ ገቢዎች ይቀነሳሉ። ስለነዚህ ገቢዎች ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል።

### በዝቅተኛ ደሞዝ ለሚሠራና ከሥራ የተሰናበተ ሰው የሥራ አጥ ክፍያ

በሥራ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ("ሸሩት ሃታዓሱካ") ከሥራ አጥ ክፍያው ላይ በዝቅተኛ ደሞዝ ወደሥራ ለተላከ ከሥራ የተሰናበተ ሰው ይደርሰው በነበረው የሥራ አጥ ክፍያ እና በዝቅተኛ ደሞዝ የሚሠራው ሥራ የአንድ ሁለተኛ/ግማሽ ደሞዝ ልዩነት ለሆነ መጠን ስጦታ ባለመብት ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው ቢያንስ 25 ቀናት በ50% የሥራ ጊዜ ("ሚስራ") ከሠራ ነው። ስጦታው የሚከፈለው ቢበዛ ለ100 የሥራ ቀናት ነው።

### አዲስ ሥራ መሥራት የጀመረ ሥራ አጥ

አዲስ ሥራ መሥራት የጀመረ ሥራ አጥ፣ በማንኛውም ምክንያት ሥራውን ቢያቆም ወደ "ሸሩት ታዓሱካ" በመመለስና በማመልከት የሥራ አጥነት ክፍያ ሊያገኝ ይችላል። ይህም በዓመት ውስጥ ለሚያገኛቸው ከፍተኛ የሥራ አጥነት ቀናት ሲሆን ለሥር አጥነት አዲስ ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልገውም።

### የሥራ አጥ ክፍያ በሞያ ትምህርት ላይ ለሚሳተፍ

"ሸሩት ታዓሱካ" ለሞያ ትምህርት ልኮት የሥራ አጥ ክፍያ ባለመብት ሆኖ ባለበት ወቅት ትምህርቱን ጀምሮ ከሆነ በሞያዊ ሥልጠናዎች ላይ ለቆየባቸው ቀናት የሥራ አጥነት ክፍያ ይከፈለዋል። ይኸውም ከፍተኛው የሥራ አጥነት ክፍያው እስከሚያልቅበት ወቅት ድረስ ነው።

በትምህርት ላይ ሆኖ የሚከፈለው የሥራ አጥ ክፍያ በሥራ አጥነት ይደርሰው ከነበረው ክፍያ 70% ይሆናል። ይህም ሥራ አጥ ከሆነና ኮርስ የማይማር ከሆነ ነው። ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ሆኖ፡- ሙሉ የሥራ አጥነት ዋስትናዎች የሚከፈሉባቸው የሙያ ሥልጠናዎች ተወስነዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሙያዊ ሥልጠና የሚማር ሰው ከፍተኛው የሥራ አጥ ክፍያ ከሚከፈልበት ቀናት የሚዘል ክፍያ ሊከፈለው ይችላል። ነገር ግን ቀናቱ ከ138 አይበልጡም።

> **ያለ በቂ ምክንያት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ሰው፣** የሥራ አጥ ክፍያውን መቀበል የሚጀምረው ሥራውን ካቆመ ከ90 ቀናት በኋላ ነው።

> **የሚስማማው ሥራ ተገኝቶለት ያልተቀበለ ሰው፣** የሥራ አጥ ክፍያውን መቀበል የሚጀምረው ሥራውን አልፈልግም ካለበት ከ90 ቀናት በኋላ ነው፣ በያንዳንዱ ሥራ አለመቀበል ከሚደርሰው ከፍተኛ የሥራ አጥ ክፍያ ላይ የ30 ቀናት ይቀነሱበታል።

### የሥራ አጥ ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ

ለመጀመሪያ ጊዜ የሥራ አጥ ክፍያ ለመቀበል በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል። የመጠየቂያ ፎርም የሆነውን 1500/לב ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ በማውረድ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

> **አዲስ!** ማመልከቻውን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ በመሙላት ከሁሉም ሰነዶች ጋር ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት "ኦንላይን" ላይ ሆኖ መላክ ይቻላል።

### ለሥራ አጥ ክፍያ ዳግመኛ ጥያቄ ማቅረብ

ቀደም ብሎ ከነበረው የባለመብትነት መጀመሪያ ቀን ጀምሮ 12 ወራት ካለፉ በኋላ ብቻ ጥያቄውን ማቅረብ ይቻላል። 40 ዓመት ያልሞላቸው ሥራ አጦች በ4 ዓመታት ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ የሥራ አጥ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርቡ በእያንዳንዱ ጥያቄያቸው ከሚደርሳቸው ከፍተኛ የቀን ብዛት 180% የሥራ አጥ ክፍያ ይቀበላሉ (በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደተዘረዘረው)። ለተጨማሪ ወቅት የሚሰጥ የሥራ አጥ ክፍያ መጠን ከሚደርሰው የሥራ አጥ ክፍያ 85% በላይ አያልፍም።

# የሠራተኞች መብት
## በኪሳራና ድርጅት መፍረስ ምክንያት

**አሠሪው የከሰረ ወይም የሚሠራበት ድርጅት የፈረሰ ተቀጣሪ ሠራተኛ የሥራ ደሞዝ ክፍያ እና የሥራ መፈለጊያ ካሳ ("ፒጹይ") ከአሠሪው ሊያገኝ መብት አለው።**

### ለድጐማው መብት ያላቸው

- አሠሪው የከሰረ ወይም የሚሠራበት ድርጅት እንዲፈርስ ተዕዛዝ የተሰጠው (አሠሪው ኮርፖሬሽን ከሆነ)።
- በሥራ መፈለጊያ ካሳ ሕግ ቁጥር 5 መሠረት ለሥራ መፈለጊያ ካሳ ባለመብት የሆኑ ሠራተኞች።
- "ኩፓት ጊሜል"፣ አሠሪው የሠራተኛው ዋስትና ያለበት "ኩፓት ጊሜል" ዕዳ ካለበት።

### ለድጐማው መብት የሌላቸው

- የግል ሠራተኛ ወይም በኩባንያው ውስጥ አክሲዮን ("ምናያ") ያለውና በእሱና በኩባንያው መካከል የሠራተኛና-አሠሪ ግንኙነት ካልነበረ
- ኃላፊነቱ በተወሰነ ኩባንያ ውስጥ ቁጥጥር ያለው፣ እንደዚሁም የውጭ ሀገርና የመስክ ሠራተኞች ሆነው እስራኤል ውስጥ በሕገወጥ መንገድ የሚኖሩ ከሆነ

### የባለመብትነት መስፈርቶች

- በአሠሪው ላይ ፍርድ ቤት እንደከሰረ ትእዛዝ፣ ወይም ድርጅቱ እንዲፈርስ ትእዛዝ፣ ወይም የጋርዮሽ ("ሹትፋት") ማፍረሻ ትእዛዝ፣ የትብብር ማኅበር/ቡድን ማፍረሻ ትእዛዝ ቢያወጣበት።
- የሠራተኛው ክስ/ጥያቄ በከሳሪው ባለአደራ ወይም በድርጅቱ አፍራሽ ከተፈቀዱ።

### የጡረተኛነት ክፍያ መጠን

#### ለሠራተኛ

ሥራ በሚቆምበት ጊዜ አሠሪው ለሠራተኛው የሚፈለግበት የሥራ ደሞዝ እና ካሳ በቢቱዋሕ ሌኡሚ በተወሰነው ከፍተኛ ድረስ ነው። **እስከ 31.7.09 ለአሠሪው የመፍረስ ትድረ ገጽዕዛዝ/የኪሳራ ትዕዛዝ የተሰጠው፣ የክፍያው ከፍተኛ መጠን 86,480 ሼቄል ነው (ጥር 2014)፤ ትዕዛዙ በ1.8.09 እና ከዚያን በላይ ከተሰጠ የክፍያው ከፍተኛ መጠን 11,2424 ሼቄል ነው (ጥር 2014)።**

#### "ለሻኢሪም"

በደሞዝ ማስከበሪያ ሕግ ቁጥር 7 መሠረት የሚደርሳቸው የሥራ ደሞዝ እና በሥራ ስንብት ካሳ ሕግ ቁጥር 5 መሠረት በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ ውሳኔ ከፍተኛ ድረስ።


#### "ለኩፓት ጌሜል"

ወደ "ኩፓት ጊሜል" ከሠራተኛው ገንዘብ ወይም ከአሠሪው ገንዘብ ወይም ደግሞ የሁለቱም ክፍያ ያልተላለፈ ከሆነ በቢቱዋሕ ሌኡሚ በተወሰነው ከፍተኛ ድረስ ይከፈላል **ጥር 2016 ላይ 17,296 ሼቄል ነው።**

#### የጋራ ማኅበር/ቡድን አባል ለሆነ

በጋራ ማኅበር ሰፈራ ወይም በኪቡጽ ቢያንስ ለ7 ዓመታት አባል የነበረ – በሕጉ እስከተወሰነው ከፍተኛ ጣራ መሠረት፥ **ጥር 2016 ላይ 69,184 ሼቄል ነው።**

ለተለያየ ጡረታ/ክፍያ ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።



# የበጎ አድራጊዎች መብቶች

**በበጎ አድራጎት ሥራው ላይ ሆኖ ጉዳት የደረሰበት የበጎ አድራጎት ሠራተኛ ወደ ሥራ መሄጃ እና መምጫውን ጨምሮ እንዲሁም በዚህ ሁኔታ ሕይወቱ ያለፈ በጎ አድራጊ ጥገኛ ለሆኑም በዚህ ምዕራፍ እንደተጠቀሰው ክፍያ ይሰጣል። "የሥራ ላይ ጉዳት ዋስትና" እዚያ በተገለጹት የባለመብትነት መስፈርቶች መሠረት።**

**"የበጎ አድራጎት ሠራተኛ"** – የበጎ አድራጎት ሠራተኞችን በመደልደል በታወቀ ሕጋዊ በሆነ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅት አማካኝነት አስቀድሞ ተመርቶ ያለደሞዝ የተቸገረ ለመርዳት የሚሠራ፣ እና ሥራው ብሔራዊ ወይም ሕዝባዊ ጥቅም ያለው፣ ያለደሞዝ እና በእስራኤል መከላከያ አገልግሎት ሥራ ክልል ስር ያልሆነ በሕጉ መሠረት የደህንነት ግዴታ የሚወጣ፣ በፍርድ በተጣለበት ግዴታ መሠረት ለተቸገረ የእርዳታ እጁን የሚዘረጋ ወይም የችግረኛን ሕይወት ወይም ንብረት ለማዳን ተግባር የፈጸመ፣ የሕዝባዊ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም በሕጋዊ ቅጣቱ ሕዝብን የሚያገለግል፣ በ"ማጌን ዳቪድ አዶም" ነጻ አገልግሎት የሚሰጥ፣ በመጀመሪያ እርዳታ ድርጅት የሚያገለግል፣ በአካል እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በሚከላከል ድርጅት የሚያገለግል ወይም በሽተኞችን በሚንከባከብ ወይም ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ሰዎችን በሚንከባከብ ድርጅት ውስጥ የሚያገለግል፣ የመቃብር/ቀብር ክንውኖችን የሚያካሂድ ድርጅት፦ በእርዳታ እና ማስተባበሪያ ሚኒስቴር የተፈቀደ ብቻ፣ በእሳት አደጋ መሥሪያ ቤት የሚሳተፍ፣ በ"ማህሌቭ" ("ቪስኮንሲን/ኦሮት ለታዓሱካ" ፕሮግራም) ፕሮግራም ሥር ያለ ደሞዝ ማህበረሰባዊ አገልግሎት የሚሰጥ፣ የሲቪል አገልግሎቶችን የሚሰጥ በሕጉ እንደሚባለው "ድህያት ሺሩት" ለ"የሺቫ" ተማሪዎች።

### የክፍያው መጠን


ለበጎ አድራጎት ሠራተኛ የሚሰጥ ክፍያ/ጡረታ በሥራ ላይ ለተጎዳ ሠራተኛ ከሚከፈለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ከመጎዳቱ በፊት ያልሠራ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ያለው የበጎ አድራጎት ሠራተኛ፣ **በቀን 109.47 ሼቄል ድጐማ ይከፈለዋል።**

### የክፍያው ጥያቄ አቀራረብ

ጥያቄውን ጉዳቱ ከደረሰ ጀምሮ 12 ወራት መጨረሻ ላይ በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።

የመጠየቂያውን ፎርም ከ"ቢቱዋሕ ሌኡሚ" ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

# በጠላት ተግባራት ጉዳት ለደረሰባቸው ካሳ



በጠላት ተግባራት ጉዳት ለደረሰባቸው የተደነገገው የጥቅማጥቅም ሕግ ለተጐእዱት ሰዎችና እና ለቤተሰቦቻቸው የመደጐሚያ፣ የማገገሚያና የጥቅማጥቅም መብት ያስገኛል።

**በጠላት ተግባራት ጉዳት ለደረሰባቸው ካሳ ባለመብት ማን ነው?**

የእስራኤል አገር ኗሪ ሆኖ በእስራኤል አገር ወይም በውጪ አገር በጠላት ተግባራት ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፣ እስራኤላዊ ዜጋ እና በሕጋዊ መንገድ ወደ እስራኤል ገብቶ እስራኤል ውስጥ በጠላት ተግባራት ጉዳት የደረሰበት፣ የውጪ አገር ሰው ሆኖ በውጪ አገር እስራኤላዊ አሠሪ ዘንድ እየሠራ (ለዚህ ጉዳይ ተፈቅዶ) በጠላት ተግባራት ጉዳት የደረሰበት።

**"የጠላት ጉዳት"** – በጠላት ኃይሎች ተግባራት ጉዳት የደረሰበት ወይም በጠላት ኃይሎች ተግባራት እንቅስቃሴ ወቅት ወዲያው በስህተት ጉዳት የደረሰበት ወይም የጠላት ተግባር ሊሆን የሚችል ጥርጣሬ ባለባቸው ምክንያቶች ሁኔታ፣ ለጠላት ተግባር ተነጣጥሮ ከነበረ መሳሪያ ወይም የጠላትን ተግባር ለማክሸፍ ተነጣጥሮ ከነበረ መሳሪያ እንዲሁም አንድን ሰው በማንነቱ/በዘሩ ምክንያት በእሥራኤሎች አረቦች ሽኩቻ ብቻ ተነጣጥሮ የሃይል መጠቀም ድርጊት በአሸባሪ ድርጅት ቢፈጸም - ድርጊቱ በመከላከያ ሚኒስቴር በተመረጠ አካል የጠላትነት ተግባር መሆኑን ካረጋገጠ።

## በጠላት ተግባራት ጉዳት ለደረሰባቸው ካሳ

### በሕክምና እንክብካቤ ወቅት የሚሰጥ ካሳ

በጠላት ተግባራት ጉዳት የደረሰበት እና በዚያ ምክንያት በሕክምናው ወቅት ሥራ መሥራት የማይችል እና በዚህ ወቅት ደሞዝ ወይም ካሳ የማይከፈለው ከሆነ የልዩ ክፍያ ባለመብት ነው።

**የድጐማው መጠን ብቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ተዘርዝሯል።**

**ለጠላት ተግባራት ጉዳት እውቅና እንዲሰጥ ጥያቄ አቀራረብ የሕክምና እንክብካቤ** ጥያቄውን ጉዳቱ ከደረሰ ጀምሮ 12 ወራት መጨረሻ ላይ በፎርም (580/לב) በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።
የመጠየቂያውን ፎርም ከ"ቢቱዋሕ ሌኡሚ" ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

### የአካል ጉዳተኝነት ወራዊ ካሳ/ክፍያ

በጠላት እኩይ ተግባር ተጎድቶ የ20% እና በላይ የአካል ጉዳት ደረጃ የተወሰነለት ተጎጂ።
የካሳው መጠን በአካል ጉዳቱ አንጻር ይወሰናል።

**የ100% የአካል ጉዳት ደረጃ ያለው የአካል ጉዳተኛ በጥር ወር 2016 ዓ.ም. ላይ የ4,466 ሼቄል ካሳ ይከፈለዋል።**
በጠላት ተግባር ጉዳት የደረሰበት የአካል ጉዳተኛ በአካል ጉዳተኞች ሕግ መሠረት (ካሳ እና ማገገሚያ) ከእስራኤል የመከላከያ ኃይል የአካል ጉዳተኛ ጋር እኩል የሆነ ክፍያ ይከፈለዋል።
**ከ10% – 19% ቋሚ የአካል ጉዳት የተወሰነለት የአካል ጉዳተኛ የአንድ ጊዜ የአካል ጉዳተኝነት ስጦታ ይከፈለዋል።**
**የአካል ጉዳተኝነት ወራዊ ካሳ/ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ**
ጥያቄውን ጉዳቱ ከደረሰ ጀምሮ 12 ወራት መጨረሻ ላይ በፎርም (581/לב) በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።
የመጠየቂያውን ፎርም ከ"ቢቱዋሕ ሌኡሚ" ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

### ልዩ ልዩ ካሳዎች/ድጐማዎች

ድጋፍ ለሚያስፈልገው የአካል ጉዳተኛ ("ነሔ ኒጽራሕ") እና መተዳደሪያ አልባ ለሆነ የአካል ጉዳተኛ ከፍተኛ መጠን ያለው ካሳ ይከፈላል።

በቅድሚያ የጡረታ መብት ከሥራው ቅድሚያ ጡረታ የወጣ እና 50 ዓመት የሞላው መሥራት የማይችል የአካል ጉዳት ደረጃው 35% እና በላይ የሆነ በተወሰኑ መስፈርቶች የልዩ ጭማሪ መብት አለው።

**የሚከፈለው የድጐማ ገንዘብ መጠን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ተዘርዝሯል።**

## በጠላት ለተሰው ግለሰቦች ቤተሰብ የሚከፈል ድጐማ

### የጥገኞች ወራዊ ካሳ/ክፍያ

በጠላት እኩይ ተግባር ተጎድቶ ለተሰዋ ግለሰብ ባለቤት፣ ወላጆች እና ልጆች ይከፈላል። የሚከፈለው የክፍያ መጠን በአገልግሎት ላይ ለተሰው ወታደሮች ቤተሰቦች ከሚከፈለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

**በጠላት የተሰው ግለሰቦች ቤተሰብ ካሳ ጥያቄ አቀራረብ**

ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ በ12 ወራት መጨረሻ ላይ በልዩ ፎርም (581/לב) በሟቹ መኖሪያ ቤት አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።
የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

### የገንዘብ ያልሆኑ ካሳዎች እና ልዩ ልዩ እገዛዎች

ሕክምና፣ ሐኪም ቤት መተኛ፣ የመዳን ሂደት፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ሙያዊ ማገገሚያ እና እንደ መኖሪያ ቤት ብድር እና ስጦታዎች፣ ለመኪና ግዢ እና ለመኪናው ወርኀዊ ወጪ የሚደረግ እገዛ፣ ለግል አገልግሎቶች ወጪዎች እና ሌሎችም የመሳሰሉ ልዩ ልዩ እገዛዎች።

ሙያዊ ማገገሚያ እና ልዩ ልዩ እገዛዎች ለሟች ባለቤቶች፣ ወላጆች እና ልጆችም ይሰጣሉ።

ጥቅማጥቅሞቹን ለማግኘት በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ የማገገሚያ ክፍል ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል።

### ሙያዊ ማገገሚያ

በጠላት እኩይ ተግባር ተጎድቶ ቢያንስ 20% የአካል ጉዳት ደረጃ የተወሰነለት ተጎጂ እንደዚሁም በጠላት እኩይ ተግባር ተጎድቶ የተሰዋ ሰው ባለቤት እና ልጆች ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ሙያዊ ማገገሚያ መቀበል ይችላሉ።

**ለተጨማሪ ዝርዝሮች "ሙያዊ ማገገሚያ" በሚለው ሥር ተመልከቱ።**

# የሥራ ላይ ጉዳተኞች ዋስትና



**የሥራ ላይ ጉዳተኞች ዋስትና የታለመው ዋስትና የገባው ግለሰብ ጉዳቱ ከደረሰበት በኋላ ገቢ ባይኖረው ያንን ለማካካስና በሙያዊ ማገገሚያ አማካይነት ወደ ሥራ ቦታው እንዲመለስ ለመርዳት ነው።**

### ባለዋስትናው ማን ነው?

በተጎዳበት ጊዜ ቢቱዋህ ሌኡሚ የተመዘገበ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ። በሞያዊ ማገገሚያ ላይ ያለ፣ የሞያ ትምህርት ላይ ያለ፣ በተለማማጅ ሕግ ወይም በሥራ አገልግሎት ሕግ (በፈተናው ሰዓት ብቻ) መሠረት ይፈተናል፤ የሚሠራ እስረኛ፣ እስራኤላዊ አሠሪ ዘንድ እስራኤል ውስጥ የሚሠራ የውጪ ዜጋ፣ የእስራኤል ኗሪ ውጪ አገር-በተወሰነ መስፈርት፣ ደሞዙ በሕግ የሚወሰን (የፓርላማ አባል እና የመሳሰሉት)።

### የሥራ ላይ ጉዳት ዋስትና ባለመብት ማን ነው?

"በሥራ ላይ ጉዳት" የደረሰበት ባለዋስትና (አደጋ ወይም የሞያ በሽታ) እናም በሥራ ላይ ጉዳት የሞት ባለዋስትና ጥገኞች (ባልየሞተባት/ሚስት የሞተችበት፣ የሙት ልጆች፣ ወላጆች እና ሌሎች ቤተሰቦች – በተለዩ ምክንያቶች)

**የሥራ ላይ አደጋ** – በሥራ ላይ ሆኖ የሚደርስ አደጋ፣ ወደ ሥራ ሲኬድ እና ከሥራ ሲመለሱ የሚደርሱትን አደጋዎች ጨምሮ፤ በሕጉ ላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች።

**የሞያ በሽታ – በሥራው ምክንያት የታመመ ባለዋስትና፣ በሕጉ ላይ በተጠቀሱት በሽታዎች መካከል የሚገኝ ከሆነ።**

> የቢቱዋህ ሌኡሚ ክፍያ ያለበት የግል ሠራተኛ ባለመብትነቱ ይገፈፋል ወይም ዝቅተኛ ክፍያ ድጎማ ይከፈለዋል (በቀረበት ውዝፍ እና በተወዘፈበት የጊዜ ርዝመት አንጻር)።

## የሥራ ላይ ጉዳት ዋስትና ድጎማ

### የሕክምና እንክብካቤ

የማዳን ሂደት፣ በ"ኩፓት ሆሊሞች" አማካኝነት የሚሰጥ የሕክምና ማገገም እና መልሶ ማቋቋም።

### የጉዳት ክፍያ

ጉዳቱ ከደረሰበት ማግስት ጀምሮ ከሥራው በመቀቱ ምክንያት ለ91 ቀናት የሚከፈል ክፍያ ነው። የጉዳት ክፍያ የሚከፈለው በሥራ ላይ ለተጎዳ እና በሞያ በሽታ የታመመ ስለዚህ ሥራውን ወይም ሌላ ተስማሚ ሥራም መሥራት ያቃተው እና በተግባር ያልሠራ እንዲሁም የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልገው ከሆነ ነው።

- የመጀመሪያዎቹ የ12 ቀናት የጉዳት ክፍያዎች ለግል ሠራተኞች አይከፈሉም።
- ለተቀጣሪ ሠራተኛ – ለጉዳቱ ቀን ክፍያ አይከፈልም፣ ነገር ግን በአሠሪው ይከፈለዋል።

ከተጎዳበት ቀን በኋላ ያሉት ሁለት ቀናት የጉዳት ክፍያ የሚከፈልባቸው 12 ቀንና ከዚያ በላይ መሥራት ለማይችል ነው።

### የክፍያው መጠን በቀን

**ከጉዳቱ በፊት ያሉት የሦስት ወራት (የዋስትና ክፍያ ግዴታ ያለበት) 75% ደሞዝ ለ90 ተከፍሎ፣ እስከ ከፍተኛው የጉዳት ክፍያ (ጥር 2016 በቀን 1,094.63) ድረስ ነው።**

### የሥራ ላይ ጉዳት ዋስትና ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ

ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በ12 ወራት ውስጥ በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋህ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ በቅጽ 211/ל ב ማቅረብ ያስፈልጋል፣ ከ"ኩፖት ሆሊም" የሚሰጠውን የመጀመሪያ ጉዳት የሕክምና ማስረጃ ማያያዝ።
ቅጹን ከቢቱዋህ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

> **አዲስ!** ማመልከቻውን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ በመሙላት ከሁሉም ሰነዶች ጋር ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት "ኦንላይን" ላይ ሆኖ መላክ ይቻላል።

## የሥራ አካለ ጎደሎነት መደጎሚያ

### የሥራ አካለ ጎደሎነት ተቆራጭ

ቢያንስ ባለ 9% ደረጃ ጊዜያዊ የሥራ አካል ጉዳተኝነት እና ባለ 20% ቋሚ የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጩ በሕክምና አካል ጉዳተኝነት ደረጃ መሠረት ከጉዳቱ በፊት ባሉት የሦስት ወራት ደሞዝ አንጻር **በጥር 2016 ለተቀጣሪ ሠራተኛ እና ለግል ሠራተኛ ከፍተኛው ወርኀዊ ተቆራጭ – 32,839 ሼቄል ነው።**
የሥራ አካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ዝቅተኛ ገቢ ክፍያ ከሥራ ቦታ የሚከፈላቸው የገቢ ማሟያ ("ሃሽላማ") ይሰጣቸዋል።

### የሥራ አካል ጉዳተኝነት ክፍያ ጥያቄ አቀራረብ

በተቻለ ፍጥነት በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ በፎርም 200/ל ב ማቅረብ ያስፈልጋል። ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

የሥራ አካለ ጉዳተኝነት ክፍያ ጥያቄ ያቀረበ ወደ ሕክምና ኮሚቴ ይጠራል። ኮሚቴው አካለ ጎዶሎነቱ በሥራው ምክንያት መሆኑን ይወስናል፣ እንዲሁም የአካለ ጉዳተኝነቱን ደረጃ።

### የሥራ አካለ ጉዳተኝነት ስጦታ

**ባለ 9% ደረጃ እና ከዚያን በላይ ነገር ግን ከ20% ለሚያንስ ቋሚ የሥራ አካለ ጉዳተኝነት የወር ተቆራጩ ሲባዛ በ43 የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጣል። በ12 ወራት ዘግይቶ የቀረበ ጥያቄ ከመዘግየቱ አንጻር ተቀንሶ ይከፈላል።**

> የሚደርስህን የተቆራጭ ወይም የስጦታ መጠን ለማወቅ – በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረገጽ ላይ ወደሚገኘው **የሥራ ቦታ አካለ ስንኩልነት ማስሊያ** ግባ።

### ልዩ ተቆራጭ

የየቀኑን ተግባር ለማከናወን የሚቸገሩ የአካለ ጉዳተኝነት እና ባለከፍተኛ ቋሚ የአካል ጉዳተኝነት ደረጃ 75% ያላቸው፤ ወይም ከ65% – 74% ባለ ቋሚ የአካለ ጉዳተኝነት ደረጃ ያላቸው ለመራመድ/መሄድ የሚቸገሩ – በግል እንክብካቤ ለመርዳት እና ከአካለ ጉዳተኝነት የተነሳ ለሚፈጠሩ አንዳንድ ወጪዎች መሸፈኛ።

ልዩ እርዳታ በ4 የእርዳታ ደረጃዎች በሚያስፈልገው የእገዛ ዓይነት መሠረት ይወሰናል።
**በጥር 2016 ከፍተኛው ልዩ ተቆራጭ 8,210 ሼቄል ነው።**

ተቆራጩን ለማግኘት በፎርም (266/ל ב) ለማገገሚያ/ማቋቋሚያ ክፍል ማቅረብ፣ ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል። የጥያቄው ተቀባይነት ሂደት በሰው ላይ የመደገፉን ደረጃ ግምት ጨምሮ በጥያቄ አቅራቢው ክፍል ነርስ እንዲሁም በድርጅቱ ሐኪም ይወሰናል።

### ለአንድ ጊዜ ክወና የሚሆን ስጦታ

ለባለ 75% ደረጃ አካል ጉዳተኞች እና ከዚያን በላይ እናም ከ65% – 74% የአካለ ጉዳተኝነት ደረጃ ያላቸው እና ለመራመድ/መሄድ የሚቸገሩ በአካላቸው ጉዳት የተነሳ ለአንድ ጊዜ የእርዳታ ሽፋን፦ ተስማሚ ቤት ይፈለግላቸዋል፣ የአጋዥ ዕቃዎች ግዢ፣ የመዘዋወር ችግርን ለመፍታት መኪና ይገዛላቸዋል ("መዘዋወር/መሄድ ለማይችሉ ብቻ")።

**የስጦታው መጠን የሚወሰነው ድርጅቱ በፈቀደው ወጪዎች ድምር ላይ ተመርኩዞ ሲሆን ነገር ግን ከከፍተኛው መጠን አያልፍም።**

ተቆራጩን ለማግኘት በፎርም (282/7ב) ለማገገሚያ/ማቋቋሚያ ክፍል ማቅረብ፣ ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

## የገቢ ማሟያ

የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ወይም የጥገኝነት ("ትሉዪም") ተቆራጭ የሚቀበል እና ገቢው አነስተኛ ሆኖ የገቢዎችን ፈተና ያለፈ ለገቢ ማሟያ ክፍያ ባለመብት ነው።
የገቢ ማሟያ ተጨማሪ ክፍያ ጥያቄው ከቀረበብት ወር ጀምሮ ይከፈላል እና እንደዚሁ ተቆራጭ ተቀባዩ በሚያስፈልገው ጊዜ (የገቢ ማሟያው ያላግባብ ተከፍሎ ከሆነ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ከሚከፍለው ተቆራጭ ላይ የመመለስ መብት አለው)። የተነጠለ ጥያቄ ለገቢ ማሟያ ክፍል ማቅረብ ያስፈልጋል።

## ተረጂ የአካል ጉዳተኛ

ጊዜያዊ አካል ጉዳተኝነት ተወስኖለት ተመልሶ ማንኛውንም ሥራ መሥራት የማይችል እና ከሥራ ገቢ የሌለው የአካል ጉዳተኛ በ"ተረጂ የአካል ጉዳተኝነት" እንዲታወቅ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ለ"ተረጂ የአካል ጉዳተኛ" ለተወሰነለት ወቅት የ100% መጠን ተቆራጭ ይከፈለዋል።

> ጥያቄውን በፎርም 279/7ב ማቅረብ የሚቻል ሲሆን ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

## የሥራ አካለ ጉዳተኛ ሞያዊ ማገገሚያ

የሞያዊ አቅጣጫ ማመላከት እና ከሥራው ዓለም ለመቀላቀል የምርመራ እርዳታ፤ በትምህርት ሰዓት የማገገሚያ ክፍያ (ከሥራ ለሚከፈለው የአካል ጉዳተኛ ተቆራጭ ማሟያ)። የትምህርት ወጪዎችን መሸፈን እንደ መጓጓዣ፣ የትምህርት ክፍያ እና የትምህርት መሣሪያዎች የመሳሰሉትን።

### የሞያዊ ማገገሚያ መስፈርቶች

ሞያዊ ማገገሚያ የሚሰጠው በሥራ ላይ ጉዳት ቢያንስ 10% ቋሚ የአካል ጉዳት ደረጃ የተወሰነላቸው እና ሌላም ተለዋጭ ሥራ መሥራት የማይችሉ እነሱ ሞያዊ ማገገሚያ ያስፈልጋቸዋል ተገቢም ናቸው።

### የሞያዊ ማገገሚያ ጥያቄ አቀራረብ

ጥያቄውን በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ በፎርም (270/7ב) ለማገገሚያ ክፍል ማቅረብ ያስፈልጋል።
ጥያቄውን ፍጹም የአካል ጉዳት ደረጃ ከተወሰነ በአንድ ዓመት ውስጥ ማቅረብ ያስፈልጋል።
ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።
**ተጨማሪ ዝርዝሮችን "ሽኩም ሚቅጾዒ" በተሰኘው ክፍል ተመልከቱ።**

# በሥራ ጉዳት ምክንያት ለሞተ ሠራተኛ ቤተሰቦች የሚከፈል ድጐማ

**በሥራ ላይ ጉዳት ለሞተ የሟች ሚስት/ባል ይከፈላል።**

## የጥገኞች ተቆራጭ

ለጥገኞች ("ትሉይም") ስጦታ የማግኘት መብት ያላቸው፦ ባል የሞተባት ልጅ የሌላት እና 40 ዓመት ያልሞላት እራሷን ገቢ ማስገኘት የምትችል፣ እንዲሁም ሚስት የሞተችበት ልጅ የሌለው እና 40 ዓመት ያልሞላው እንዲሁም ለራሱ ገቢ ማስገኘት የሚችል (አጠቃላይ ገቢው በወር ከ5,394 ሼቄል በታች የሆነ)።
ለፍጹም አካል ጉዳተኛ ለባለዋስትናው ከሚደርሰው ተቆራጭ ከ40% እስከ 100% የተቆራጭ መጠን በልጆች ቁጥር መሠረት ይደርሰዋል።
የጥገኞች ተቆራጭ የሚያገኙና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማሟያ ክፍያ ይከፈላቸዋል።

### የጥገኞች ተቆራጭን ለማግኘት ማመልከት

ማመልከቻውን ሠራተኛው ከሞተ በኋላ በ12 ወራት ውስጥ በተሰኘ ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

## የጥገኞች ስጦታ

የአንድ ጊዜ ስጦታ መጠኑ 36 የወር ተቆራጮች ድምር ነው።
የስጦታ መብት ያለው የተቆራጭ መብት የለውም።
የጥገኞችን ("ትሉይም") ተቆራጭ የማግኘት መብት ያላቸው፦ ባል የሞተባት ልጅ ያላት እና 40 ዓመት የሞላት ወይም ለራሷ ገቢ ማስገኘት የማትችል፣ እንዲሁም ሚስት የሞተችበት ልጅ ያለው እና 40 ዓመት የሞላው ወይም ለራሱ ገቢ ማስገኘት የማይችል (አጠቃላይ ገቢው በወር ከ5394 ሼቄል በታች የሆነ)።

## የጋብቻ ስጦታ

ጋብቻ የመሠረተ የሟች ባል ወይም የመሠረተች የሟች ሚስት የ36 ወራት ተቆራጮች ድምር ስጦታ ይሰጣቸዋል። ስጦታው በሁለት ደረጃዎች ይከፈላል፣ አንዱ በጋብቻው ማግስት ሁለተኛው ደግሞ ጋብቻው ከተመሠረተ ከሁለት ዓመታት በኋላ ሲሆን (የጥገኞች ("ትሉይም") ተቆራጭ መብቱ ይቃጠላል/አይሠራም)።
ስጦታው ወዲያውኑ ስለሚከፈል ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልግም።

## የጥገኞችን ተቆራጭ የሚያገኝ ወይም የምታገኝ የሟች ባለቤት ሞያዊ ማገገም

የሞያዊ አቅጣጫ ለማመላከት የምርመራ እርዳታ የትምህርት ወጪዎችን መሸፈን እና በትምህርት ወቅት የመተዳደሪያ ወጪዎችን መሸፈን – ባለቤቱ/ቷ በሥራ ላይ አደጋ እንደሞተበት/ባት የሚታወቅ እና ሞያ የሌለው ወይም ለመተዳደሪያ በሞያ የማይጠቀም ከሆነ/ነች ወይም በባለቤቱ/ቷ ሞት ምክንያት የሞያ ለውጥ የሚያስፈልግ ከሆነ ለሞያዊ ማገገም ተስማሚ ነው።

ጥያቄውን በመኖሪያ አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት ቅርንጫፍ በፎርም (270/7ב) ለማገገሚያ ክፍል ማቅረብ ያስፈልጋል።
ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ እና በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።
**ተጨማሪ ዝርዝሮችን "ሽኩም ሚቅጾዒ" በተሰኘው ክፍል ተመልከቱ።**

## ወላጅ ለሞተባቸው ልጆች የመተዳደሪያ ወጪዎች ክፍያ ("ድሜይ ምሕያ")

አብዛኛው ሰዓቱ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ለሞያ ትምህርት የሚውል ልጅ በወላጁ ገቢ ምርመራ መሠረት። **በጥር 2016 የመተዳደሪያው መጠን በወር 788 ሼቄል ነው።**
ተቆራጩን ለሚቀበል ግለሰብ ቢቱዋሕ ሌኡሚ የተምህርት ዘመን ከመከፈቱ በፊት የመተዳደሪያ ወጪዎች ማመልከቻ ፎርም ይልካል። ፎርሙን በመሙላት ወደ ቅርንጫፉ መላክ ያስፈልጋል።

## የ"ባር ሚጽቫ" ስጦታ

ወላጅ የሞተበት የ13 ዓመት ወንድ ልጅ እና ወላጅ የሞተባት የ12 ዓመት ሴት ልጅ።
**የስጦታው መጠን በጥር 2016 መሠረት 5,838 ሼቄል ነው።**
ስጦታው የሚከፈለው ወዲያው ነው።

## የሞት ጊዜ ስጦታ

ደረጃው 50% እና ከዚያን በላይ የሥራ አካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ተቆራጭ የሚቀበል ወይም የተረጂዎች ("ትሉይም") ተቆራጭ ተቆራጭ የሚቀበል ሰው ቢሞት ለባለቤቱ ወይም ባለበት ከለለው ለልጁ (በሕጉ እንደተገለጸው) የአንድ ጊዜ ስጦታ ይሰጣል።
**የስጦታው መጠን በጥር 2016 መሠረት 8,757 ሼቄል ነው።**

ለቀሪዎቹ የተቆራጭ ተቀባዩ ቤተሰቦች የአካል ጉዳቱን ተቆራጭ 60% ሲባዛ በ36 የአንድ ጊዜ ክፍያ በተወሰኑ መስፈርቶች በቀደመው ተቆራጭ ፋንታ ይሰጣቸዋል።



# የአካለ ስንኩልነት ዋስትና



በአካለ ስንኩልነት ዋስትና ወርኀዊ ተቆራጭ ይከፈላል። የሚከፈለውም በአካለ ስንኩልነቱ ምክንያት ሠርቶ ደመወዝ የማግኘቱን ችሎታ ላጣ ወይም ሠርቶ ደመወዝ የማግኘቱ ችሎታ በጣም ለቀነሰ ግለሰብ ነው። በአካለ ስንኩልነት መዋቅር ለአከል ስንኩል ልጅም ድጎማ የሚከፈል ሲሆን ለልዩ አገልግሎቶች ደግሞ ተቆራጭ ይከፈላል።

## የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ

### የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ መብት ያለው ማን ነው?

"አካለ ስንኩል" – የእስራኤል ኗሪ የሆነ፣ የሆነች እና የቤት እመቤት ያልሆነች ከ18 እስከ ጡረታ ዕድሜ ድረስ (የእርጅናን ምእራፍ ተመልከቱ) በበሽታ፣ በአደጋ ወይም ከተወለዱ ጀምሮ በአካል፣ የጭንቅላት ወይም የአዕምሮ ችግር ኖሯቸው በዚያ ምክንያት ለመሥራት ችግር የሚሆንባቸው፡

- ከባድ ችግር ኖሮባቸው ወይም የተቆራጭ ቀጣይ መብት ያላቸው ከማዕከላዊው/መደበኛው ደሞዝ 60% በላይ የማይቀጠሩ **(ጥር 2016 ላይ 5,678 ሼቄል ነው)**
- ሌሎቹ በሙሉ – ከማዕከላዊው/መደበኛው ደሞዝ 45% በላይ የማይቀጠሩ **(ጥር 2016 ላይ 4,259 ሼቄል ነው)።**

> **ወጥቶ መሥራት በጣም ያዋጣል**
>
> የምትሠራ ብትሆንም መቀበል ትችላለህ። ተቆራጭህ በአነስተኛ መጠን የሚቀንስ ቢሆንም፣ ከሥራህና ከተቆራጩ የምታገኘው አጠቃላይ ገቢ ከተቆራጩ ብቻ ከምታገኘው ገቢ የበለጠ ነው።
>
> ተቆራጩንም እየተቀበልክ ምን ያህል ገንዘብ ከሥራህ ማግኘት እንደምትችል ማወቅ ትፈልጋለህ? በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ወዳለው **"የገቢ ማስሊያ"** ቦታ ግባ።

ለ"አካል ጉዳተኛ" አደጋው ሊደርስበት አካባቢ "ከ18 ዓመት በታች ሆኖ የሠራ" ሰው ያው ይታሰብለታል።

የቤት እመቤትም እንደ "አካል ጉዳተኛ" ልትታሰብ ትችላለች። ይኸውም ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ የነበረች፣ ተከታታይ 12 ወራት (24 ተከታታይ ያልሆኑ ወራት) የአካል ጉዳተኝነት ጥያቄውን ከማቅረቧ ቀድሞ ወይም ሥራ ከማቆሟ በፊት በነበሩት 48 ወራት፣ የተቆራጩን ጥያቄ ካቀረበች በኋላ ሥራዋን ያቆመች እንዲሁም ከባሏ ጋር የማትኖር የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ጥያቄውን ከማቅረቧ ቀድመው ያሉትን 24 ወራት አብራው ያልኖረች ወይም ከዚያን በኋላ ከ1.3.05 በኋላ አግብታ ከማግባቷ በፊት "እንደምታገኘው ደሞዝ" ተቀብላ ከሆነ።

"አካል ጉዳተኛ የእቤት እመቤት" – እስራኤል አገር ኗሪ ዕድሜ ከ18 – ጡረታ መውጫ ድረስ (የእርጅናን ምዕራፍ ተመልከቺ)፣ ባለትዳር እና የማትሠራ፣ ባለቤቷ በእርጅና እና በ"ሸአሪም" ዋስትና ያለው በጉዳቱ ምክንያት በመደበኛው የቤት እመቤትነት መተግበር ያልቻለች ወይም በጉዳቱ ምክንያት የቤት እመቤትነት ተግባሯ ከ50% በላይ የቀነሰ።

### የአካለ ጉዳተኛነት ተቆራጭ ባለመብትነት መስፈርቶች

1. የሕክምና የአካል ጉዳተኝነት – ቢያንስ በ60% ወይም ቢያንስ በ40% የተጠቃለለ የአካል ጉዳተኝነት ለባለዋስትናው የተወሰኑ የአካል አለመብቃቶች (ጉዳቶች) ኖረውበት በአንዱ ቢያንስ የ25% የሕክምና አካል ጉዳተኝነት የተወሰነለት። (ለአካል ጉዳተኛ የቤት እመቤት ቢያንስ 50%)።
2. ተቀጥሮ ለመሥራት ወይም በቤት ውሳጥ ለመሥራት አቅም ማጣት – ማጣት – ቢያንስ በ50% መጠን።

**የባለመብትነቱ መጀመሪያ –** ተቀጥሮ የመሥራት (ወይም በቤት ውስጥ የመሥራት) የአካል ደረጃው ብቁ አይደለም ከተባለ 90 ቀን በኋላ በእነዚህ 90 ቀናት ማብቂያ ውስጥ የሕክምና ክፍያ የሚከፈል ከሆነ
የአካል ደረጃው ብቁ አይደለም ተብሎ ከተወሰነ 30 ቀን በኋላ በተለዩ ሁኔታዎች ከ1.3.16 ጀምሮ ተቆራጭ መቀበል ይቻላል።
**የበሽታ ክፍያ የሚከፈልህ ከሆነ፣ ተቆራጩ የሚከፈልህ የበሽታ ክፍያ ተከፍል ሲያልቅ ነው።**

### የተቆራጩ መጠን በጥር 2016:

**አንድ ብቸኛ ሰው የሥራ አለመብቃቱ 100% ከሆነ 2,342 ሼቀል (ቀጥሎ ሙሉ የብቸኛ ተቆራጭ ተዘርዝሯል) በሥራ አለመብቃት ደረጃው አንጻር የሥራ አለመብቃት ደረጃው 60% – 74%፣ ወይም ከገቢው አንጻር።**

ለሥራ ያለመብቃት ደረጃቸው ቢያንስ በ75% ደረጃ የተወሰነላቸው የአጠቃላይ አካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ የሚቀበሉ እና የሕክምና አካል ጉዳተኝነት ቢያንስ 50% የተወሰነላቸው እንደ የሕክምና አካል ጉዳታቸው መጠን **ከ252 – 372 ሼቄል በተቆራጫቸው ላይ ጭማሪ አላቸው።**

የጥገኞች ጭማሪ – ከመደበኛ ወይም ከአማካይ ደሞዝ ከ57% የማይበልጥ ገቢ ያለው ወይም ያላት ባለቤት (በጥር 2014 መሠረት በወር 5181 ሼቄል) **ለአካል ጉዳተኛው ከሚከፈለው 50%** (የቤት እመቤት ለባለቤቷ ጭማሪ የማግኘት መብት የላትም) ፦
ለልጅ (ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ልጆች ለእያንዳንዱ)
**ለአካል ጉዳተኛው ወይም የአካል ጉዳተኛ ለሆነች የቤት እመቤት ከሚከፈለው ወርኀዊ ተቆራጭ 40%።** የጥገኞች ጭማሪ የሚሰጠው በገቢ ምርመራ መሠረት ነው።

### የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ጥያቄ አቀራረብ

የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ጥያቄውን በጥያቄ አቅራቢው መኖሪያ ቤት አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ በፎርም 7801/ב ማቅረብ ያስፈልጋል፣ ካልሆነ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ። የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል። ሁሉንም አስፈላጊ ማስረጃዎች ከመጠየቂያው ፎርም ጋር ማያያዙን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

> **አዲስ!** ማመልከቻውን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ በመሙላት ከሁሉም ሰነዶች ጋር ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት "ኦንላይን" ላይ ሆኖ መላክ ይቻላል።

የተቆራጩን ጥያቄ የአካል ጉዳተኛው እራሱ ማቅረብ አለበት። ምናልባት በአካሉ አለመብቃት ወይም በአዕምሮ ችግር ካልቻለ ቤተሰቦቹ ወይም ሌላ የሚወክለው ሰው በስሙ የማቅረብ መብት አላቸው።

የተቆራጩን ጥያቄ ጥያቄው ከተነሳ በ12 ወራት ውስጥ ማቅረብ ያስፈልጋል። የተቆራጩን ጥያቄ ዘግይቶ ማቅረብ ለተቆራጭ ያለውን መብት ሊጎዳ ይችላል።

ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና ተቆራጩን በከፊል የሚያገኝ ሰው ይግባኝ የማለት/ዳግመኛ የመጠየቅ መብት አላቸው፣ በእርግጥ በሕጉ እና በድንጋጌው መስፈርት መሠረት እንደገና ይታይልን የሚለውን ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው።

> **የዋስትናን ክፍያ ከመክፈል ነጻ መሆን**
>
> - የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ የሚከፈለው እና ሌላ ምንም ዓይነት ገቢ የሌለው ተቆራጩ በሚከፈለው ጊዜ ከዋስትና ክፍያ ነጻ ነው።
> - የሥራ አለመብቃት ደረጃው 100% እና ከዚያን በላይ ለአንድ ዓመት ወይም በቋሚነት የተወሰነለት የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ የሚከፈለው ሰው ተቆራጩ በሚከፈለው ጊዜ ሌላ ተጨማሪ ገቢ ቢኖረውም ከዋስትና ክፍያ ነጻ ነው። ነገር ግን የግል ሠራተኛ ከሆነ የዋስትናውን ክፍያ ለሥራ ጉዳተኞች ዘርፍ ይከፍላል፣ ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆነ ግን ዋስትናውን አሠሪው ለሥራ ጉዳተኞች ዘርፍ እና ለከሰሩ ሠራተኞች እና ለፈረሰ ማህበር ሠራተኞች መብት ዘርፍ ይከፍላል።

## ሞያዊ ማገገሚያ

ቢያንስ የ20% የሕክምና የአካል ጉዳተኝነት ደረጃ የተወሰነለት እና በደረሰበት ችግር ምክንያት ሥራውን መሥራት የማይችል እና ሌላ ተስማሚ ሥራም መሥራት የማይችል ከሆነ እንዲሁም ሞያዊ ማገገም የሚያስፈልገውና ተገቢው ከሆነ፣ በምርመራ/በመለየት ሂደት እርዳታ፣ ሞያዊ የሆነ አቅጣጫ ማስያዝ እና በሥራ ማዋሃድ፣ (በሞያ ትምህርት ጊዜ የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ለማይከፈለው እና በከፊል የሚከፈለው) እንደዚሁም የትምህርት ክፍያ ይከፈልለታል፣ የትምህርት ቁሳቁስ ወጪ እና ወደትምህርቱ መሄጃ እና መመለሻ መጓጓዣ ይሸፈንለታል።

ለማገገሚያው ባለመብት መሆንህን ለመመርመር በመኖሪያ አካባቢህ ወደሚገኝ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ የማገገሚያ ክፍል አመልክት።

**ተጨማሪ ዝርዝሮችን "ሸኩም ሚቅጾዒ" በሚለው ክፍል ሥር ተመልከቱ።**

## ለልዩ አገልግሎቶች የሚከፈል ተቆራጭ

ለልዩ አገልግሎቶች የሚከፈለው ተቆራጭ ባለመብት የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት እስከ ጡረታ ዕድሜ ክልል ያሉ ወንዶችና ሴቶች ሆነው በዕለት ተዕለት የቤት ውስጥ ተግባራቸው በሌላ ሰው ላይ ጥገኛ ለሆኑት (ልብስ መልበስ፣ መመገብ፣ መታጠብ፣ መመገብ፣ የቤት ውስጥ ዝውውር እና የግል ንጽሕና) ወይም በራሳቸው ላይ የሕይወት አደጋ እንዳይደርስ ወይም በዙሪያው ባሉት ላይ እንዳያደርሱ ለመከላከል ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ነው።

እንደዚሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ልዩ ተቆራጭ ሊከፈል ይችላል። ለምሳሌ "ዲያሊዛ" ለሚደረግላቸው፣ "የኬሞቴራፒያ" ሕክምና ለሚያገኙና ንቅለ-ተከላ ለተደረገላቸው። በተጨማሪም ሐኪም ቤት ውስጥ ተኝቶ በመሣሪያ ኃይል ለሚተነፍስ መጠኑ ከፍ ያለ ተቆራጭ ይከፈላል።

**የተቆራጩ መጠን የሚወሰነው በ3 የጥገኝነት ደረጃዎች ላይ ተመርኩዞ ነው፡ 50%፣ 112% እና 188%። በተወሰነው የባለመብትነት መቶኛ ላይ ተመርኩዞ፣ የተቆራጩ መጠን በወር ከ1401 ሼቄል እስከ 5045 ሼቄል ድረስ ነው (ጥር 2016)።**

"በመሣሪያ ኃይል የሚተነፍስ አካለ ስንኩል" በተቆራጩ ላይ ተጨማሪ **1817 ሼቄል** ለመቀበል ባለመብት ነው (ከሚያዚያ 2015 ጀምሮ)።

### የተለዩ አገልግሎቶች ተቆራጭ መብት መስፈርቶች

- በእንክብካቤ ድርጅት ውስጥ ተኝቶ የማይታከም።
- በእስራኤል ውስጥ ያለ። በተወሰኑ መስፈርቶች በውጪ አገር ላለ አካል ጉዳተኛም ተቆራጩ ለተወሰነ ወቅት ይከፈለዋል።
- የሕክምና አካል ጉዳተንነት (ለተለዩ አገልግሎቶች) ቢያንስ በ60% ደረጃ ተወስኖለት ተቆራጭ የሚከፈለው።
  ወይም የሕክምና አካል ጉዳተንነት (ለተለዩ አገልግሎቶች) ቢያንስ በ75% ደረጃ ተወስኖለት ተቆራጭ የማይከፈለው፣ ከሥራ የሚያገኘው ገቢ በድንጋጌው መሠረት ከተቆራጩ መጠን የማይበልጥ ከሆነ እና በሆነ ሕግ መሠረት ለግል እንክብካቤ ለቤት ውስጥ እርዳታ የማያገኝ ከሆነ።
- የዝውውር/የእንቅስቃሴ ክፍያ የማይከፈለው ከሆነ ነገር ግን በሕክምና የእንቅስቃሴ ውሱንነት 100% ካልተወሰነለት በስተቀር፣ ወይም መንቀሳቀሻ ወንበር ተወስኖለት እየተጠቀመበት ያለ ወይም የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ባለመኪና የሆነ ቢያንስ የ100% ደረጃ የተለዩ አገልግሎቶች የተወሰነለት።

### ለልዩ አገልግሎቶች ተቆራጭ ጥያቄ አቀራረብ

የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጭ ጥያቄውን በጥያቄ አቅራቢው መኖሪያ ቤት አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ (በፎርም 7849/לב) ማቅረብ ያስፈልጋል። ከማመልከቻው ጋር ሁሉንም የሕክምና ማስረጃዎች እና ሌሎች ግንኙነት ያላቸውን ማስረጃዎች ማያያዝ ያስፈልጋል። ቢበዛ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት ያሉትን 6 ወራት ውዝፍ ማግኘት ይቻላል።

> ❯ **አዲስ!** ማመልከቻውን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ሞልቶ ሁሉንም ማስረጃዎች "ኦንላይን" ሆኖ መላክ ይቻላል።

### ለአዲስ ገቢ ከባድ የአካል ጉዳተኖች የሚሰጥ የተለየ ክፍያ – "ዓልያ" ባደረጉበት የመጀመሪያ ዓመት ላይ

ከ18 ዓመት እስከ ጡረታ መውጫ ዕድሜ ያሉ ከባድ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው አዲስ ገቢዎች (የእርጅናን መዕራፍ ተመልከት) ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ከ90 ቀናት በኋላ ዓመት እስከሚሞላቸው ድረስ በተወሰኑ መስፈርቶች የልዩ ክፍያ መብት አላቸው። ክፍያው ከ91ኛው ቀን ጀምሮ ከሚከፈል ልዩ ክፍያ እና ከ181ኛው ቀን ጀምሮ ከሚከፈል የአካል ጉዳተኝነት የተዋቀረ ነው። ዝርዝሩን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ማግኘት ይቻላል።

## በሞት ጊዜ የሚሰጥ ክፍያ

ለባለቤት የሚከፈል የአንድ ጊዜ ክፍያ፣ ባለቤት ከሌለ የአካል ጉዳተኝነት ተቆራጩ ለተከፈለው ሟች ልጅ (በሕግ እንደተገለጸው)። አንድ ልጅ የአካለ ስንኩል ልጅ ድጎማ የሚከፈለው ቢሆንና በሞት ቢለይ ከ1.4.16 ጀምሮ በሞት ጊዜ የሚሰጥ ክፍያ ለወላጆቹ ይከፈላል።

**የክፍያው መጠን በጥር 2016 ዓ.ም. 8,757 ሼቄል ነው።**

## የአካለ ስንኩል ልጅ ድጎማ

የሚከፈለው ለወላጅ ነው። ምክንያቱም የሕክምና ችግር ያለበትን አካል ስንኩል ልጅ ማሳደግ ብዙ የመንከባከብ ጫና ስላለበት ነው። የድጎማው ፐርሰንት 3 ደረጃዎች አሉት፡ 50%፣ 100% እና 188% ባለው የጤና ችግር ዓይነት ወይም በሌላ ሰው ላይ ባለው የጥገኝነት ደረጃ።

**የድጎማው መጠን በወር ከ1,095 ሼቄል እስከ 4,487 ሼቄል ድረስ ነው (ጥር 2016)።**

"በመሣሪያ እየታገዘ የሚተነፍስ ልጅ" ለድጎማው **የ1,817 ሼቄል ጭማሪ** ይቀበላል (ከሚያዚያ 2015 ጀምሮ)።

ከአንድ በላይ አካለ ስንኩል ልጅ ድጎማ የሚቀበልበት ቤተሰብ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ ከፍተኛ ፐርሰንት ላለው ተቆራጭ ባለመብት ናቸው።

### ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ክፍያ መብት ያለው ማን ነው?

- የእድገት ማዝገም ከባድ ችግር ያለበት 3 ዓመት ያልሞላው ልጅ (ከ91 ቀናት ጀምሮ)።
- ከ3 ዓመት እስከ 18 ዓመት ያለ የዕለት ተዕለት ተግባሩን ለመፈጸም በዕድሜው ካሉ ይልቅ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ በሌላ ሰው እርዳታ ላይ ጥገኛ የሆነ (ለቤት ውስጥ ዝውውር፣ ልብስ መልበስ፣ መታጠብ፣ መመገብ እና የግል ንጽህና፣ ወዘተ.)
- እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያለ ልጅ በራሱ ላይ የሕይወት አደጋ እንዳይደርስ ወይም በዙሪያው ባሉት ላይ እንዳይደርስ ለመከላከል ጥበቃ የሚያስፈልገው (ከ91 ቀን ጀምሮ)።
- ከሚከተሉት በሽታዎች ውስጥ በአንዱ ተጠቂ የሆነ እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያለ ልጅ፦ የአዕምሮ ዘገምተኛ (ከተወለደ ጀምሮ "ቲስሞኔት ዳዎን" ካለበት)፣ በእያንዳንዱ ጆሮ ከ40 ዴሲቤል በታች የመስማት ችሎታ የወረደ (ከተወለደ ጀምሮ)፣ በእያንዳንዱ ዓይን የማየት ችሎታ ከ6/60 በታች፣ የእይታ ፊልዱ ("ስዴ ርዕያ") ከ20° በታች የወረደ ሁሉም በመስተካከል (ከ91 ቀን ጀምሮ)፣ "ኦቲዝም"፣"ሳይኮሲስ"/"ፕሲኮዛ"፣ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የ"ሳይካትሪክ-ባህሪ" (ከ91 ቀን ጀምሮ)፣ (ከ3 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ) በመግባባት ዕርዳታ የሚያስፈልገው።
- በእስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያለ ልጅ በመመሪያው በተዘረዘረው መሠረት የተለየ የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልገው (ከ91 ቀን ጀምሮ)።

### የክፍያው መብት መስፈርቶች

እስራኤል ውስጥ ያለ ልጅ (በተወሰኑ መስፈርቶች እስራኤል ውስጥም ባይኖር) በድርጅት ውስጥ በአዳሪነት ያልተያዘ ወይም በማደጎ ቤተሰብ ያልተያዘ፣ የመዘዋወሪያ/መንቀሳቀሻ ክፍያ የማይቀበል ነገር ግን የእንቅስቃሴ ውሱንኑነት ደረጃው ከ80% በላይ ተወስኖለት ካልሆነ በስተቀር ወይም ተሽከርካሪ ወንበር የሚያስፈልገው ከሆነና እየተጠቀመ ከሆነ ወይም ደግሞ ለወላጆቹ ተጨማሪ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ካላቸው።

በድርጅት ተይዞ ያለ ልጅ ወላጆቹ ሁሉን በድርጅቱ ውስጥ ለልጁ የሚያስፈልገውን ወጪውን የሚችሉ ከሆነ የክፍያ መብት አለው።

### ለክፍያው ጥያቄ አቀራረብ

የክፍያውን ጥያቄ የሚያቀርበው ልጁ አብሮት ያለው ወላጅ ነው። ልጁ ከወላጆቹ ጋር ከሌለ የልጁ ሞግዚት ("አፖትሮፑስ") ወይም ልጁ አብሮት ያለው/የሚይዘው ሰው የክፍያውን ጥያቄ ያቀርባል። ጥያቄውን በተገቢው በፎርም 7821/לב በልጁ መኖሪያ ቤት አካባቢ ላለ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል። የመጠየቂያውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል። ሁሉንም የሕክምና ማስረጃዎችን እና የትምህርቱን ማስረጃ፣ "የእድገቱን ሂደት እንክብካቤ" የሚያሳየውን ማስረጃ በመመሪያው መሠረት ከሚመለከተው አካል ወስዶ ከመጠየቂያው ፎርም ጋር ማያያዝ ያስፈልጋል።

> ❯ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ክፍያ ውዝፉም የሚከፈል ሲሆን ቢበዛ እስከ ዓመት ድረስ ያለው ውዝፍ ነው የሚከፈለው – ሁሉም በመመሪያው መሠረት ነው።

## በ"ሪንግ ዎርም" ("ጋዜዜት") ለተጎዱ የሚሰጥ ካሳ

በ"ሪንግ ዎርም" ("ጋዜዜት") ለተጎዱ በሚሰጠው ካሳ ሕግ መሠረት ከጥር 1995 ጀምሮ በጸረ "ሪንግ ዎርም" የጨረራ ሕክምና የተጎዱ የካሳ መብት አላቸው (ወይም ቀሪዎቹ) ከ1.1.46 እስከ 31.12.60 ድረስ በሕግ በታወቀው አካል የተደረጉ።

በሕጉ በተዘረዘረው አንዱ በሽታ የታመመ እንደጉዳተኛ ይቆጠራል፣ እንደ በራስ ወይም የአንገት አካባቢ ካንሰር ("ሳርታን")፣ የደም ካንሰር እና ሌሎችም።

ጥያቄው በመኖሪያ አካባቢ ላለ የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይቀርባል። የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት ነው ባለመብትነቱን የሚወስነውና እንደዚሁም ለጥያቄ አቅራቢው ጥያቄው ተቀባይነት እንዳገኘና እንዳላገኘ የሚነግረው። ክፍያው የሚሰጠው በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት አማካይነት ነው።

## በደም መቀበል ለተጎዱ የሚሰጥ ካሳ

በደም መቀበል ለተጎዱ ("ኤድስ") በሚሰጥ ካሳ ሕግ መሠረት፣ ከ31.12.81 ጀምሮ እስከ 1.1.87 ድረስ በሕዝብ የሕክምና አገልግሎት በደም መቀበልም ሆነ በመስጠት ምክንያት በደማቸው ውስጥ የኤድስን ቫይረስ ተሸካሚ የሆኑ ካሳውን የማግኘት መብት አላቸው።

ከበሽተኛው ጋር በተደረገ ንክኪ ምክንያት የቫይረሱ ተሸካሚ ከሆኑ ሕጉ ለትዳር ባልደረቦችም ሆነ ለልጆች ይሠራል።

> ❯ የክፍያውን ባለመብትነት የሚወስነው የጤና ጥበቃ ባለሞያዎች ኮሚቴ ነው። ክፍያው የሚሰጠው በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት አማካይነት ነው።

## በፖልዮ በሽታ ለተጎዱ የሚሰጥ ካሳ

በፖልዮ ለተጎዱ በሚሰጠው ካሳ ሕግ መሠረት የአንድ ጊዜ ካሳ እና የወር ተቆራጭ ወይም (ስጦታ በተቆራጩ ፋንታ) የእስራኤል አገር ኗሪ ለሆኑ እና በእስራኤል ውስጥ በልጅነት ልምሻ ለታመሙ። ካሳውን ለማግኘት ጥያቄ ለማቅረብ በተዘጋጀው ፎርም 7870/לב ላይ ሞልቶ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል፣ ፎርሙን ከድርጅቱ ቅርንጫፍ መውሰድ ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ" የኢንተርኔት ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል።



# የመንቀሳቀሻ ድጎማ

የመንቀሳቀሻ ድጎማ (“ጊምላት ናያዱት”) የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች የሚያስገኝ ሲሆን የሚሰጠውም እግራቸው ላይ ችግር ላለባቸውና ይህም እንቅስቃሴያቸውን ለሚገድባቸው ነው።
ይህም የሚደረገው በኅብረተሰቡ ውስጥ ተዋኅደው እንዲኖሩ ለመርዳትና የራሳቸውን ነጻ ሕይወት እንዲያጐለብቱ ነው። ተቆራጩ የሚከፈለው ከገንዘብ ሚኒስቴር በጀት ላይ ሲሆን ገንዘብ ሚኒስቴርና ቢቱዋሕ ሌኡሚ በፈረሙት የመንቀሳቀሻ (“ናያዱት”) ውል መሠረት ነው።

### የእንቅስቃሴው የተገደብ የሚባለ ማን ነው? የመንቀሳቀሻ ("ናያዱት") ክፍያ ("ጊምላ") ባለመብትስ ማን ነው?

"እንቅስቃሴው የተገደበ" – የእስራኤል ኗሪ ከ3 ዓመት እስከ ጡረታ ዕድሜ ያለ እና እስራኤል ውስጥ የሚገኝ፣ በተጻፈው የችግር ዝርዝር መሠረት፣ በእግሩ ችግር ምክንያት የእንቅስቃሴውን ገደብ ምን ያህል ፐርሰንት እንደሆነ የጤና ጥበቃ ኮሚቴ የወሰነለት። በተወሰኑ መስፈርቶች ክፍያው ከጡረታ ዕድሜ በኋላም ይቀጥላል።

> በእንቅስቃሴ መገደብ ችግር እንዳለ የሚወስነው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕክምና ኮሚቴ ሲሆን ስለሆነም የመንቀሳቀሻ ("ናያዱት") ጥቅማጥቅም ለማግኘት ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ማመልከቻ ከማስገባታችሁ በፊት መጀመሪያ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕክምና ኮሚቴ ጉዳዩን እንዲመረምረው ማመልከት አለባችሁ።

## በመንቀሳቀሻ ድጎማ ሥር የሚሰጡ የጥቅማጥቅም ዓይነቶች

## የመንቀሳቀሻ ተቆራጭ

በእንቅስቃሴው ለተገደበ ሰው ለመንቀሳቀሻው ወርኀዊ ተቆራጭ ይከፈለዋል። ተቆራጩ እንደ መኪናው ወቅታዊ ወጪ ይሻሻላል።

### ባለመኪና የሆነ ሰው ለተቆራጩ መብት ይኖረው ዘንድ የሚያደርጉ መስፈርቶች

"እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው ለራሱ መኪና ወይም ለሚጠቀምበት መኪና የመንቀሳቀሻ ተቆራጭ የማግኘት መብት እና ብድር የማግኘትም መብት አለው።

ለተቆራጩ ጭማሬ መብት ያለው (በጥር 2016 መሠረት ገቢው ከ2,189 ሼቄል የሚበልጥ) እና የሥራው ቦታ ቢያንስ በሁለቱም አቅጣጫ 40 ኪ.ሜ. ርቀት ያለው፣ እና ወደሥራው ለመሄድ በቋሚነት በመኪናው የሚጠቀም።

### መኪና የሌለው ሰው ለተቆራጩ መብት ይኖረው ዘንድ የሚያደርጉ መስፈርቶች

"እንቅስቃሴው የተገደበ" መኪና የሌለው ሰው ለተቆራጩ ጭማሬ መብት ያለው (በጥር 2016 መሠረት ገቢው ከ2189 ሼቄል የሚበልጥ ከሆነ) ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነና የእንቅስቃሴው ገደብ ቢያንስ 80% ተወስኖለት ከሆነ እና የባለመኪናን ተቆራጭ የማያገኝ እንዲሁም የአጠቃላይ አካለ ጉዳተኝነትን ተቆራጭ የማያገኝ ከሆነ።

"ተቀጣሪ" ያልሆኑ መኪና የሌላቸው፦ ለተለዩ አገልግሎቶች ተቆራጭ የሚያገኙ* ወይም ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ የሚያገኙ** ወይም በድርጅት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና ቀጥሎ በየአንጻሩ የተዘረዘረውን መስፈርት የሚያሟሉ ብቻ።

### ለተለዩ አገልግሎቶች ተቆራጭ የሚያገኝ

አንድ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ "እንቅስቃሴው ለተገደበ" መኪና የሌለው ሰው ተቆራጭ መብት አለው፦

1. 18 ዓመት ከሞላው፣
2. የእንቅስቃሴው ገደብ 100% ተወስኖለት ከሆነ ወይም የሕክምና ኮሚቴ ተሽከርካሪ ወንበር እንደሚያስፈልገው ወስኖለት ከሆነና እየተጠቀመበት ከሆነ።

### ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ የሚያገኝ

የእንቅስቃሴው ገደብ ቢያንስ 80% ተወስኖለት ከሆነ ወይም የሕክምና ኮሚቴ ተሽከርካሪ ወንበር እንደሚያስፈልገው ወስኖለት ከሆነና እየተጠቀመበት ከሆነ።

### በድርጅት ውስጥ የሚኖር

አንድ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ "እንቅስቃሴው ለተገደበ" መኪና የሌለው ሰው ተቆራጭ መብት አለው፦

1. የእንቅስቃሴው ገደብ 100% ተወስኖለት ከሆነ (ለልጅ – ቢያንስ 80%) ወይም ተሽከርካሪ ወንበር የሚያስፈልገው ከሆነና እየተጠቀመበት ከሆነ።
2. ለተለዩ አገልግሎቶች ተቆራጭ የማያገኝ ወይም በድርጅት ውስጥ በመኖሩ ምክንያት ብቻ ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ የማያገኝ።
3. ቢያንስ በወር 6 ጊዜ ከድርጅቱ አካባቢ በመኪና የሚወጣ ከሆነ።
4. ከድርጅቱ የሚወጣበትን ወጪ የትኛውም የሕዝብ ድርጅት የማይሸፍን ከሆነ።

## በመኪና ግዢ ምክንያት ያልተከፈለ ዕዳ ("ሃልቫአ ኦሜዴት")

ይህ ብድር የሚሰጠው በስምምነቱ መሠረት ለመኪናው የሚወጡትን ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመሸፈን ነው። ያልተከፈለ ዕዳን በስምምነቱ ትዕዛዛት መሠረት መመለስ ነው።የብድሩ መጠን በእንቅስቃሴው ገደብ ፐርሰንት አንጻር ነው። የመንገድ ደህንነት ተቋም ("ማኾን") "እንቅስቃሴው የተገደበው" ሰው በስምምኑቱ መሠረት ከተፈቀደለት መኪና የበለጠ ትልቅ መኪና ያስፈልገዋል ብሎ በሚወስንበት ሁኔታ ለመኪና መግዣ የሚሰጠው ብድር በተቋሙ ውሳኔ መሠረት ይሰጠዋል። ያልተከፈለ ዕዳው ፐርሰንት የሚወሰነው በእንቅስቃሴው ገደብ ፐርሰንት አንጻር እንደዚሁም የእንቅስቃሴ ገደብ ያለበት ሰው መንጃ ፈቃድ ካለው ወይም ከሌለው ነው። የብድሮቹ መጠን በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ቀርቧል።

### ያልተከፈለ ዕዳ ላለው መብት እንዲኖር የሚያደርጉ መስፈርቶች

1. "እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው መንጃ ፈቃድ ያለው ሆኖ ቢያንስ 40% የእንቅስቃሴ ገደብ ተወስኖለት ከሆነ።
2. እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው መንጃ ፈቃድ የሌለው ሆኖ ቢያንስ 60% የእንቅስቃሴ ገደብ ተወስኖለት ከሆነ እንደዚሁም “የመንዳት ፈቃድ” ያለው አብሮት በአንድ ሕንጻ ውስጥ የሚኖር ወይም አጠገቡ ባለ ሕንጻ ውስጥ የሚኖር ሆኖ እንቅስቃሴው በተገደበው ሰው እና በሾፌሩ በሚኖሩበት ሕንጻዎች መካከል ያለው ርቀት ከ1500 ሜትር የማይበልጥ ወይም ርቀቱ የበለጠ ሆኖ በሰፈሩ ውስጥ ቅርበት ባላቸው ሕንጻዎች ውስጥ የሚኖር ከሆነ።

### “የመንዳት ፈቃድ ያለው”

የቅርብ ዘመድ ወይም ተንከባካቢ ሆኖ በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ነው።

1. “የቅርብ ዘመድ” ከእነዚህ አንዱ ነው፡- ባል/ሚስት፣ ልጅና የልጅ ባል/ሚስት፣ አባት፣ እናት – የእንጀራ አባትና እናት እንደዝዚሁም በጉዲፈቻ የሚያሳድጉትን ጨምሮ፣ ወንድም፣ እኅት፣ እሚታ፣ የልጅ ልጅ። ከእነዚህ አንዱ የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ከሆነና የሚኖረውም ከላይ ከተጠቀሱት ቢያንስ ከአንዱ ጋር በአንድ ሕንጻ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ወይም በሱ መኖሪያና በሌሎቹ መኖሪያ መካከል ያለው ርቀት ከ1500 ሜትር የማይበልጥ ከሆነ ወይም አንዱ ከሌላው ጋር በአንድ መንደር (“ይሹቭ”) ውስጥ በተቀራረቡ ሕንጻዎች ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ።
2. “ተንከባካቢ” (“መታፕል”) የሚባለው የቅርብ ዘመድ ያልሆነ ነው። ነገር ግን የቢቱዋሕ ሌኡሚ ማገገሚያ ባለሙያ "እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው የቅርብ ዘመዱም ቢሆን በአብዛኛዎቹ የቀን ሰዓታት ውስጥ እንዲረዳው ሊወስን ይችላል። ተንከባካቢውና እንክብካቤ የሚደረግለት ሰው በአንድ ሕንጻ የሚኖሩ ወይም የተለያዩ ሕንጻዎች ሆነው በሕንጻዎቹ መካከል ያለው ርቀት “የቅርብ ዘመድ” ተብሎ በተደነገገው ውስጥ ያለውን ርቀት የማይበልጥ ከሆነ ነው።

ያልተከፈለውን ዕዳ በእንቅስቃሴ ውል ውስጥ ባሉት መመሪያዎች መሠረት መመለስ ያስፈልጋል።

## መኪና እና የተለዩ የመኪና ቁሳቁሶችን ለመግዛት የሚሰጥ ብድር

### (ይህም ቀረጥ ለመክፈል ከሚጠቅመው ያልተከፈለ ዕዳ በተጨማሪ ነው)

ልዩ መሣሪያዎች የተገጠሙበት ተሽከርካሪ የሚባለው በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆኖ ወደ ውስጡ ሊገባበት የሚችል ተሽከርካሪ ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆነው እያሉ ሊነዱት የሚችሉት ተሽከርካሪ ነው።

- የመጀመሪያውን መኪናውን ለሚገዛ – ከአዲስ መኪና ዋጋ 80% (ያለቀረጥ). ወይም ያለቀረጥ ወይም ቀረጥ-አልባ ከሆነው የመኪናው ዋጋ ከሁለቱ መካከል በርካሹ መሠረት።
- መኪናውን ለሚቀይር – በነበረው መኪና እና በሚገዛው መኪና መካከል ባለው ልዩነት ቀረጥ-አልባ መጠን ለሚገዛ፣ ወይም አዲሱ መኪና ቀረጥ-አልባ ከሆነ ከሁለቱ መካከል በርካሹ መሠረት፣ ያለቀረጥ ከተገዛው የመኪናው ዋጋ 80% እስከ ከፍተኛው መጠን ድረስ – ከሁለቱ መካከል ርካሹን።

እንቅስቃሴው የተገደበ ሰው
መኪና በሚቀየርበት በማንኛውም ወቅት ብድሩ የሚሰጥ ሲሆን በእንቅስቃሴ ውል መሠረት ባለው ባለመብትነት ላይ ተመርኩዞ ነው።

### የባለመብትነት መስፈርቶች

- የሕክምና ኮሚቴው ወይም የሕክምና ይግባኝ ኮሚቴ የእንቅስቃሴ እክል ያለበት ሰው ተሽከርካሪ ወንበር ያስፈልገዋል ብሎ ወስኖ ከሆነና ግለሰቡም ወንበሩን እየተጠቀመበት ከሆነ።
- የመንገድ ደኅንነት ሕክምና ተቋም ልዩ መሣሪያዎች የተገጠሙበት ተሽከርካሪ ያስፈልገዋል ብሎ ከወሰነ።
- የእንቅስቃሴ ችግር ያለበት ሰው የግዴታ ውል ፈርሞ ከሆነና በውሉም መሠረት ለሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች ቃል ከገባ፡-
  - በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆኖ ወደ ውስጡ ሊገባበት የሚችል ተሽከርካሪ መግዛት ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሆነው እያሉ ሊነዱት የሚችሉትን ተሽከርካሪ መግዛት።
  - የመንገድ ደኅንነት ሕክምና ተቋም ጥሩ ናቸው ብሎ የወሰናቸውን ልዩ መሣሪያዎች በተሽከርካሪው ላይ መግጠም።

ብድሩ የሚሰጠው የመንጃ ፈቃድ ላላቸውና ለሌላቸው ሲሆን 5 ዓመት ሲያልቅ ብድሩ ወደ ስጦታ ይለወጣል። ይህም ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ብድሩ አስቀድሞ እንዲመለስ ካልወሰነ ነው።

> ❯ በሕጉ መሠረት ወይም በሌላ ውል ተሽከርካሪውን ያለቀረጥ ለመግዛት መብት ያለው (ልዩ መሣሪያዎች የተገጠሙበት ተሽከርካሪ ወይም የግል ተሽከርካሪ) በሕጉ መሠረት ወይም ልዩ በሆነው ስምምነት እንደሚቀበል ለመምረጥ መብት አለው።

### ልዩ መሣሪያዎች ለተገጠሙበት ተሽከርካሪ የሚሆኑ ልዩ መሣሪያዎችን ለመግዛት የሚያገለግል ብድር

ልዩ መሣሪያዎቹን ለመግዛት የሚሆን ብድር የሚሰጠው ከሚከተሉት ውስጥ አነስተኛውን ነው፡

1. ልዩ መሣሪያዎቹ፣ የሚገጠሙበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው 95% የሆነ።
2. ልዩ መሣሪያዎቹ፣ የሚገጠሙበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ዋጋ መሠረት 95% ከሆነ። ይህም የግዢውንና የመግጠሙን ታክስ ዋጋ ጨምሮ ነው።

### የባለመብትነት ሁኔታዎች

"እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው ልዩ የመኪና መሣሪያዎችን ለመግዛትና ለማስገጠም ብድሩን የመውሰድ መብት የሚኖረው የሚቀጥሉትን መስፈርቶች **በሙሉ** የሚያሟላ ከሆነ ነው።

- መሣሪያው በሚገጠምበት ቀን የእንቅስቃሴ ተቆራጭ (“ኪጽባት ናያዱት”) የሚቀበል ከሆነ።
- የሕክምና ኮሚቴ ወይም የሕክምና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ተሽከርካሪ ወንበር ወስኖለት ከሆነና በወንበሩ እየተጠቀመበት ካለ።
- የመንገድ ደኅንነት የሕክምና ተቋም የወሰነለት መኪና የተለዩ መሣሪያዎች የሚገጠሙበት መኪና መሆኑን ከወሰነ እና በመኪናው ላይ የሚገጠሙበትንም መሣሪያዎች ከወሰነ።

ብድሩ የሚሰጠው የመንጃ ፈቃድ ላላቸውና ለሌላቸው ሲሆን በ5 ዓመት ውስጥ ወደ ስጦታ ይቀየራል። ይህም ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መሣሪያዎቹ እንዲመለሱለት አስቀድሞ ካልጠየቀ ነው።

> ❯ ለግል መኪና ልዩ መሣሪያዎች ለመቀበል ወይም ሊገዛቸው የስጦታ መብት ያለው ሰው፣ በሕጉ መሠረት ወይም በሌላ ስምምነት እርዳታውን እንደሚቀበል የመምረጥ መብት አለው።

### ለግል መኪናዎች ልዩ መሣሪያዎች ለመግዛት እና ማስገጠም የዋለ ወጪ መመለስ

ለግል መኪናዎች ልዩ መሣሪያዎች ለመግዛት እና ማስገጠም የዋለ ወጪ የሚመለሰው ከእነዚህ ከተጠቀሱት ዋጋዎች ውስጥ አነስተኛ የሆነውን ነው።

1. ልዩ መሣሪያዎቹ፣ የሚገጠሙበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው 95% የሆነ።
2. ልዩ መሣሪያዎቹ፣ የሚገጠሙበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ዋጋ መሠረት 95% ከሆነ።

### የባለመብትነት ሁኔታዎች፡

"እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው ልዩ የመኪና መሣሪያዎችን ለመግዛትና ለማስገጠም ብድሩን የመውሰድ መብት የሚኖረው የሚቀጥሉትን መስፈርቶች **በሙሉ** የሚያሟላ ከሆነ ነው።

- መሣሪያው በሚገጠምበት ቀን የእንቅስቃሴ ተቆራጭ (“ኪጽባት ናያዱት”) የሚቀበል ከሆነ።
- የመንገድ ደኅንነት ሕክምና ተቋም ተሽከርካሪ ልዩ መሣሪያዎቹ ለመንዳት ያመቹታል ብሎ ወስኖለት ከሆነ።
- ጊዜ ያላለፈበት የመንጃ ፈቃድ ካለው።
- ለእሱ የተወሰነለት የግል መኪና ከሆነ።
- መሣሪያዎቹ በተገጠሙ በ6 ወራት ውስጥ የቀረጥ ወረቀት (“ሐሽቦኒት ማስ”) እና የተገጠሙት መሣሪያዎች ዝርዝር ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝ ካለው።

> ❯ ለግል መኪና ልዩ መሣሪያዎች ለመቀበል ወይም ሊገዛቸው የስጦታ መብት ያለው ሰው፣ በሕጉ መሠረት ወይም በሌላ ስምምነት እርዳታውን እንደሚቀበል የመምረጥ መብት አለው።

## የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ መግዣ ብድር

የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ የሚባለው በመኪናው ላይ የተገጠመ መሣሪያ ሲሆን ተሽከርካሪ ወንበሩን ወደ መኪናው ጣራ ላይ የሚያወጣ ወይም ወደ መኪና ዕቃ ማስቀመጫ ክፍል የሚከት መሣሪያ ነው።

የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ መግዣ ብድር ከእነዚህ ከተጠቀሱት ዋጋዎች ውስጥ አነስተኛ የሆነውን ነው።

1. የማንሻ መሣሪያው መግዣ፣ የሚገጠምበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው 95% የሆነ።
2. ወኪል የሆነ (“መያትጻግ) የማንሻ መሣሪያው መግዣ፣ የሚገጠምበት ክፍያና ቀረጡን ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋው 95% የሆነ። የማንሻ መሣሪያው ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለዋወጥ ይችላል።

### የባለመብትነት ሁኔታዎች፡

"እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ ለመግዛትና ለማስገጠም መብት የሚኖረው የሚቀጥሉትን መስፈርቶች **በሙሉ** የሚያሟላ ከሆነ ነው።

- መሣሪያው በሚገጠምበት ቀን የእንቅስቃሴ ተቆራጭ (“ኪጽባት ናያዱት”) የሚቀበል ከሆነ።
- የሕክምና ኮሚቴ ወይም የሕክምና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ተሽከርካሪ ወንበር ያስፈልገዋል ብሎ የወሰነለት እና ወንበሩን እየተጠቀመበት ያለ ከሆነ።
- የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ ሊገጠምለት የሚችል መኪና ያለው እና ለመኪናው የሚስማማውን ማንሻ የገዛ።

ለተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ የሚሆን ብድር በ5 ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሚሆነው "እንቅስቃሴው የተገደበ" ሰው የባለመብትነት መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚቀጥል ከሆነ ነው።

> ❯ የተሽከርካሪ ወንበር ማንሻ ለመቀበል ወይም ሊገዛቸው መብት ያለው ሰው፣ በሕጉ መሠረት ወይም በሌላ ስምምነት ማንሻውን እንደሚቀበል የመምረጥ መብት አለው።

## ለመጓጓዣ የዋለ ወጪ ተመላሽ

በሕክምና ኮሚቴ ፊት መቅረብ ወይም በዝውውር/እንቅስቃሴ ("ናያዱት") ስምምነት መሠረት ሌሎች ምርመራዎችን ማድረግ ያለበት በጤናው ምክንያት እና በሚኖርበት ቦታ ምክንያት በሕዝብ መጓጓዣ መጓጓዝ የማይችል እንዲሁም ምርመራዎቹ በተደረጉበት ወር የዝውውር/እንቅስቃሴ ("ናያዱት") ተቆራጭ መብት ከሌለው በተወሰኑ መስፈርቶች ለመጓጓዣ ያወጣቸው ወጪዎች ይመለሱለት ዘንድ መብት አለው።

## ልዩ መሣሪያዎች በተገጠሙለት መኪና መንዳትን ለመለማመድ

ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ በእንቅስቃሴያቸው የተገደቡ በተሽከርካሪ ወንበር የሚጠቀሙ ሰዎች ልዩ መሣሪያዎች በተገጠሙበት መኪና ላይ እንዲለማመዱ ልዩ ፕሮግራም ያንቀሳቅሳል።
ልምምዱ የሚደረገው የተራቀቁ የመንጃ መሣሪያዎች በተገጠሙበት መኪና ላይ ሲሆን ትምህርቱ የሚሰጠው አካለ ስንኩላንን መንዳት በሚያለማምዱ አስተማሪዎች አማካይነት ነው።
ልዩ የመንጃ መሣሪያዎች የተገጠሙበት መኪናን መንዳት መለማመድ የሚፈልግ ግለሰብ 8261/7ב የተሰኘ የማመልከቻ ፎርም መሙላት አለበት።

## የመኪና ማቆሚያ ወረቀት/ካርድ

የመኪና ማቆሚያው ካርድ የሚሰጠው በትራንስፖርት ሚኒስቴር አማካይነት ነው።
ለአካለ ስንኩላን ለሚሰጠው የመኪና ማቆሚያ ካርድ ባለመብት የሚሆነው፡-


- በእንቅስቃሴ ረገድ የእንቅስቃሴ ገደብ ፐርሰንት የተወሰነለት
- እንቅስቃሴን በሚመለከት ጥቅማጥቅም የማያገኝ ነገር ግን ቢያንስ 60% አካለ ስንኩልነት የተወሰነለት እና በትራንስፖርት ሚኒስቴር የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ።

ዝርዝር መረጃዎች በትራንስፖርት ሚኒስቴር ድረ ገጽ ላይ።

## ለመንቀሳቀሻ ድጐማ ጥያቄ አቀራረብ

የ"ናያዱት" ጥቅማጥቅም ማመልከቻ ከማቅረብ በፊት ለክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ የእንቅስቃሴን ገደብ ለማስወሰን የሕክምና ምርመራ እንዲደረግ 8220/7ב የተሰኘ የማመልከቻ ፎርም መላክ ያስፈልጋል።
ፎርሙን ከዞኑ የጤና ጥበቃ ቢሮ፣ ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፎችና ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የዞኑ ሕክምና ኮሚቴ ድጐማ (“ጊማላ”) የሚያስገኘውን የእንቅስቃሴውን ችግር ደረጃ ከወሰነ በኋላ የእንቅስቃሴ ጥቅማጥቅሞች ለማግኘት ለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ማመልከት ያስፈልጋል።
8200/7ב የተሰኘውን የማመልከቻ ፎርም ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፎችና ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።
በሕክምና ኮሚቴው ውሳኔ የተጎዳ መስሎ የሚታየው ሰው ውሳኔውን በተቀበለ በ60 ቀናት ውስጥ ለጤና ጥበቃ የጤና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

# በአደጋ የተጎዱ ሰዎች ዋስትና



በአደጋ የተጎዱ ሰዎች ዋስትና በአደጋ፣ በቤት፣ በዕረፍትና መዝናኛ ጊዜ ለተጎዳው ሰው እንደዚሁም በአደጋው ምክንያት የመሥራት ችሎታውን ያጣው ተቆራጭ ያገኛል። በሕጉ መሠረት ተቆራጩ የሚከፈለው የመሥራት ችሎታ ለታጣበት ቢበዛ ለ90 ቀናት ነው።

## አደጋ ስንል ምን ማለት ነው?

የገንዘብ ድጎማ ሊያሰጥ የሚችል አደጋ ማለት አንድ ግለሰብ **በውጫዊ ምክንያቶች** ያልተጠበቀ ድንገተኛ አደጋ ከደረሰበትና መሥራት የማይችል ከሆነ ነው።

መሥራት የማይችል የሚባለው የሚከተሉትን መስፈርት ካሟላ ነው፡

- ተቀጥሮ ወይም በግል ሥራ የሚተዳደር ግለሰብ ሥራዉን መቀጠል ካልቻለ ወይንም ሌላ የሥራ ዓይነት መሥራት ካልቻለ
- ተቀጥሮ ወይንም በግል ሥራ የማይሠራ በተጨማሪም በሆስፒታል በሕክምና ላይ ወይንም ቤቱ የአልጋ ቁራኛ ከሆነ ነው
- የቤት እመቤት – በቤት ውስጥ ምንም ዓይነት የሥራ እንቅስቃሴ ማድረግ የማትችል ከሆነ ነው።

## አደጋ ለደረሰበት የሚሰጠውን ድጎማ የመቀበል መብት ያለው ማን ነው?

ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው ግለሰብና እስከ የጡረታ መውጫ የዕድሜ ክልል ያለ፣ ተቀማጭነቱ በእስራኤል ሀገር የሆነ (አዛውንትን በተመለከተ ያለውን ምዕራፍ ተመልከት)፣ በእስራኤል ሀገር ወይንም ውጭ ሀገር አደጋ የደረሰበት በተጨማሪም መሥራት የማይችሉ ከሆነ በእስራኤል ሀገር የቆዩበት ጊዜ ታስቦ ከላይ በተጠቀሱት መስፈርቶችና በሌላ ቦታ ሥራ ካልሠራ የጤና ምርመራ ካደረገና **አደጋው ካጋጠመው በ72 ሰዓት ውስጥ የጤና ምርመራ ካደረገ** ለአደጋ የሚሰጠው ድጎማ ይደርሰዋል።

ለአደጋ ጊዜ የሚሰጠው ድጎማ ለአንድ ግለሰብ የማይሰጠው መሥራት በማይችልበት ወቅት ሌላ የድጎማ ዓይነቶችን ለመቀበል ባለመብት ከሆነ ነው። ለምሳሌ የበሽታ ክፍያ፣ የመኪና አደጋ ለደረሰባቸው የካሳ ክፍያ ሕግ፣ ወዘተ.

## አደጋ ላጋጠመው ግለሰብ ለቀን የሚታሰብለት ሒሳብ

- **ተቀጥሮ ለሚሠራ ወይንም በግል ሥራ ለሚተዳደር ግለሰብ አደጋው ከመድረሱ 4 ወራት በፊት ለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መ/ቤት ይከፈል ከነበረው ገንዘብ 75% እጅ ይህንንም በ90 በማካፈል (በጥር 2014 ለቀን ከፍተኛው ክፍያ እስከ 1,094.63 ሼቄል ይጠጋል)።**
- **ለማይሠሩ ግለሰቦች እና የቤት እመቤት ለሆኑ በቀን 72.98 ሼቄል በጥር 2014**

## የክፍያ ጊዜ

**አደጋው ከተከሰተ ማግስት ጀምሮ ለ90 ተከታታይ ቀናት ለአደጋ ተብሎ የሚከፈለው ክፍያ ይከፈላል።**

**ተቀጥሮ ለሚሠራ ወይንም በግል ሥራ ተዳዳሪ ለሆነ** መሥራት ያልቻለው ከ12 ቀናት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ለአደጋ ተብሎ የሚከፈለው ክፍያ አይከፈለውም።

**ለማትሠራና የቤት እመቤት ለሆነች** አደጋ ከደረሰበት ማግስት ጀምሮ ላሉት 14 ቀናት ይህ ለአደጋ ተብሎ የሚከፈለው ክፍያ አይከፈላቸውም።

## የይግባኝ ማመልከቻ ስለ ማቅረብ

**አደጋው ከደረሰባቸው አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ** የሕክምና መረጃ በመያዝ አቅራቢያችሁ ከሚገኘው የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መ/ቤት በአደጋ ለተጎዱ የሚሰጠውን ድጎማ እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ማቅረብ ትችላላችሁ። ከተባለው ቀን አልፎ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት ላያገኙ ይችላሉ።

የማመልከቻ ፎርም የሆነውን 2201/ל ב ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ወይንም ከመሥሪያ ቤቱ ድረ ገጽ ማውረድ ትችላላችሁ። ፎርሙንም በፖስታ ቤት፣ በፋክስ ወይንም በቅርንጫፉ የሳጥን አገልግሎት መላክ ትችላላችሁ።

# በቤተሰብ ውስጥ በተፈጠረ ሁከት ምክንያት ወላጆቹ ለሞቱበት ልጅ የሚሰጥ ድጎማ

ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ባል/ሚስት በፈጠሩት ሁከት ምክንያት ወላጁ ለሞተበት ልጅ ልዩ ድጎማ ይከፍላል።

ይህ ድጎማ የሚከፈለው የሟች ልጆች ባለመብት ከሆኑትና ከሚቀበሉት ሌሎች ድጎማዎች በተጨማሪ ነው። እነዚህም ለምሳሌ የልጆች ድጎማ፣ የ"ሸአሪም" ድጎማ እና ሌሎች "ቂጽባዎች" ናቸው።

## የባለመብትነት ሁኔታዎች

ልጁ ለዚህ ድጎማ ባለመብት የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ያሉት እንደሆነ ነው፡

- የሞተው ወላጅ የእስራኤል ኗሪ ከሆነ
- አንዱ ወላጅ ሕይወቱን ያጣው በባሉ/ሚስቱ ሲሆን (የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ሳይፈጽሙ በጓደኝነት ያሉትንም ያካትታል)
- የ የአገሪቱ አቃቤ ሕግ ሁኔታው ድጎማ እንደሚያሰጥ ከፈቀደ
- ግድያው የተፈጸመው ከ1.3.1994 በኋላ ከሆነ

## የድጎማው መጠን

**100% – 60% ከሙሉ ድጎማው 6817 ሼቄል በጥር 2014፣ እንደ ልጆቹ ቁጥር መጠን።**

## ለድጎማው ማመልከት

ልጁ በእሱ እንክብካቤ ሥር የሆነ ሰው ማመልከት ይችላል። ይህም ያለ ሕጋዊ ጠባቂ ("አፖትሮፑስ") ትእዛዝም ሊፈጸመ የሚችል ሲሆን የ"ረቫኻ" አገልግሎት የድጋፍ ደብዳቤ አያይዞ ማቅረብ ያስፈልጋል።
18 ዓመት የሞላው ልጅ ጥያቄውን ራሱ ማቅረብ ይችላል።
ይህን የድጎማ መጠየቂያ ማመልከቻ በአቅራቢያ በሚገኝ የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማቅረብ ይቻላል። 235/ל ב የተሰኘውን የማመልከቻ ፎርም ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ከኢንተርኔት አውርዶ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

# ሙያዊ ማገገሚያ



በቢቱዋሕ ሌኡሚ ውስጥ ያለ ሙያዊ ማገገሚያ ማለት የሕክምና ሂደት ሲሆን አካለ ስንኩላንን እና ባል የሞተባቸው ተስማሚ ሥራ አግኝተው ተዋህደው እንዲሠሩ ለመርዳት ነው። እንደዚሁም የ“ረቫኻ” አገልግሎቶች በሥራ ላይ እያሉ አደጋ ለደረሰባቸውና በጠላት ተንኰል ጉዳት ለደረሰባቸው ጭምር ነው።

## ለሙያዊ ማገገሚያ ባለመብት የሚሆኑት እነማን ናቸው?

- በሥራ የአካል ጉዳት የደረሰበትና 10% የአካል ጉዳተኛነቱ የታወቀለት ወይም ጉዳቱ ሙያ በሚማርበት ጊዜ የታወቀለት ከሆነ
- አካለ ጐደሎ – በሥራ ወይም በጠላት የተጎዳ ሳይሆን፣ የሕክምና አካለ ጎደሎነት ተረጋግጦለት 20% አካለ ጎደሎ ሆኖ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የአካለ ጎደሎ ድጐማ ባይቀበልም፣ ለሙያዊ ማገገሚያ ባለ መብት ይሆናል።
- በጠላት የአካል ጉድለት የደረሰበትና 20% የአካል ጎደሎነት የተወሰነለት እንደሆነ፣ በጠላት ተጎድቶ በዚህ ምክንያት የሞተ እንድሆነ የሟች ሚስትና የሟች ልጆች ለሙያዊ ማገገሚያ ባለመብት ይሆናሉ።
- ባሏ የሞተባት/ሚስቱ የሞተችበት ሆነው በ“ሽኢሪም” ወይም በሥራ ጊዜ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ጥገኞች መምሪያ ክፍል የታወቁ ከሆኑ

በደረሰባቸው የአካል ጉድለት ምክንያት በቀድሞ የሥራ ቦታቸው ተመልሰው መሥራት የማይችሉ ከሆነ፣ ወይም በሌላ በሚስማማቸው የሥራ ቦታ ገብተው መሥራት የማይችሉ ከሆነ እነዚህ ሁሉ ለሙያዊ ማገገሚያ ባለመብቶች እንዲሆኑ ተወስኗል።

ባሏ የሞተባት/ሚስቱ የሞተችበት፣ ዕድሜያቸው ሥራ መሥራት በሚያስችል ክልል ውስጥ ሆነው ግን ሙያ የሌላቸው ከሆኑ ወይም ለመኖር በሙያቸው የማይተዳደሩ፣ ወይም ባል/ሚስት በመሞቱ ምክንያት የሙያ ለውጥ ማድረግ ያስፈለጋችው ከሆነ፣ ለሙያዊ ማገገሚያ ባለመብት ይሆናሉ።

## የሙያዊ ማገገሚያ አገልግሎቶች ምን ናቸው?

- ለምርመራና ለሙያ መመሪያ እርዳታ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው።
- በማገገሚያ ወቅት ወይም በትምህርት ወቅት በሚከፈለው ክፍያ ዕርዳታ ያገኛል። (የአካለ ስንኩልነት ድጐማ ለማይቀበል ወይም በግማሽ ለሚቀበል አካለ ስንኩል)
- ለኑሮ መደጐሚያ የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ (ሚስት/ባል ለሞተባቸው)
- እንደዚሁም ትምህርት ነክ ለሆኑ ወጭዎች ለምሳሌ፣ የትምህርት ክፍያ፣ የትራንስፖርት ወጭዎች፣ መጽሐፎችና የትምህርት መሣሪያዎች።

ሁሉም ክፍያ በትምህርት ሰዓትና በመተዳደሪያው ደንብ መሠረት ነው።

በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የሚሠራ በማገገሚያ ዘርፍ ባለሙያ የሆነ የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ፣ አካል ጉዳተኛው ተስማሚውን ሙያ እንዲመርጥ ይረዳዋል። ይህም ሠራተኛው አካል ጉዳተኛውን በደንብ ካወቀውና ምኞቱን፣ ችሎታውንና የሚገድቡትን ሁኔታዎች ካአራ በኋላ ነው።

የማገገሚያው ባለሙያ እንደየአስፈላጊነቱ ከሕክምና፣ ሥነ ልቡና፣ የሥራ መስክና ሌሎችም ባለሙያዎች ጋር ይመካከራል። ይህም ሲሆን በገበያ ላይ ያለውን ተፈላጊነት፣ ሙያውን ለመቀበል ያደረገውን ጥረት ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

የትምህርቱ ጊዜ፣ ባሕሪይና ቦታው፣ የሚወሰኑት እንደአካል ጉዳተኛው ጤንነት ሁኔታ፣ የአካለ ጉደሎነቱ መጠን በመቶኛ፣ ችሎታዎቹና የመረጠው ሙያ ከግምት ከገቡ በኋላ ነው። ሙያውን በትምህርቱ መጨረሻ የምስክር ወረቀት ወይም ዲግሪ ሊሰጡ በሚችሉ የተለያዩ የትምህርትና ሙያዊ ሥልጠና ማዕከላት ውስጥ መማር ይቻላል። በጽልጠናው ሂደት መጨረሻ ወደ ሥራ ገበታ ለመሰማራት “ህሳማ” በተባለው ፕሮግራም እርዳታ መቀበል ይቻላል።

የማገገሚያ አገልግሎት በተለያዩ መንገዶች ሊሰጡ ይችላሉ እነዚህም፣ ግላዊ የሆኑ፣በቡድን በሚሰጡ ትምህርቶች (“ሳድናዎች”)፣ ማኅበራዊ ድርጊቶች በሚረዱ ሁኔታዎች በሂደት ይሰጣሉ።

## በሥራና በጠላት ለተጎዱ የሚሰጠው የ“የረቫሃ አገልግሎት እርዳታ፤

በ”ረቫሃ” አገልግሎት በኩል በሕግና በደንቡ መሠረት፣ በሥራና በጦርነት ለተጎዱ የአካል ጉዳተኞች የድጐማና የማገገም እርዳታ ተጨምሯል።

### በሥራ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው

የአካለ ስንኩልነታቸው ደረጃ ቢያንስ 75% የሆነ ወይም መሄድ ያቃታቸውና የአካለ ስንኩልነታቸው ደረጃ 65%-74% የሆነ፣ በተለዩ ሁኔታዎች ለግል መንከባከቢያ ልዩ የሆነ ድጐማ ባለመብት ይሆናሉ። ይህም ዕርዳታ ለአንድ ጊዜ መገልገያ የሚሆን መኪና መግዣ፣ መኖሪያ ቤትን ለማመቻቸትና አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟያ የሚያገለግላቸው ሲሆን ከቦታ ቦታ ራሳቸውን ችለው ለማይሄዱ አካል ጉዳተኞች የሚሰጥ ነው።

### በጠላት እንቅስቃሴ የተጎዱና፤ በጠላት እንቅስቃሴ ጊዜ በሞት ለተለዩ፣ ለሐዘንተኛ ቤተሰቦች

ለኑሮ መደጐሚያ ከሚቀበሉት በተጨማሪ የሚያግዝ ደጋፊ ይሰጣቸዋል።


በማገገሚያው መምሪያ የሚሠሩ የማኅበራዊ ሠራተኞች በቡድንና በግል፣ ሐዘንና አስከፊ ገጠመኝን (“ትራውማ”) የሚቋቋሙበት ዕገዛ ያደርጉላቸዋል። እንደዚሁም ብዙ ዓመት በችግር ያሉ ቤተሰቦችን የሚያግዙ በጎ አድራጊዎች ይመደባሉ።

## ለሙያ ማገገሚያ ማመልከት

በምትኖሩበት አካባቢ በሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ፎርም 270/7ቧን ሞልቶ ማስገባት። በኢንተርኔትም በቢቱዋሕ ልዑሚ ድረ ገጽ በማውረድ በፖስታ ወይም በፋክስ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት መላክ ይቻላል።

> ለሙያ ማገገሚያ ባለመብት መሆናችሁን ለማወቅ መኖሪያ ቤታችሁ አቅራቢያ ለሚገኝ ቅርንጫፍ ማገገሚያ ክፍል እንድታመለክቱ ትጋበዛላችሁ። ለተጨማሪ ዝርዝሮች ለስልክ ቁጥር 02-6463488 ደውሉ።

# የሀቭታሐት ሀክናሳ ድጐማ



**"ሀቭታሐት ሀክናሳ" ማለት ለኑሮ የሚያስፈልገውን ዝቅተኛውን ገቢ ማግኘት ላልቻለ ለእያንዳንዱ እስራኤላዊ ሆነ ቤተሰብ የሚከፈል ድጐማ ነው።**

## የሀቭታሐት ሀክናሳ ድጐማ ባለመብት ማን ነው?

የእስራኤል ኗሪ የሆነ ለኑሮው የሚሆን ዋስትና በእጁ የሌለው ሁሉ ለሀቭታሓት ሀክናሳ ድጐማ ባለ መብት ነው። የእስራኤል ኗሪ፣ የገቢው መጠን ለኑሮው ከሚያስፈልገው ገቢ በታች ያነሰ የሆነ እንደሆን ለገቢው ማሟያ ድጐማ ይሰጠዋል፣ (የደመወዝ ማሟያ፣ ለሥራ አጦች የሚሰጥ ገንዘብ፣ እንዲሁም ለልጆች ማሳደጊያ የሚሰጥ. ወዘተ.)

**ድጐማው የሚከፈለው ማመልከቻው ከቀረበበት ወር ጀምሮ ነው።**

## "ሀቭታሐት ሀክናሳ" ለመቀበል ባለመብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች

"ሃቭታሓት ህክናሳ" ለመቀበል የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ሁለቱም ማለትም ባል ሚስት ማሟላት አለባቸው፥

- **ዕድሜ –** 20 ዓመት የሞላው በልዩ ምክንያቶች (በበሽታ፣ እርግዝና፣ አደንዛዥ ዕጽ በመጠቀምና ሌሎችም) አሥራ ስምንት ዓምት የሞላው ከሆነ ሀቭታሓት ሀክናሳ ሊቀበል ይችላል።
- **ተከታታይ ኗሪነት –** ቢያንስ 24 ወራቶች እስራኤል አገር በተከታታይ የኖረ

ይህ ሁኔታ የማይመለከተው - እስራኤል አገር የመጣ አዲስ ገቢ ቢያንስ 12 ወራት ያልሞሉት፣ እስራኤል አገር አዲስ ገቢ ከሆነ ገና 5 ዓመት ያልሆነው፣ ወላጆቹን በሞት ያጣ ልጅ፣ ወላጆቹ የተውት ልጅ፣ ባል/ሚስት ቢያንስ 24 ተከታታይ ወራት የእስራኤል ኗሪ ከሆኑ፣ እሱ ወይም ባላቤቱ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የጡረታ ድጐማ ወይም የ"ሽአሪም" ድጐማ ወይም በሥራ አደጋ የደረሰባቸው የሚቀበሉትን ድጐማ የሚቀበልና በጎ አድራጊዎች የሚቀበሉትን የሚቀበል

- **የገቢና ተሽከርካሪ ምርመራ –** ማመልከቻ ያቀረበው ግለሰብና የባል/ሚስት ገቢ አንድ ላይ ሆነው በሕጉ ከተፈቀደው አነስተኛ ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ከሆነ። ግምት ውስጥ የማይገቡ ገቢዎች አሉ። በይዞታው ወይም በእሱ ጥቅም ሥር ተሽከርካሪ (ሞተር ሳይክልን ጨምሮ) ካሉና ዋጋው ከ40760 ሼቄል የማይበልጥ ከሆነ፣ ከድጐማው ላይ ገንዘብ ይቀነሳል። ገንዘቡ የሚትታሰበው በዕድሜው፣ በገቢው መጠንና በመኪናው ዋጋ ላይ ተመሥርቶ ነው። በሕክምና ምክንያት የተነሣ ተሽከርካሪ ያለው ገቢው ከ40760 ቢበልጥም ከመኪናው የተነሣ ከድጐማው ላይ ምንም ገንዘብ አይቀነስበትም።
- **የሥራ ምርመራ –** ለ"ሀቭታሓት ሀክናሳ" ድጐማ ያመለከተውና ሚስት/ባል ከሚከተሉት ውስጥ እንደ አንዱ የሚቆጠሩ ከሆነ፤
  - ሥራ አጥ
  - ዝቅተኛ በሆነ ደመወዝ የሚሠራ
  - በሙያ ትምህርት ሥልጠና ላይ የሚገኝ

### የሥራው ምርመራ የማይመለከተው፥

- 30 ቀናት በተከታታይ ሊሠራ የማይችል በሽተኛ።
- በሥራ ማገገሚያ ("ሺኩም ሚክጾዒ") ላይ የሚገኝ።
- ዕድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ ወንድና ሴት (ስለ ሽምግልና የተደነገገውን ክፍል ተመልከት)
- ሁለት ዓመት ያልሞላው ልጅ የሚያሳድግ አባት ወይም እናት ብቸኛ አሳዳ
- ያገባ አባት፣ ልጆቹ በእሱ ቁጥጥር ያሉና ከእነሱም ትንሹ ገና 7 ዓመት ያልሞላው ከሆነ
- በሽተኛ ቤተሰብን የሚንከባከብ (ባል/ሚስት፣ ልጅ፣ የሚያሳድገው ልጅ፣ ወላጆች)
- የአካለ ስንኩል ልጅ ወላጅ
- ቢያንስ ከ6 ተከታታይ ወራቶች በኋላ የተፈታ እስረኛ (ከተፈታበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ወራት ያህል)
- የአገልግሎት ሥራ የሚሠራ እስረኛ
- የቁም እስረኛ
- እርጉዝ ሴት (ከ13 ሳምንት የእርግዝና ጊዜ ጀምሮ እስከምትወልድ ድረስ)
- የአልኮሆል ወይም የአደንዛዥ ዕጽ ሱሰኛ የሆነ
- መንገድ የሚኖር (መኖሪያ የሌለው)
- ኡልፓን ተማሪ
- በቢቱዋሕ ሌኡሚ ስምምነት በማገገሚያ የሚገኝ ወይም በእስረኞች ማገገሚያ ባለሥልጣን ወይም መንግሥት በሚቆጣጠረው ማገገሚያ ቦታ የሚገኝ
- በአደጋ ወይም በድንገተኛ ሁኔታ በችግር ላይ የሚገኝ
- ልጅ፣ ከወላጆቹ አንዱ የእስራኤል ኗሪ ሆኖ በእስር ላይ የሚገኝ /አንደኛው ወላጁ የእስራኤል አገር ኗሪ ያልሆነ
- የቤት እስረኛ የሆነን ልጅ፣ ባል/ሚስት የሚጠብቅ
- 75% ብቁ ያለመሆን ደረጃ የተወሰነለት
- በተደበደቡ ሴቶች መሸሸጊያ ("ሚቅላጥ") ውስጥ የምትገኝ ሴት

## "ሀቭታሓት ሀክናሳ" የሚቀበል - ወደ ውጭ በሚሄድበት ጊዜ

"ሀቭታሓት ሀክናሳ" የሚቀበል ወደ ውጭ ከመሄዱ በፊት የድጐማ መብቱን ቢያጣራ ይመረጣል።

- በእስራኤል አገር ወር ሙሉ ያልነበረ "ሀቭታሓት ህክናሳ" ተቀባይ፣ የዚያን ወር ድጐማ የመቀበል ባለመብት አይሆንም፤
- በዓመት ሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከአገር የወጣ (ከጥር 1 እስከ ታኅሣሥ 31 ድረስ) ከአገር በወጣበትና ወደ አገር በተመለሰበት ወሮች "የሀቭታሓት ሀክናሳ" ባለመብት አይሆንም።
- "ሽሩት ታዓሱካ" መገኘት የነበረበት "ሀቭታሓት ሀክናሳ" ተቀባይ ወደ ውጭ በመውጣቱ ምክንያት ሳይገኝ ቢቀር የዚያ ወር ድጐማ ባለ መብት አይሆንም።

> ወደ ውጭ የወጣበት ምክንያት ሕክምና ለመቀበል ከሆነና ይህን ሕክምና እስራኤል ውስጥ ማግኘት የማይችል ከሆነ፣ ወይም በሽተኛውን ይዞ ለሕክምና ወደ ውጭ የሚሄድ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፈቃድ ያለው፣ ውጭ በቆየበት ጊዜ እስከ 6 ወራት የ"ሀቭታሓት ሀክናሳ" ባለመብት ይሆናል።

## ዝቅተኛ ደመወዝ ተከፍሎት የሚሠራ

ቅጥር ሠራተኛ ወይም የግል ሠራተኛ ከሥራ የሚያገኘው ገቢ በሰንጠረዡ ላይ ከተጠቀሰው መጠን በታች ከሆነ፣ **ለገቢ ማሟያ ጭማሪ** ባለመብት ሊሆን ይችላል። ይህም ሊሆን የሚችለው ሙሉ ሰዓት የሚሠራ ከሆነ፣ ወይም በጤንነቱ ወይም በሌላ ምክንያት በከፊል የሚሠራ ከሆነ ነው።

ከአደጋ በተከለለ ፋብሪካ ውስጥ የሚሠራ ለገቢ ማሟያ ጭማሪ ባለመብት ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው በፋብሪካው ውስጥ ተቀባይ በሆነ የሥራ መጠን የሚሠራ ከሆነ ነው።

## ለድጐማው ባለመብት የማይሆኑት

- ተቋም ውስጥ የሚገኝና ይህ ተቋም ወጭው በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሶክኑት ሃየሁዲት፣ በከተማ አስተዳደር ወይም በሃይማኖት ተቋማት የሚሸፈን ከሆነ፣
- መደበኛ ውትድርና አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብና ባለቤቱ
- የኪቡጽ ወይም ሞሻቭ አባል
- በከፍተኛ ተቋማት የሚማር ተማሪ፣ ከሁለተኛ ደረጃ በላይ በሚያስተምር ተቋም ውስጥ የሚማር፣ በ"የሺቫ" እና ቅስናን ባሚያስተምሩ ተቋሞች የሚማሩ


ቢሆንም በ"ሽሩት ተእሱካ" ሽኜ ደብዳቤ መሠረት የሚማርና ብቸኛ ወላጅ የሆነ በተወሰኑ ሁኔታዎች ባለመብት ሊሆን ይችላል።

## ለ"አቭታሓት ሀክናሳ" ማመልከቻ አቀራረብ

ይህን የድጐማ መጠየቂያ ማመልከቻ በአቅራቢያ በሚገኝ የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማቅረብ ይቻላል። ድጐማው የሚከፈለው ማመልከቻው ከገባበት ወር ጀምሮ ነው። የ"ሀቭታሓት ሀክናሳ" ውዝፍ ስለማይከፈል ማመልከቻ ሳታስገቡ አትቆዩ።
የማመልከቻውን ፎርም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ከኢንተርኔት አውርዶ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

## በሞት ጊዜ የሚሰጥ ገንዘብ፣

ይህ የአንድ ጊዜ የስጦታ ገንዘብ የሚሰጠው "ሀቭታሓት ሀክናሳ" ሲቀበል ቆይቶ ለሞተው ሰው ለባል/ሚስት፣ ባል/ሚስት ከሌለ ለልጅ (በሕጉ በተጠቀሰው መሠረት)
**የገንዘቡ መጠን በጥር 2012፣ 8757 ሼቄል ነው።**



| በጥር 2016 የሙሉ ድጐማው መጠን በሼቄል* | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የቤተሰብ አወቃቀር | "ሚብሐን ታዓሱካ" የማይመለከታቸው፣ዕድሜያቸው 20+-25 ወይም ልጆች ያሏቸው፣ ዕድሜያቸው 20-55 የሆነ በማንኛውም የባለመብትነት ምክንያት** | | ዕድሜያቸው 55 እና ከዚያ በላይ የሆኑ | |
| | የሙሉ ድጐማው መጠን | ለድጐማው ባለመብት የሚያደርግ ከፍተኛው የሥራ ገቢ (ከሥራው ውጪ ሌሎች ገቢዎች ከሌሉ) | የሙሉ ድጐማው መጠን | ለድጐማው ባለመብት የሚያደርግ ከፍተኛው የሥራ ገቢ |
| ወንደላጤ/ሴተላጤ | 1,730 | 2,944 | 2,162 | 3,596 |
| ባልና ሚስት | 2,378 | 4,059 | 3,243 | 5,158 |
| ባልና ሚስት + ልጅ | 2,594 | 4,505 | 3,762 | 5,726 |
| ባልና ሚስት + 2 ልጆችና ከዚያ በላይ | 2,897 | 5,297 | 4,281 | 6,434 |
| አንድ ወላጅ + ልጅ | 2,897 | 5,490 | 3,535 | 7,484 |
| አንድ ወላጅ + 2 ልጆች | 3,373 | 6,284 | 4,400 | 8,926 |
| ወላጅ የሞተበት ልጅ/የተተወ ልጅ | 2,022 | | | |
| 2 ወላጅ የሞተባቸው ልጆች /2 የተተው ልጆች | 2,963 | | | |
| ማንኛውም ወላጅ የሞተበት ልጅ/የተተወ ልጅ | 865 | | | |

* ከባልና ሚስት ውስጥ አንዱ ተኝቶ የሚታከም ከሆነና ወጪው በሙሉ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በ"ሶኽኑት ሀይሁዲት ወይም በካባቢ አስተዳደር የሚሸፈን ከሆነ፣ ባል/ሚስት የእስራኤል ኗሪ ካልሆኑ፣ ዕድሜዋ አነስተኛ ሆኖ ከወላጆቿ ጋር የምትኖር ከሆነ ጀድጐማው ገንዘብ ላይ 649 ሼቄል ይቀነሳል።

** ዕድሜያቸው ከ20 እስከ 25 የሆኑና ልጅ የሌላቸው እንደዚሁም አስገዳጅ የሥራ ፈተና ("ሚቭሐን ታዓሱካ") ያለባቸው ድጐማቸው በ20% ይቀንሳል።
ዕድሜያቸው ከ25 እስከ 55 የሆኑና ከፍ ያለ ፐርሰንት ያለው ድጐማ ከ12/2002 ጀምረው በተከታታይ የተቀበሉ ወይም የ6 ተከታታይ ወር ዕረፍት አድርገው የተቀበሉ ከፍ ያለ የድጐማ ፐርሰንት ይኖራቸዋል።

› የሚደርስህን ተቆራጭ መጠን ማወቅ ከፈለግክ – ቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ወደሚገኘው የሀቭታሐት ሀክናሳ ማስሊያ ውስጥ ግባ።

# የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ

**የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የታለመው የእስራኤል ኗሪ የሆኑ፣ በእጃቸው ለልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የፍርድ ቤት ውሳኔ ያላቸውን እናትና ልጅ ለመርዳት ሲሆን እነሱም መክፈል ከሚገባው ግለሰብ ክፍያውን የማይቀበሉ ከሆነ ነው።**



የገንዘቡ መጠን ለልጅ ማሳደጊያ በተፈረደው መሠረት ወይም በቢቱዋሕ ሌኡሚ ደንብ መሠረት – በጣም ትንሽ በሆነው መጠን መሠረት። ቢቱዋሕ ሌኡሚ ለባለ መብቱ ገብዘቡን በየወሩ ይከፍልና በፍርዱ መሠረት ከባለዕዳው ሙሉውን ገንዘብ ያስከፍላል። ቢቱዋሕ ሌኡሚ ባለዕዳውን ገንዘቡን ማስከፈል ከቻለ፣ የሚያስከፍለው መጠን ቢቱዋሕ ሌኡሚ ለባለመብቱ ከሚከፍለው የበለጠ ከሆነ፣ ልዩነቱን ለባመብቱ ይከፍላል።

> ❯ የሚደርስሽን የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ መጠን ማወቅ ከፈለግሽ – ቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ ወደሚገኘው "ሜዞኖት" ማስሊያ ውስጥ ግባ።

## ለልጆች ማሳደጊያ ለሚሰጠው ገንዘብ ባለመብት ማን ነው?

- **ሚስት** የእስራኤል አገር ኗሪ የሆነችና ከፍርድ ቤት የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የተፈረደላት፣ ከባለዕዳው ጋር አብራ የማትኖር፣ ባለ ዕዳው የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ በተፈረደበት ጊዜ የእስራኤል ኗሪ የሆነ ወይም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ከ48 ወራቶች የመጨረሻዎቹን 24 ወራቶች እስራኤል አገር የኖረ።
- **ልጅ** የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የተፈረደለትና ከእናቱ ጋር የሚኖር።

## የመብቱ ሁኔታዎች

- ለሴት – የምታሳድገው ቢያንስ አንድ ልጅ ከእሷ ጋር ካለ ወይም ያገባች እራሷን ማስተዳደር የማትችል፣ (የምታሳድገው ልጅ እንኳን ከእሷ ጋር ባይኖርም)፣ ዕድሜዋ 60 እና ከዚያ በላይ የሆነ (የምታሳድገው ልጅ እንኳን ከእሷ ጋር ባይኖርም)
- ልጅ – እስከ 18 ዓመት ወይም እናቱ ያልያዘችውና ከእናቱ ጋር የማይኖር፣ እራሱን ማስተዳደር የማይችል፣ በመንግሥት ሆነ በአካባቢ አስተዳደር ወጪ ያልተያዘ ከሆነ።
- የገቢ መጠን ምርመራ – በሕጉ መሠረት የገቢ መጠን ምርመራን የሚያሟላ ከሆነ።
- የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የምትቀበለው ሴት ከአገር የወጣች እንደሆነ ገንዘቡን መቀበሏን ትቀጥላለች። ገንዘቡን የምትቀበለውም በዓመት ውስጥ ወደ ውጪ የወጣችው **ከ3 ጊዜ የማይበልጥ** ከሆነና (ከጥር 1 እስከ ታኅሣሥ 31 ድረስ) አጠቃላይ ቀናቱ ከ72 የማይበልጡ ከሆነ ነው። ጉዞው ለሕክምና እስከሆነ ድረስ እነዚህ መመሪያዎች ተግባራዊ አይሆኑም።፣

| በቢቱዋሕ ሌኡሚ ደንብ መሠረት በ2016 የሚሰጠው የገንዘብ መጠን | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 55 ዓመት ያልሞላት | | 55 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናት | |
| | የተቆራጩ ገንዘብ መጠን | ድጐማው ዜሮ የሚሆንበት ነጥብ* | የተቆራጩ ገንዘብ መጠን | ድጐማው ዜሮ የሚሆንበት ነጥብ* |
| ልጆች የሌሏት ሴት ማመልከቻ ካቀረበች | 1,730 ሼቄል | 2,934 ሼቄል | 2,162 ሼቄል | 4,832 ሼቄል |
| አንድ ልጅ ያላት ሴት | 2,897 ሼቄል | 5,489 ሼቄል | 3,535 ሼቄል | 7,499 ሼቄል |
| 2 ወይም ከዚያ በላይ ልጆች ያሏት ሴት | 3,373 ሼቄል | 6,282 ሼቄል | 4,400 ሼቄል | 8,941 ሼቄል |
| እንደገና ያገባች ሴት/በሕዝቡ የምትታወቅ + ልጅ | 2,022 ሼቄል | 4,030 ሼቄል | 2,022 ሼቄል | 4,977 ሼቄል |
| እንደገና ያገባች ሴት/በሕዝቡ የምትታወቅ + 2 እና ከዚያ በላይ ልጆች | 2,963 ሼቄል | 5,599 ሼቄል | 2,963 ሼቄል | 6,546 ሼቄል |
| ሞግዚት (አፖትሮፑስ) ሥር ያለ ልጅ | 2,022 ሼቄል | 3,360 ሼቄል | | |
| በሞግዚት (አፖትሮፑስ) ሥር ያለ 2 ልጆች | 2,963 ሼቄል | 4,893 ሼቄል | | |
| በሞግዚት (አፖትሮፑስ) ሥር ያለ እያንዳንዱ ተጨማሪ ልጅ | 865 ሼቄል | 1,236 ሼቄል | | |

* የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የምትቀበለው ሴት ገቢ ከሥራና ከድጐማዎች የምታገኘው እዚህ የተጠቀሱትን ዝቅተኛ መጠን የሚተኩ ከሆነ የምታገኘው የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ በከፊል ይሆናል።
ገቢዋ ከዚህ መጠን ከፍ የሚል ከሆነ የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ ለመቀበል ባለመብት አትሆንም።

## ለልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ ማመልከት፣

ለልጅ ማሳደጊያ መጠየቂያ የተዘጋጀውን ፎርም 5400/ב በመሙላት በመኖሪያ አካባቢ በሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ማመልከት ይቻላል። በተጨማሪም ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ አውርዶ በመሙላት በደብዳቤ ወይም በፋክስ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማመልከት ይቻላል።

ከማመልከቻው ፎርም ጋር የፍርዱን ወረቀት ዋና ቅጅ ማያያዝ ያስፈልጋል። ከ"ሆጻአ ለፖአል" ፋይል እንደሌላት ማረጋገጫ ደብዳቤ ማምጣት ያስፈልጋታል፤ የመጨረሻዎቹን 3 ወራት የደመወዝ መጠን የሚያሳዩ "ትሉሾች"፣ ከባንክ የባንኩ ሒሳብ በሴቷ ስም ብቻ መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ ማምጣት ያስፈልጋል።

# ለጽዮናዊ እስረኞችና በጠላት እጅ ተይዞ በሌላ አገር ለተገደለ ቤተሰቦች የሚሰጥ ድጐማ

የእስራኤል ዜግነት ያለውና እስራኤል ኗሪ ሆኖ፣ የጽዮናዊ እስረኛ መሆኑን የሚፈቅደው ባለሥልጣን ራሱ ወይም በእስር ቤት የሚገኝ የጽዮናዊ እስረኛ ቤተሰብ፣ በይሁዲነቱ የተገደለው ቤተሰቦች፣ በሕጉ መሠረት በ1992 እንደተወሰነው የጽዮናዊ እስረኛና ቤተሰቦቻቸው ለዚህ ድጐማ ባለመብት ይሆናሉ።

**የባለመብት ዓይነቶች**

- በጽዮናዊነቱ የታሰረ ወይም የተያዘ፣ በመታሰሩ፣ በመያዙና በመሰደዱ ምክንያት አካሉ የጎደለ፣ የአካል ጉድለቱ ደረጃ ቢያንስ 10% የሆነ።
- የጽዮናዊ እስረኛ ወይም የተያዘ፣ የአካል ጎዳት ባይደርስበትም የገቢ መመዘኛን የሚያሟላ ከሆነ።
- በጽዮናዊነቱ የታሰረ ወይም የተያዘና ተይዞ ከስድስት ወራት በላይ የቆየ፣ እንዲሁም በጠላት አገር በእሥራት የሚገኝ ቢያንስ ከጠፋ ስድስት ወር ያለፈው ግለሰብ ባለቤትና ልጆች ለዚህ ድጐማ ባለመብት ይሆናሉ።
- ተይዞ ወይም ታስሮ ወይም በስደት የነበረና እስራኤል አገር ከተቋቋመች በኋላ የሞተ የጽዮናዊ እስረኛ ቤተሰቦች*
- እስራኤል አገር ከተቋቋመች በኋላ በሌላ አገር ለጽዮናዊነት እንቅስቃሴ በማድረጉ፣ ይሁዲ በመሆኑ ወይም ለእስራኤል ባለው ድጋፍ ምክንያት የተገደለ ግለሰብ ቤተሰቦች*፣ ባሏ በውጭ አገር ታስሮ ወይም ተይዞ የሞተባት ሴት፣ በሕጉ መሠረት የዚህ ድጐማ ባለ መብት አይደለችም።
- ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድጐማ ሲቀበል የነበረ ጽዮናዊ እስረኛ ከሞተ የሚቹ ሚስት/ባል፣ ወይም ልጆች (ወላጅ አልባ የሆኑ)

## አካሉ ለጐደለ ጽዮናዊ እስረኛ የሚሰጥ ድጐማ

የድጐማው መጠን የሚወሰነው እንደ አካለ ጐደሎነቱ ፐርሰንት መጠን ነው። የአካል ጎደሎነቱ ደረጃ 100% የተሰጠው አካለ ጐደሎ በምዕራፍ 4ሀ ከናዚ ጋር ለተዋጉ በተወሰነው ሕግ መሠረት የተወሰነውን ያገኛል።

**በጥር ወር 2016 – 4,506 ሼቄል።**

## እንደገቢው መጠን ለጽዮናዊ እስረኛ የሚሰጥ ድጐማ

ይህ ድጐማ የሚከፈለው የገቢ መመዘኛ ለሚያሟላ አካሉ ለጎደለ ለጽዮናዊ እስረኛና አካሉ ላልጎደለ ጽዮናዊ እስረኛም ጭምር ነው። **የዚህም ከፍተኛው የድጐማ መጠን ለአንድ ሰው 2680 ሼቄል** (በጥር ወር 2016) **ለባልና ሚስት ደግሞ 4020 ሼቄል** (በጥር ወር 2016) ለዚህ ድጐማ ባለመብት የሆነ እንደ ገቢው መጠን ከአርኖና 66% ቅናሽ ያገኛል።

## እስራት ላይ ለሚገኝ ጽዮናዊ እስረኛ ሚስት/ባልና ልጆች የሚሰጥ ድጐማ

የድጐማው መጠን በባል/ሚስት ገቢ መጠን ይወሰናል።
ምንም ገቢ የሌለው ሰው ሀብታሓት ሀክናሳ የሚቀበለውን ያህል ድጐማ ይከፈለዋል።

## ጽዮናዊው እስረኛ በእስር ላይ እንዳለ ለሞተባቸው ቤተሰቦች የሚሰጥ ድጐማ

ይህ ድጐማ በቤተሰብ ደንብ መሠረት በጦርነት ለሞቱት ወታድሮች ቤተቦች ከሚሰጠው ጋር እኩል ነው። (የመከላከያ ሚኒስቴር)

## በጠላት እጅ ተይዞ በሌላ አገር ለተገደለ ቤተሰቦች የሚሰጥ ድጐማ

ይህ የድጐማ መጠን በጦርነት ለሞቱ ወታደሮች ቤተሰቦች ከሚሰጠው ጋር እኩል ነው። (የመከላከያ ሚኒስቴር)

## ጽዮናዊ ባሏ በውጭ አገር ለተገደለባት ሴት የሚሰጥ ድጐማ

የዚህ ድጐማ መጠን እንደ "ኪጽባት ቫኢሪም" መጠን ነው። (በሕጉ መሠረት ለሌላ ድጐማ ባለመብት ባትሆንም)

## የጥገኛ ድጐማ

ይህ ድጐማ የሚሰጠው ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ለጽዮናዊነት እስረኞች የሚሰጠውን ድጐማ ሲቀበል ቆይቶ ለሞተ፣ ባል/ሚስት ወይም ልጆች የሚሰጥ ድጐማ ነው። ይህ ባል/ሚስት የሞተበት፣ የጽዮናዊነት ድጐማው የሚቋረጠው እንደገና የተጋባ እንደሆነ ነው። የድጐማው መጠን ጽዮናዊው እስረኛ ከመሞቱ በፊት ይቀበል ከነበረው ድጐማ 60% ነው። ለጥገኛና ለ"ሺኢሪም" ድጐማ ወይም ለጥገኛና በሥራ ለተጎዳ ለሚሰጥ ድጐማ ባለመብት የሆነ ከሁለቱ ድጐማዎች አንዱን መምረጥ አለበት።

## በሞት ጊዜ የሚከፈል ድጐማ

ይህ ድጐማ የሚከፈለው ጽዮናዊ እስረኛ ባል/ሚስት ለሞተባቸውና ወላጅ ለሞተባቸው ልጆች ነው። ይህም የሚሆነው በሌላ ሥልጣን ሕግ በሞት ጊዜ የሚሰጥ ድጐማ ባለመብት ያልሆነ እንደሆነ ነው።
**የድጐማው ክፍያ መጠን በጥር 2012 - 9089 ሼቄል**

## ለጽዮናዊ እስረኛ አካለ ጎደሎ የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች

ሕክምና፣ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ መታከም፣ ማገገም፣ ሙያ እየተማረ የሚያገግምበት፣ የሰባት ቀን ወጭ ሊሸፍን የሚችል ለመዝናኛ የሚሰጥ ክፍያ፣ የጥቅማጥቅሞች ድጐማ፣ እንደዚሁም በ"አርኖና" ክፍያ ላይ ቅናሽ ያገኛል (እስከ 66%)።

---

* ባል/ሚስት፣ ልጅ፣ ወላጅ፣ ወንድም ወይም እኅት

# ለ"ሐሲዴ ዖላም" የሚሰጥ ድጐማ

"ያድ ቫሼም" የተባለው የመዘከሪያ ድርጅት "ሐሲዴ ዖላም" መሆኑን ዐውቆ ያጸደቀለት ከሆነ፣ ተቀማጭነቱ እስራኤል አገር ከሆነ፣ እንደዚሁም ቤተሰቦቹ (ባል/ሚስት የሌለ ከሆነ፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ደንብ መሠረት ልጁ የሆነ ተቀማጭነቱ እስራኤል አገር የሆነ) እነዚህ የድጐማው ባለመብት ናቸው።

## የካሣው ክፍያ በገንዘብ

በየወሩ የሚከፈለው የገንዘብ መጠን የአማካይ ደመወዝን ያህል ይሆናል። **በጥር ወር 2016 – 9464 ሼቄል።**

## የ"ሀቭራአ" "ስጦታ" እና የ"አርኖና" ቅናሽ

ለ"ሐሲዴ ዖላም" ሚስት/ባል ለመንግሥት ሠራተኛ ክፍያ መጠን ለስምንት ቀን የሚሆን የ"ሀቭራአ" ክፍያ እንደዚሁም ለአርኖና ክፍያ 66% ቅናሽ ይደረግለታል።

# የ"ሻኢሪም" ዋስትና

**አንድ እስራኤላዊ ኗሪ ከሞተና በሕይወት እያለ የ"እርጅና" እና የ"ሻኢሪም" ዋስትና በሕጉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ መሠረት ከነበረው ለሚች ባለቤት እና ልጆች ተቆራጭ ("ቂጽባ") ያስገኛል።**



## "የሻኢሪም" ተቆራጭ

### "የሻኢሪም" ተቆራጭ ባለመብት የሚሆነው ማን ነው?

- **ሚስቱ የሞተችበት** – ባለዋስትናዋ በሞተችበት ወቅት ባል ወይም በሕጋዊ መንገድ ባይጋቡም በሕዝብ የታወቁ ከሆነ፣ ከተጋቡ ቢያንስ አንድ ዓመት ከሆናቸው፣ (ባል 55 ዓመትና ከዚያም በላይ ከሆነው ከተጋቡ ግማሽ ዓመት ከሆናቸው)፣ የሟቿ ልጅ ከእሱ ጋር ካለ ወይም የገቢውን መመዘኛ የሚያሟላ ከሆነ።
- **ባሏ የሞተባት** – በሞተበት ወቅት የሟቹ ሚስት ወይም በሕጋዊ መንገድ ባይጋቡም በሕዝብ የታወቁ ከሆነ፣ ከተጋቡ ቢያንስ አንድ ዓመት ከሆናቸው (ዕድሜዋ 55 እና ከዚያም በላይ ከሆነ ከተጋቡ ግማሽ ዓመት ከሆናቸው) ወይም ልጅ ወልዳለት ከሆነ።
- **ልጅ (ወላጁ የሞተበት)** – ሟቹ በሞተበት ወቅት ልጁ የሆነ፣ (የእንጀራ ልጅ፣ የጉዲፈቻ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ሟቹ ብቻ ያሳድጋቸው የነበር፣ ባለትዳር ከሆኑት በስተቀር) ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሁኔታ በሱ ላይ ያለ ከሆነ።
    - 18 ዓመት ያልሞላው
    - 20 ዓመት ያልሞላውና ትምህርቱን ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በላይ የሚማር ወይም ለማትሪክ ፈተና ለማሟላት የሚማር፣ ወይም የትምህርት ችሎታው የተጓደለ ከሆነና ቢቱዋሕ ሌኡሚ በሚያውቀው ተቋም ውስጥ የሚማር ከሆነ
    - 20 ዓመት ያልሞላውና በሕግ ዕውቅና በተሰጠው ተቋም (ለምሳሌ ዩኒቬርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ የሺቫ፣ ሙያዊ ሥልጠና) ውስጥ የሚማር ከሆነና ቢያንስ በሳምንት ውስጥ ለ20 ሰዓት የሚማር ከሆነ
    - 20 ዓመት ያልሞላውና ውትድርና ከመሄዱ በፊት የውትድርና ተቋም ለዚህ ተብሎ በተቋቋመ ት/ቤት ውስጥ ገብቶ የሚማር ከሆነ
    - 24 ዓመት ያልሞላውና በወታደር አገልግሎት ውስጥ ግዴታዊ አገልግሎት የሚያደርግ (የመብቱ ጊዜ 36 ወራቶች)
    - 24 ዓመት ያልሞላውና በበጎ ፈቃድ ሕዝብን በማገልገል የሚያግዝ (ቢቱዋሕ ሌኡሚ በሚያውቀው ተቋም ውስጥ)
    - 24 ዓመት ያልሞላውና ውትድርና ሆኖ ትምህርት የሚማርና በመማሩ ምክንያት የውትድርና አገልግሎቱ የተላለፈለት፣
    - 21 ዓመት ያልሞላውና ሕዝብን ለማገልገል ዓላማ በበጎ ፈቃድ እስከ 12 ወራት የሚያገለግል (የውትድርና አገልግሎቱ በበጎ አድራጎቱ ምክንያት የተላለፈለት)

> "የሻኢሪም" ተቆራጭ ባለመብት የሚሆኑት ልጆች እናታቸው ሥራ ሠርታ የማታውቅ ከሆነ ነው (ከቤት ሥራ በስተቀር)

### ለ"ሻኢሪም" ተቆራጭ ባለመብት የሚያደርጉ መመዘኛዎች

- ሟቹ በሞተበት ሰዓት የእስራኤል አገር ኗሪ ከሆነ
- ሟቹ "የመመዘኛውን ዘመን" ያሟላ ከሆነ – ከመሞቱ በፊት 12 ወራቶች ዋስትና የነበረው ከሆነ፣ ወይም ከመሞቱ በፊት ከ5 አመት ውስጥ 24 ወራት ዋስትና ያለው ከሆነ፣ ከመሞቱ በፊት ከ10 ዓመት ውስጥ 60 ወራት ዋስትና የነበረው ከሆነ ወይም 144 የዋስትና ወራት ከነበረው፣ ወይም 60 የዋስትና ወራቶች፣ ዋስትና ከሌላቸው ወራቶች ያላነሱ ከሆነ
  የመመዘኛ ወቅት የማይመለከተው – ዋስትና ያለው አዲስ ገቢ ከሆነ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ፣ ዋስትና ያለው 19 ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ፣ ዋስትና ያላት ሴት ከተፋታች ወይም ባሏ ከሞተ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሞተች፣ ዋስትና ያለው ለባለቤቱ ወይም ልጆቹ ዋናው የገቢ ምንጩ ከሆነ፣ ልጆች ያሉት ባለዋስትና ከሞተ፣ የአካለ ጎደሎነት ድጎማ ስትቀበል የነበረች ባለዋስትና
- የዋስትና ክፍያ (ቅጥር ሠራተኛ ላልሆኑና የቤት እመቤት ላልሆነች ሴት)

> ባለዕዳ ሰው ከሞተ የ"ኪጽባት ሻኢሪም"ን ሊያሰርዝ ወይም መጠኑን ሊያስቀንስ ይችላል። (እንደ ዕዳው መጠንና እንዳልተከፈለበት ጊዜ) በዚሁ አጋጣሚ መብቱ በሕግ ይታያል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የስጦታው ባለመብትነት ከፍትሕ አንጻር ይመረመራል።

> ለ"ሻኢሪም" ተቆራጭ ባለመብት መሆንህን ለመመርመር – በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ወደሚገኘው የ"ሻኢሪም" ማስሊያ ግባ።

### በጥር 2016 የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ የክፍያ መጠን

**ሚስት የሞተበት/ባል የሞተባት ያለ ልጅ ዕድሜያቸው ከ40 - 50 ዓመት ለሆኑ 1150 ሼቄል**
**ሚስት የሞተበት/ባል የሞተባት ያለ ልጅ ዕድሜያቸው 50 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆኑ 1531 ሼቄል**
**ሚስት የሞተበት/ባል የሞተባት ዕድሜያቸው 80 ዓመት 1617 ሼቄል**
**ሚስት/ ባል ለሞተበት ከአንድ ልጅ ጋር 2249 ሼቄል**
**ሚስት የሞተበት/ባል የሞተባት ከሁለት ልጆች ጋር 2967 ሼቄል**
**ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ልጅ 718 ሼቄል**

### በመሠታዊው ተቆራጭ ላይ የሚጨመር የቬቴክ ተጨማሪ

የሚች ባለቤት ለ"ቬቴክ" ጭማሪ ባለመብት የሚሆኑት ባለዋስትናው ከመሞቱ በፊት ቢያንስ 11 ዓመትና ከዚያ በላይ ዋስትና የነበረው ከሆነ ነው።

የጭማሪው መጠን፡ ለእያንዳንዱ ዓመት ከ11ኛ ዓመት ጀምሮ ለዋስትናው – ከ"ኪጽባው" 2% ከፍተኛው የጭማሪ መጠን 50%

### የጤንነት ዋስትና አቀናነስ

ከ"ኪጽባት ሻኢሪም" የዋስትና ክፍያ 103 ሼቄል ብቻ ይወርዳል። ይህም የሚሆነው "ኪጽባት ሻኢሪም" ተቀባዩ ዋስትና የሚያስከፍለው ሌላ ገቢ የሌለው እንደሆነ ነው።

## የገቢ ማሟያ

ገቢው አነስተኛ የሆነና "ኪጽባት ሻኢሪም" የሚቀበል፣ የሥራ መመዘኛ የሚያሟላና ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟላ (ለምሳሌ ተሽከርካሪ፣ ንብረት) ለገቢ ማሟያ "ኪጽባ" ባለመብት ይሆናል። ተጨማሪው ገንዘብ የሚሰጠው ተቆራጩ ከዝቅተኛው የገቢ መጠን ጋር እንዲስተካከል ይጠቅማል።

### በጥር 2016 የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ የክፍያ መጠን ከገቢ ማሟያ ጋር

**ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት ያለ ልጅ 2981 ሼቄል**
**ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት ከአንድ ልጅ ጋር 5028 ሼቄል**
**ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት ከሁለትና ዚያ የሚበልጡ ልጆች ጋር 5962 ሼቄል**
**ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት 70 ዓመት የሞላቸውና ነገር ግን 80 ዓመት ያልደረሱ 3042 ሼቄል**
**ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት እና 80 ዓመት የሞላቸው 3151 ሼቄል**

### ለ"ሻኢሪም" ተቆራጭ እና ለገቢ ማሟያ ማመልከት

410/7ב በተሰኘው ፎርም ላይ በጽሑፍ በአቅራቢያ በሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ማመልከት ይቻላል። ይህን የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ ማመልከቻ ሰውየው ከሞተበት ቀን ጀምሮ እስከ 12 ወር ድረስ ማመልከት ይቻላል።

ሟቹ ጡረተኛ ወይም የአካለ ጎደሎ ተቆራጭ ተቀባይ ከነበረ፣ የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ የሚከፈለው ሰውየው በሞተ በወሩ የመጀመሪያ ቀን ነው። ግን ሟቹ ጡረተኛና የአካል ጉዳተኛ ተቆራጭ የማይቀበል ከሆነ የ"ሻኢሪም" ተቆራጭ በሚከተሉት ዓይነት ይከፈላል፡-

- የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጩ የገቢ ማሟያ የሚያስፈልገው ከሆነ ክፍያው በሞተበት ወር 1ኛ ቀን ጀምሮ ይከፈላል
- የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ የገቢ ማሟያ የማያስፈልገው ከሆነ፣ የሞተው በወሩ ከ16 በፊት ከሆነ በሞተበት ወር 1 ይከፈለዋል፣ የሞተው በወሩ ከ15 በኋላ ከሆነ የሚከፈለው በወሩ 1 ቀን ሲሆን በሞተበት ወር ሳይሆን በሚቀጥለው ወር ማለት ነው።

ባለመብቱ ያመለከተው ዘግይቶ ከሆነ ተቆራጩን የሚያገኘው ከ12 ወራት በኋላ ነው።

የማመልከቻውን ፎርም ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ከኢ.ንተርኔት ላይ በማውረድ በፖስታና በፋክስ መላክ ይቻላል።

## ልዩ ድጎማ ("ሺ.ኢ.ሪም")

የእስራኤል ኗሪ ሆኖ ዋስትና ያልገባ ምክንያቱም እስራኤል አገር የመጣ ዕድሜው 60 ዓመት ከሞላ በኋላ ሲሆን ለሱ ሚስትና ልጆች የሻኢ.ሪም ተቆራጭ ይከፈላቸዋል። የልዩ ድጎማው ክፍያ በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ መሠረት ከ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ ክፍያ አያንስም፣ ግን የ"ቬቴክ" ጭማሪ አይኖረውም።

### ለልዩ ድጎማ ባለመብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች ("ሻኢ.ሪም")

ለድጎማ መብት የማይኖረው፣ በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ሕግና ደንብ መሠረት ነው። በገቢው ምርመራ የሚያሟላ፣ ተጨማሪ የገቢ ማሟያ የሚከፈለው እንደ መብቱ ሁኔታ ነው።

## የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ ባለመብት የሆኑና ለሌሎች ተቆራጮች ባለመብት የሆኑ ሰዎች

የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭና ሌላ ተመሳሳይ ተቆራጭ የመቀበል መብት ያለው፣ በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ሕግና በሌሎችም ሕጎች መሠረት ከሁለቱ ተቆራጮች ውስጥ አንዱን መምረጥ አለበት። የጡረታ ድጎማ የሚቀበልና በኋላ ለ“ሻኢ.ሪም” ባለመብት የሆነ፣ “ሻኢ.ሪም” የሚቀበልና ለጡረታ ድጎማ ባለመብት የሆነ፣ ሙሉውን የጡረታ ድጎማ ለመቀበልና የ“ሻኢ.ሪሙ”ን ድጎማ በከፊል እንዲቀበሉ፣ መብታቸው በሕጉ መሠረት ይታያል።

## በውጭ አገር የሚኖር

“ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” ወይም ልዩ “ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” የምትቀበል ከሆነ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ስትነሳ ለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ማሳወቅ አለብህ።

## የ"ሻኢ.ሪም" ስጦታ

ሚስቱ/ ባሏ የሞተበት ዕድሜያቸው 40 ዓመት ያልሞላውና ልጆች የሌሏቸው ከሆነ፣ ሚስቱ የሞተችበት የገቢው መጠን ከፍተኛ ሆኖ “ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” ባለመብት እንዳይሆን ካገደው፣ አንድ ጊዜ የሚከፈል ስጦታ ባለመብት ይሆናሉ አንጂ በየወሩ ለ”ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” ባለመብት አይሆኑም።

የስጦታው መጠን – የ36 ወራት የ”ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” ክፍያ ይሆናል።

## በጋብቻ ጊዜ የሚሰጥ ስጦታ" (እርዳታ)

ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ የሚቀበል፣ ያገባ/ ያገባች አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ የ36 ወራት “ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም”፣ የ”ስጦታ" ባለመብት ይሆናሉ። ስጦታው በሁለት ዓይነት መጠን ይከፈላል፤ አንደኛው ከጋብቻ ቀን በኋላ፣ ከተጋባ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ መብት ይቋረጣል፣ ከልዩ ምክንያቶች በስተቀር ባሏ የሞተባት የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጩን ያለማቋረጥ ትቀበላለች።

ሚስት የሞተበት/ባል የሞተባት ተጋብተው "የሺ.ኢ.ሪም ስጦታ" የተቀበሉ፣ ከተጋቡ በአሥር ዓመት ውስጥ ቢፋቱ፣ እንደገና የ“ሻኢ.ሪም” ተቆራጭ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል።

## የሙያ ማገገሚያ ሚስት ለሞተበት/ባል ለሞተባት

ምርመራ፣ ወደ ሥራ ለመሠማራት የባለሙያተኞች መመሪያና ዕርዳታ፣ የሙያ ትምህርት፣ (የሙያ ስልጠና ) በሚማሩበት ጊዜ የሚከፈል የመተዳደሪያ ገንዘብና ትምህርትን በተመለከተ ልዩ ልዩ ወጭዎችን በመሸፈን ይረዳል።



### ለሙያ ማገገሚያው ባለመብት ማን ነው?

ዕድሜያቸው በሠራተኛ ዕድሜ ክልል ያሉ ሚስቱ የሞተችበት/ባሏ የሞተባትና በ"ሻኢ.ሪም" መምሪያ ወይም በሥራ ጊዜ የተጎዱ ሰዎች መምሪያ የታወቁ ከሆኑና የሙያ ዕውቀት የሌላቸውና ለመተዳደሪያቸው መሥራት የማይችሉ ከሆኑ ወይም ሚስት/ባል ስለሞተባቸው ሙያ ለመቀየር የተገደዱ እንደሆነ ነው። የሙያ ማገገሚያውን ለመቀበል በአቅራቢያ በሚገኘው ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ የማገገሚያ ጸሐፊ ማመልከትና አስፈላጊውን የሙያ ማገገሚያ ፎርም መሙላት ያስፈልጋል።

## ወላጅ ለሞተባቸው የሚሰጥ የመተዳደሪያ ገንዘብ

ወላጅ የሞተበት ልጅ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ከአንደኛ ደረጃ በላይ በትምህርት በመማር ወይም የሙያ ስልጠና ከሆነ እንደ ወላጁ የገቢ መመዘኛ። የትዳር ጓደኛው ከሞተበትና ለ“ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” ተጨማሪ ክፍያ ባለመብት ከሆነ ወላጅ ጋር ለሚኖር ልጅ **የክፍያው መጠን በጥር 2016 ላይ 569 ሼቄል** ነው። አንድ ልጅ ለእሱ ሆነ ለወንድሙ የ"ሻኢ.ሪም" ተቆራጭ ጭማሪን የሚቀበልለት የትዳር ጓደኛው የሞተበት ሰው ከሌለው የሚያገኘው ድጎማ 788 ሼቄል ነው።

የማመልከቻ ፎርም የሆነውን 2910/7ב በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ከኢ.ንተርኔት በማውረድ በፖስታ ቤት ወይም በፋክስ መላክ ይቻላል።

## ስጦታ ባር ሚጽቫ

ወላጅ ለሞተበት የ13 ዓመት ወንድ ልጅ፣ ወላጅ ለሞተባት ሴት ልጅ 12 ዓመት። **ጥር 2016 ዓ.ም. የሚሰጠው የስጦታ መጠን 5,838 ሼቄል ነው።** ይህ ስጦታ ልዩ “ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” የሚቀበሉትን አይመለከትም።

## የማሞቂያ ስጦታ

ዕድሜው ለጡረታ የደረሰና “ኪ.ጽባት ሻኢ.ሪም” የሚቀበል፣ በዓመት አንድ ጊዜ የማሞቂያ ስጦታ የሚከተሉት ሁኔታዎች ያሉት ከሆነ ይከፈለዋል።

- ከሚከተሉት ወራቶች ውስጥ በጥቅምት፣ ኅዳርና ታኅሣሥ በዚያው ዓመት ለጡረታ ማሟያ ገንዘብ ተቀብሎ ከሆነ።
- ከሁለት ወር ባላነሰ፣ በሕጉ መሠረት "ቀዝቃዛ" ተብሎ በተወሰነው አካባቢ የሚኖር ከሆነ።

የሚሰጠው ስጦታ ለመላው ቤተሰብ ነው። **የስጦታው ገንዘብ መጠን በጥር 2016 ዓ.ም. 553 ሼቄል ሲሆን** የሚከፈለውም ወዲያውኑ ከጥቅምት ወር ተቆራጭ ጋር ነው።

## በሞት ጊዜ የሚከፈል ስጦታ

የሞተው ሰው ከሚከተሉት የአንዱ "ኪ.ጽባ" ተቀባይ ከነበረ፣ ጡረታ፣ ሻኢ.ሪም፣ አካለ ጎደሎ፣ የሥራ ጉዳተኛ፣ በሞቱ ጊዜ ሚስቱ/ባሏ ለነበረው አንድ ጊዜ ብቻ የሚከፈለ ተቆራጭ ይከፈለዋል። ባል/ሚስት ከሌለ ለልጁ ("ልጅ" የሚለውን ቀደም ባለው ገጽ ተመልከት) ይከፈለዋል።


ከ1.4.16 ጀምሮ አንድ ልጅ የአካለ ስንኩልነት ድጎማ ይከፈለው ከነበረና በሞት ቢለይ ለወላጆቹ "የሞት ተቆራጭ" "(ማዓናክ ፐቲራ") ይከፈላቸዋል።

**በጥር 2016 የሚከፈለው ገንዘብ መጠን 8757 ሼቄል ነው።**

## በቀብር ጊዜ የሚሰጥ ገንዘብ

በቀብር ሥነ ሥርዓት ጊዜ ለሚያስፈልገው ወጭ መሸፈኛ እንዲሆን የሚከፈለው ለ"ሔቭራት ካዲሻ" ነው።

# የጡረታ ዋስትና



**የጡረታ ዋስትና የታቀደው ለእስራኤል ኗሪዎች በእርጅና ጊዜ ቋሚ ገቢ ለማስገኘት ነው። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ለ“ገቢ ማሟያ ጭማሪ” ባለመብት ናቸው።**

## የጡረታ ዋስትና

### ባለመብት ማን ነው?

በሕጉ መሠረት የጡረታ ኪጽባ የሚከፈለው፣ የእስራኤል ኗሪ ለሆነ በእስራኤል ለተወልደ ወይም በመጀመሪያ ጊዜ እስራኤል የገባው ዕድሜው 62 ዓመት ሳይሞላው ከሆነ ነው። ዕድሜው 62 ዓመት ከሞላው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እስራኤል አገር ከገባ፣ በተለዩ ሁኔታዎች ልዩ ኪጽቫ ይከፈለዋል። (የሚከተለውን ተመልከት)

የእስራኤል አገር ኗሪ የሆነ ሌላ አገር ሄዶ የሚኖር ከሆነ እስራኤል ውስጥ መኖር ቢተውም የእርጅና ዋስትና ሊያገኝ ይችላል። የእስራኤል ኗሪ የሆነ በእስራኤል ውስጥ የእርጅና ተቆራጭ ማግኘት ከጀመረ በኋላ ውጭ አገር ሂዶ መኖር ቢጀምር፣ እስራኤል አገር መኖሩን ቢተውም የእርጅና ተቆራጩን መቀበል ይቀጥላል።

### እስራኤል አገር ኗሪ የሆነች ሴት ለተቆራጩ ባለመብት ትሆናለች፣ እላይ ከተጻፈው በተጨማሪ እሷ ከሚከተሉት ውስጥ አንዷ ከሆነች ነው፣

- ያላገባች ሴት – ልጃገረድ፣ የፈታች ሴት ወይም ባሏ የሞተባት ("ኪጽቫት ሺኢሪም" ከምትቀበል ሴት በስተቀርና ከቤት እመቤትነት በስተቀር ሠርታ የማታውቅ)
- የቤት እመቤት ከመሆን አልፋ፣ ሥራ የምትሠራ ባለትዳር ሴት (በደመወዝ ተቀጥራ የምትሠራ ወይም የራሷ ድርጅት ያላት)
- ባለትዳር ሴት ባሏ በቢቱዋሕ ሌኡሚ የጡረታ ወይም የ"ሺኢሪም" ዋስትና የሌለው (በዕድሜው ምክንያት ወይም የእስራኤል አገር ኗሪ ባለመሆኑ) ቅጥረኛ ወይም የግል ሥራ ባይኖራትም
- "አጉና" – ማለትም ባሏ ሊፈታት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የጠፋና በሕይወት ይኑር አይኑር ያልታወቀ፣ (ያገባች ሴት ሁለት ዓመት አካባቢ ባሏ ዱካው የጠፋ ወይም ሁለት ዓመት ያለፈቃዷ በውጭ አገር የሚገኝና "መዞኖት" የማይሰጣት) ተቀጥራ ወይም በግሏ የማትሠራ፣
- የቤት እመቤት (ባለትዳር ሴት የቤት እመቤት ከመሆን በስተቀር ሥራ የማትሠራ ባሏ ዋስትና ያለው) ባሏ የሞተባትና ከሴት እመቤትነት በስተቀር ሥራ ሠርታ የማታውቅ “ኪጽባት ሻኢሪም” ወይም "ኪጽባት ትሉይም"፣ ከታህሳስ 31 1930 በኋላ የተወለዱ ለጡረታ ዋስትና ባለመብት ሊሆኑ ይችላሉ። ከጥር 1 1930 በፊት የተወለዱ ከጥር 2013 ጀምሮ የጡረታ ዋስትና ሊቀበሉ ይችላሉ።

### የባለመብትነት ሁኔታዎች

1. **ለ"ጡረታ ገንዘብ ባለመብት ለሚያደርገው ዕድሜ" መድረስ**

   ለጡረታ ገንዘብ ባለመብት የሚያደርገውን ዕድሜ የሚወስኑ ሁለት ቀኖች አሉ፤

   . **የጡረታ ዕድሜ፣ (መብቱ በገቢው መሠረት የሚወሰንበት ዕድሜ)** – ዕድሜህ/ሽ ለጡረታ ባለመብት የሚያደርግህ/ሽ ከሥራ የምታገኘው ገቢ ለአንድ ሰው ብቻ ከ5394 ሼቄል ያልበለጠ፣ ወይም በወር 7193 ሼቄል ለሁለት ሰው፣ ሌላ የገቢ ምንጭህ ለአንድ ሰው ከ16182 ያልበለጡ እንድሆን፣ ለሁለት ሰው ከ21579 ሼቄል ያልበለጡ እንደሆነ (በጥር ወር 2016) ነው።

   **ከጡረታ የሚገኝ ገቢ እንደ ገቢ አይቆጠርም።**
   **የጡረታ ዕድሜ ለወንዶች** – 67 ዓመት ነው።
   **የጡረታ ዕድሜ ለሴቶች** – በፓርላማ ውሳኔ መሠረት የሴቶች የጡረታ ዕድሜ ከ1950 እስከ 1954 ታኅሣሥ ለተወለዱ 62 ዓመት ነው።
   ሌላ ውሳኔ እስካልተሰጠ ድረስ ከ2017 ጀምሮ የሴቶች የጡረታ ዕድሜ ደረጃ በደረጃ እንደተወለዱበት ቀን ከ62 እስከ 64 ይጨምራል።

   . **ለጡረታ ገንዘብ ባለመብት የሚያደርግ ዕድሜ** – የገቢህን/ሽን መጠን ሳይመለከት የጡረታ ባለመብት የሚያደርግህ/ሽ ዕድሜ ነው።

**ወንዶችን ለጡረታ ገንዘብ ባለመብት የሚያደርገው ዕድሜ** – 70 ዓመት ነው።

### ሴቶችን ለጡረታ ባለመብት የሚያደርገው ዕድሜ (ሌላ ውሳኔ እስካልተወሰነ ድረስ)

| የትውልድ ቀን | | ለጡረታ ባለመብት የሚያደርገው ዕድሜ |
|---|---|---|
| ከ...ቀን | እስከ...ቀን | |
| - | ሰኔ – 39 | 65 |
| ሐምሌ – 39 | ነሐሴ – 39 | 65 ዓመትና 4 ወር |
| መስከረም – 39 | ሚያዚያ – 40 | 65 ዓመትና 8 ወር |
| ግንቦት | ታኅሣሥ – 40 | 66 |
| ጥር – 41 | ነሐሴ – 41 | 66 ዓመትና 4 ወር |
| መስከረም – 41 | ሚያዚያ – 42 | 66 ዓመትና 8 ወር |
| ግንቦት – 42 | ታኅሣሥ – 44 | 67 |
| ጥር – 45 | ነሐሴ – 45 | 67 ዓመትና 4 ወር |
| መስከረም – 45 | ሚያዚያ – 46 | 67 ዓመትና 8 ወር |
| ግንቦት – 46 | ታኅሣሥ – 46 | 68 |
| ጥር – 47 | ነሐሴ – 47 | 68 ዓመትና 4 ወር |
| መስከረም – 47 | ሚያዚያ – 48 | 68 ዓመትና 8 ወር |
| ግንቦት – 48 | ታኅሣሥ – 48 | 69 |
| ጥር – 49 | ነሐሴ – 49 | 69 ዓመትና 4 ወር |
| መስከረም – 49 | ሚያዚያ – 50 | 69 ዓመትና 8 ወር |
| ግንቦት – 50 | ወዘተ. | 70 |

2. **"ብቁ የመሆን ወቅት" ማሟያ**

   ለጡረታ ባለመብት የሚያደርጉት ከ10 የመጨረሻ የዋስትና ዓመታት ውስጥ 60ዎቹ ወራቶች የጡረታ ባለመብት ያደርጋሉ ወይም 144 የዋስትና ወራቶች ወይም 60 የዋስትና ወራቶች፣ ይህም የሚሆነው የዋስትና ወራቶች ዋስትና ከሌላቸው ወራቶች ያላነሱ እንደሆነ ነው።

3. **የዋስትና ገንዘብ አከፋፈል (ተቀጣሪ ላልሆኑ ባለዋስትናዎች፣ የቤት እመቤት ላልሆነች ሴት)**

> › የዋስትና ገንዘብ ዕዳ ያለበት ዕዳውን እስከሚከፍል ድረስ የሚቀበለው ገንዘብ ይቋረጥበታል ወይም እንደ ዕዳው መጠንና ያልከፈለበት ጊዜ ታስቦ ገንዘቡ ተቀንሶ ይሰጠዋል።

### መሠረታዊው የጡረታ ተቆራጭ ገንዘብ መጠን በጥር 2016 (በሼቄል)

**በባለመብትነት ሁኔታዎች መሠረት ለመሠረታዊው ተቆራጭ ወደፊት የሚዘረዘሩ ጭማሪዎች ይጨመራሉ፣**

**ብቻውን ለሚኖር – 1531**
**ለጥንድ – 2301**
**ብቻውን ለሚኖርና ዕድሜው 80 እና ከዚያ በላይ ለሆነ – 1617**
**ለጥንድ እና ዕድሜያቸው 80 እና ከዚያ በላይ ለሆኑት – 2387**
**ለጥንድ ከአንድ ልጅ ጋር – 2785**
**ለጥንድ ከሁለት ወይም ከዚያ ከሚበልጡ ልጆች ጋር – 3269**
**ብቻውን የሚኖር ከአንድ ልጅ ጋር – 2015**
**ብቻውን የሚኖር ከሁለት ወይም ከዚያ ከሚበልጡ ልጆች ጋር – 2499**
**ከተቆራጩ ላይ ለጤና ዋስትና ክፍያ ለአንድ ሰው 196 ሼቄል፣ ለጥንድ 283 ሼቄል (ጥር 2016)**

### የተቆራጩ ተጨማሪ ክፍያ

**የ“ቬቴክ” ጭማሪ** –የዋስትናው ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ ከሆነ፣ የመጀመሪያዎቹ 10 ዓመታት ኪጽባ 2% ቬቴክ ይታሰብለታል።
ከፍተኛው የቬቴክ ተጨማሪ – 50%።
ለቤት እመቤት ይህ ተጨማሪ አይሰጣትም።

**የ"ድህያት ኪጽባ" – ተጨማሪ –** የኪጽባው 5%፣ ከሥራ በሚያገኘው ደመወዝ ምክንያት፣ በየዓመቱ ለሚሰጠው ኪጽባ ባለመብት ያልነበረ፣ ለጡረታ መብት እስከሚደርስ ድረስ፣ (የወንዶች ዕድሜ – 70 ዓመትና የሴቶች – ሰንጠረዡን ይመልከቱ)

**የጥገኞች ተጨማሪ –** የሚከፈለው ተቆራጭ ከሚቀበለው ሰው፣ ባል ወይ ሚስት ሲሆን እነሱም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቆራጭ የማይቀበሉ ሲሆኑ፣ ለመጀመሪያዎች ሁለት የ"ኪጽባ" ተቀባይ ልጆች ይከፈላል። ለቤት እመቤት ለጥገኞች ተብሎ ተጨማሪ አይሰጣትም።

- **ባል –** ተቆራጩን የምትቀበለው ባል የእስራኤል አገር ኗሪ፣ ቢያንስ ካገባት አንድ ዓመት የሆነው ወይም ሕጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ አብሯት የሚኖር፣ ዕድሜው 70 ዓመት የሆነው ወይም ዕድሜው 50 ዓመት ሞልቶት የገቢ መመዘኛ መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ።
- **ሚስት –** ተቆራጭ የሚቀበለው ሰው ሚስት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የምታሟላ ከሆነ፣ የእስራኤል አገር ኗሪ ከሆነች፣ ካገባችው ቢያንስ አንድ ዓመት ከሆነ ወይም ሕጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ አብራው ከኖረች፣ ወይም ልጅ ወልዳለት ከሆነ፣ ዕድሜዋ 45 የሞላት ከሆነ ወይም ከእሷ ጋር የእሱ ልጅ ካለ፣ ዕድሜዋ ለጡረታ የደረሰ ወይም የገቢ መመዘኛውን የምታሟላ ከሆነ።
- **ልጅ –** ወንድ ወይም ሴት (የእንጀራ ልጅ፣ ጉዲፈቻ ልጅ/የማደጎ ልጅ፣ የልጅ ልጅ መተዳደሪያው ጡረታ ከሚቀበለው ሰው ጋር ከሆነ ካገቡ ወጣቶች በስተቀር) ከሚከተሉት አንዱን ከሆነ፣
  - ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላው
  - ዕድሜው 20 ዓመት ያልሞላውና ትምህርቱን ከአንደኛ ደረጃ በላይ የሚማር ወይም የማትሪክ ፈተናውን ለማሟላት የሚማር ወይም ትምህርት ለመማር ጉድለት ያለበት ሆኖ የሚገኘው ቢቱዋሕ ሌኡሚ በሚያውቀው ተቋም ውስጥ ከሆነ።
  - ዕድሜው 20 ዓመት ያልሞላው ለውትድርና ግዴታ ከመሄዱ በፊት፣ በውትድርና ተቋም ውስጥ በመርዳት የሚያገለግል ከሆነና ተቋሙ ለዚህ ጉዳይ የታወቀ ከሆነ።
  - ዕድሜው 24 ዓመት ያልሞላውና በውትድርና ውስጥ መደበኛ አገልግሎት የሚሰጥ (የባለመብትነት ወቅቶች 36 ወራቶች ናቸው)።
  - ዕድሜው 24 ዓመት ያልሞላውና በበጎ ፈቃደኝነት በሺሩት ሌኡሚ የኒያገለግል (የሚያለግልበት ተቋም በቢቱዋሕ ሌኡሚ የታወቀ ከሆነ)።
  - ዕድሜው 24 ዓመት ያልሞላውና በ"ዐቱዳ" የሚማርና የውትድርና አገልግሎት ዘመኑ በትምህርቱ ምክንያት የተራዘመለት ከሆነ።
  - ዕድሜው 21 ዓመት ያልሞላውና በበጎ ፈቃደኝነት በሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች እስከ 12 ወራቶች የሚያገለግል፣ የውትድርና አገልግሎት ጊዜው በዚህ የበጎ አድራጎት ምክንያት የተራዘመለት ከሆነ።

> ❯ ለጡረታ ባለመብት መሆንህንና በየትኛው ዕድሜ ላይ ባለመብት መሆንህን ለማወቅ ድረ ገጹ ላይ ወደሚገኘው "የጡረታ ማስሊያ" ግባ።

## ለጡረታ ተቆራጭ ማመልከት

"ለጡረታ ኪጽባ ባለመብት" ለሚያደርገው ዕድሜ የተቃረበ ሁሉ ፎርም 480/לב (ዕድሜው ለዚህ ለተቃረበ ሁሉ በፖስታ ቤት ይላክለታል) ሞልቶ በአቅራቢያው በሚገኘው ቢቱዋሕ ማመልከት ይችላል። ይህን ፎርም በቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማግኘት ሲቻል፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ከኢንተርኔት ማውረድና ሞልቶ በፖስታ ቤትና በፋክስ መላክም ይቻላል።

ወሩ በገባ 1 ቀን አንስቶ እስከ 15 ቀን ድረስ ለጡረታ ተቆራጭ ባለመብት የሆነ፣ የጡረታ ባለመብት ካደረገው ከወሩ 1 ቀን ጀምሮ "ኪጽባው" ይከፈለዋል።

በወሩ 16 ቀን ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ የጡረታ ባለመብት ከሆነ፣ "ኪጽባው" የሚከፈለው ባለመብት ከአደረገው ወር በኋላ፣ ከ1 ቀን ጀምሮ ነው። ለገቢ ማሟያ ባለመብት ከሆነ፣ የጡረታው ገንዘብ በዚያው ወር 1 ቀን ጀምሮ ይከፈለዋል። (ባ1eመብት የሆነው በወሩ 15 ቀን በኋላ ቢሆንም)

"የኪጽባው" ባለመብት ካደረገው ወር ጀምሮ፣ ማመልከቻው ከ12 ወር በኋላ የተመለከተ ከሆነ፣ ያልተመለከተባቸውን ወራት ክፍያ፣ ከ12 ወራት በኋላ ለመክፈል ቢቱዋሕ ሌኡሚ ሥልጣን አለው። ማመልከቻውን ዕድሜው ለጡረታ ከደረሰ በኋላ ያመለከተ ከሆነ (ለወንዶች 70 ዓመት ለሴቶች ቀደም ብሎ በተገለጸው ላይ መመልከት ይቻላል) ያለፈውን ክፍያ ረዘም ባለ ጊዜ ክፍያ ሊሰጣቸው ይችላል። ለማንኛውም በጡረታ ዕድሜና በባለመብትነት ዕድሜ፣ ባለመብትነቱ

> ❯ የጡረታ ገንዘብ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚቀበል ጡረተኛ ከ6 ወር በላይ ወደ ውጭ አገር ለመሄድና ለመቆየት ካሰበ፣ ተከታይ መብቱ እንዲታይለት ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ማሳወቅ አለበት።

# የገቢ ማሟያ

ገቢው ዝቅተኛ የሆነ የጡረታ ገንዘብ የሚቀበልና የገቢውን ፈተና መመዘኛ የሚያሟላ፣ ለተጨማሪ የገቢ ማሟያ ባለመብት ይሆናል። ጭማሪው የሚያሟላው ዝቅተኛውን የተቆራጭ መጠን ነው።

## የጡረታ ተቆራጭ የገንዘብ መጠን ከገቢ ማሟያ ጋር በጥር ወር 2016 (በሼቄል)

**ለአንድ ሰው – 2,981**
**ዕድሜው 70 ዓመት ለሞላውና 80 ዓመት ገና ላልሆነው – 3,042**
**ዕድሜው 80 ዓመት ለሆነው አንድ ሰው – 3,151**
**ለጥንድ – 4706**
**ተቆራጩን የሚቀበል ጥንድ 70 ዓመት ከሆናቸው – 4,808**
**ተቆራጩን የሚቀበል ጥንድ 80 ዓመት ከሆናቸው – 4,980**
**ለጥንድ ከአንድ ልጅ ጋር – 5,640**
**ለጥንድ ከሁለትና ከዚያ በላይ ልጆች ጋር – 6,574**
**ለአንድ ሰው ከአንድ ልጅ ጋር – 5,028**
**ለአንድ ሰው ከሁለትና ከዚያ በላይ ልጆች ጋር – 5,962**
**ከጡረታው ገንዘብ ላይ የጤና ዋስትና 103 ሼቄል ይቀነሳል።**
የጡረታ ገንዘብ ከገቢ ማሟያ ጋር የሚቀበል ወደ ውጭ አገር በሄደበት ጊዜ፣ ለገቢ ማሟያው ባለመብት መሆኑን ማጣራት አለበት።

## ለተጨማሪ የገቢ ማሟያ ማመልከቻ

ለጡረታ ባለመብትነት ማመልከቻ በሚገባበት ጊዜ በፎርም 430/לב ለገቢ ማሟያው ማመልከት ይቻላል። ወይም በሌላ ጊዜ፣ ገቢው የገቢ ማሟያ እስከሚያስፈልገው ድረስ ያነሰ እንደሆነ በዚህ ጊዜ ማመልከት ይቻላል።

ተጨማሪ የገቢ ማሟያ ማመልከቻ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ሁልጊዜ በየወሩ ባለመብት የሆነበት ኪጽባ በሚከፈልበት ጊዜ ይከፈለዋል። (ሳይፈረድ፣ ተጨማሪው የገቢ ማሟያ የተከፈለው ከሆነ፣ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ከሚከፍለው ድጐማ ገንዘብ ላይ በመቀነስ የከፈለውን ገንዘብ የማስመለስ መብት አለው።)

# ልዩ ድጐማ (ጡረታ)

ይህ ልዩ የጡረታ ድጐማ የሚከፈለው ዕድሜው 62 ከሆነው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እስራኤል አገር የገባ እንደሆነ ነው። ያገባች ሴት ከባሏ ጋር የምትኖር ለዚህ ልዩ ድጐማ ባለመብት አይደለችም።ባለመብት የምትሆነው ዕድሜዋ "ለጡረታ ገንዘብ ባለመብት" ለመሆን የደረሰ እንደሆነ ነው።

## ድጐማ ባለመብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች (ጡረታ)

ቀደም ባለው ገጽ እንደተገለጸው ለጡረታ መብት የሚያበቃው ዕድሜ፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ መሠረት የኪጽባ መብት አለማግኘት፣ የገቢ መመዘኛውን አሟልቶ መገኘት፣

ይህን ልዩ ድጐማ የሚቀበል ወደ ውጭ በሚሄድበት ጊዜ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

## የልዩ ድጐማው መጠን

የልዩ ድጐማው መጠን ለአንድ ሰው፣ ባለ ትዳርና ልጆች ላሉት፣ በቢቱዋ ሌኡሚ ሕግ መሠረት ከጡረታው ከሚከፈለው ጋር አንድ ነው፣ ግን የ"ቬቴክ" ተጨማሪና ተጨማሪ "ድህያ ኪጽባ" አይከፈልም።

## ለልዩ ድጐማውና ለተጨማሪ የገቢ ማሟያ ማመልከት

በአቅራቢያ በሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በፎርም 4501/לב ማመልከት ያስፈልጋል። ልዩ ድጐማ (ጡረታ) ማመልከቻ በገባበት ወር 1 ቀን ጀምሮ ይከፈላል። (ድጐማው ማመልከቻ ከመግባቱ በፊት ለነበረው ወር አይከፈልም)።

# በክረምት ጊዜ ለማሞቂያ የሚሰጥ ገንዘብ

በዓመት አንድ ጊዜ ለማሞቂያ ተብሎ ጡረታ ለሚቀበል ሰው ገንዘብ ይከፈለዋል፣ ይህም ገንዘብ የሚከፈለው ከታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች አሟልቶ ከተገኘ ነው።

1. ጡረታ የሚቀበለው ሰው ተጨማሪ የገቢ ማሟያ በዚያው ዓመት ጥቅምት፣ ኅዳር ወይም ታኅሣሥ ውስጥ በአንዱ የተቀበለ እንደሆነ ነው። ወይም የጡረታው ተቆራጭ ከአካለ ስንኩልነት ተቆራጭ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እንደሆነ ነው።
2. የሚኖረው በሕጉ መሠረት "ቀዝቃዛ" ተብሎ በታወቀው አካባቢ ቢያንስ ለሁለት ወር የሚኖር።

የሚሰጠው ገንዘብ ለመላው ቤተሰብ ነው። **የገንዘቡ መጠን በጥር ወር 2016 ዓ.ም. 553 ሼቄል** ነው። የሚከፈለው ወዲያው ሲሆን ከጥቅምት ወር የጡረታ ክፍያ ጋር ይሆናል።

# በሞት ጊዜ የሚሰጥ ገንዘብ

የጡረታ ገንዘብ ሲቀበል የነበረው ሟች፣ ባል/ሚስት – አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ክፍያ፣ ባል/ሚስት ለሌለ ይህ ክፍያ ለልጅ (ልጅ የሚለውን አባባል ቀደም ብሎ ስለተገለጸ ተመልከት) ይሰጣል።
**የክፍያው መጠን በጥር ወር 2016 ዓ.ም. 8,757 ሼቄል** ነው። (ጡረታ ሲቀበል የነበረውና የሞተው፣ የገቢ ማሟያ ተከፍሎትም ቢሆን)።

ጡረታ እስከ የገቢ ማሟያ የሚቀበለው ሰው ባል/ሚስት ከሞተ፣ ይህ በሞት ጊዜ የሚሰጠው ገንዘብ የሚከፈለው ወዲያውኑ ነው። ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልግም።

ባልና ሚስቱ በትንሽ ጊዜ ልዩነ ከሞቱ፣ ይህ ገንዘብ ሟቾቹን ሲንባከባቸው ለነበረው ይከፈላል።

# የእንክብካቤ ዋስትና ("ቢቱዋሕ ሲዑድ")



ቢቱዋህ ሌኡሚ ከ“ረቫኻ” መሥሪያ ቤት፣ ከጤና ጥበቃና “ኩፓት ሆሊም” ጋር በመተባበር የእንክብካቤ ዋስትና የተባለውን ሕግ ያንቀሳቅሳል። በሕጉ መሠረት ይህ የእንክብካቤ እርዳታ የሚሰጠው ዕድሜያቸው ለጡረታ የደረሰና በቤታቸው እየኖሩ ለቀን ቀን እንቅስቃሴያቸው የሌላ ሰው እርዳታ የሚያስፈልጋቸው (ለመልበስ፣ ለመታጠብ፣ ለመመገብ ወይም ቤት ውስጥ ለመሄድ) እንደዚሁም ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ሽማግሌዎች፣ ለእነሱና ለአካባቢያቸው ዋስትና ሲባል ነው።

## የሽማግሌዎችና ባልቴቶች እንክብካቤ ድጐማ

የሽማግሌዎችና ባልቴቶች እንክብካቤ ድጐማ የአገልግሎት ድጐማ ነው። ለዚህ ድጐማ ባለመብት ለሆነው ግለሰብ፣ ለየዕለት እንቅስቃሴውና በቤት ውስጥ ሥራ እንዲረዳው የእንክብካቤ ድጐማ ይሰጠዋል።

ድጐማውን በገንዘብ መልክ እንዴት መቀበል እንደሚቻል ወደፊት የሚቀርቡትን ነገሮች ተመልከት።

### ለእንብክብካቤ ድጐማ ባለ መብት የሚሆነው ማን ነው?

የእስራኤል አገር ኗሪ የሆነና ዕድሜው ለጡረታ የደረሰ፣ (ስለ ጡረታ የተጻፈውን ምዕራፍ ተመልከት) ለየቀኑ እንቅስቃሴውና ለጥበቃ የሌላ ሰው ዕርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ነው።

### ለእንክብካቤ ድጐማ ባለመብት የሚያደርጉ ሁኔታዎች፣

- ዕድሜ – ከላይ እንደተጠቀሰው።
- ከኅብረተሰቡ ጋር የሚኖር – እንክብካቤ በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ ያልገባ።
- የገቢ ፈተናዎችን የሚያሟላ – ለእንክብካቤ ድጐማ ባለቤት የሚያደርገው የገቢ ፈተናው ነው።
- ባለ ዋስትናው የልዩ አገልግሎት ድጐማ ከቢቱዋ ሌኡሚ የማይቀበል ከሆነ (በሥራ ላይ በደረሰበት አደጋ አካለ ጎደሎ ለሆኑት የሚሰጥ፣ አጠቃላይ ለአካለ ጎደሎ የሚሰጥ)፣ ለግል እንክብካቤ ተብሎ ድጐማ የማይቀበል ወይም ለጥበቃ ተብሉ ከመንግሥት የማይቀበል (እንዲህ ዓይነት ድጐማ የሚቀበል በቢቱዋሕ ሌኡሚ የእንክብካቤ ሕግ መሠረት ለእንክብካቤ በሚሰጠው ድጐማና ለጥበቃ ከመንግሥት በሚሰጠው ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለበት)።
- ባለዋስትናው ለየዕለት እንቅስቃሴው፣ በከፍተኛ ደረጃ የሌላ ሰው እንክብካቤና ዕርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ (ለመልበስ፣ ለመታጠብ፣ ለመመገብ፣ በሚጸጸዳበት ጊዜ ለመርዳት፣ ቤት ውስጥ ለመሄድ እንዲሆም የመሳሰሉትን) ወይም ባለዋስትናው ለራሱና በአካባቢው ዋስትና ሲባል ጥበቃ የሚያስፈልገው ሲሆን ነው።

> የሽማግሌው/ባልቴቷ የሌላ ሰው እንክብካቤ የመፈለግ መጠን፣ የሚያስፈልገው የጥበቃ አስፈላጊነት መጠን፣ ባለሙያ ሰው በሽማግሌው/ባልቴቷ ቤት በሚያደርገው ምርመራ መሠረት፣ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ይወስናል። (ነርስ፣ ፊዚዮትራፒስት፣ “መራፔ በኢሱክ”)። የሥራ አቅሙ ውሱን የሚሆነው ለጊዜው ከሆነ፣ ለጊዜው የእንክብካቤ ድጐማ ይሰጠዋል። ዕድሜያቸው 90 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆኑ አረጋዊያን፣ ምርመራ የሚደረግላቸው በ”ጊሪያትሪ” ወይም በ”ፊስኮጌሪያትሪ” አማካኝነት ነው።

> ለሽማግሌዎች/ባልቴቶች እንክብካቤ ድጐማ ባለመብት መሆንህን ለማወቅ – ቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ የሚገኘውን የእንክብካቤ ("ሲዑድ") ማስሊያ ተጠቀም።

### ለሽማግሌዎች/ባልቴቶች እንክብካቤ ድጐማ ባለመብት ለሆኑት የሚሰጠው አገልግሎት ምን ዓይነት ነው?

በእንክብካቤ ዋስትና ደንብ መሠረት ለባለመብቱ፣ በዕለት ዕለት ተግባሩ የሚረዱትና እንክብካቤ የሚያደርጉለት፣ የቤት ውስጥ ሥራም የሚሠሩለት፣ እንደ ሽማግሌው/ባልቴቷ ችግር ሁኔታና የአካባቢው እንክብካቤን በተመለከተ በባለሙያ ኮሚቴ ታይቶ ይመደባሉ።

ከነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ ለእንክብካቤው ድጐማ ባለቤት አገልግሎቶች ይመረጣሉ፣ እነዚህ አገልግሎቶች በሚኖርበት አካባቢ ከተገኙ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

- በቤት ውስጥ ለየዕለት ድርጊት የምትንከባከብና የምትረዳ (“መታፔሌት”) (ለመልበስ፣ ለመታጠብ፣ ለመመገብ፣ በሚጸዳዳበት/በምትጸዳዳበት ጊዜ ለመርዳት፣ ቤት ውስጥ እንዲሄድ/እንድትሄድ መርዳት) የቤት ውስጥ ሥራ መሥራትና ሽማግሌውን/ባልቴቷን መጠበቅ።
- ለአንድ ጊዜ ጥቅም ብቻ የሚውሉ ፈሳሽ የመምጠጥ ችሎታ ያላቸውን ነገሮች ማቅረብ
- በሽማግሌዎች/ባልቴቶች መዋያ ቦታ መንከባከብ
- የልብስ ማጠብ አገልግሎት መስጠት
- በችግር ጊዜ የ“ድረሱልኝ” ጥሪ የሚያስተላልፍ መሣሪያ

### የድጐማው መጠን

የእንክብካቤ ድጐማ የሚሰጠው በሦስት ደረጃ ነው፣

- 91% ድጐማ (9.75 ሰዓቶች በሳምንት) በከፍተኛ ሁኔታ በዕለት ኑሮውና የየቀን እንቅስቃሴው የሰው ዕርዳታና ጥበቃ በጣም ለሚያስፈልገው ሽማግሌ/ለሚያስፈልጋት ባልቴት የሚሰጥ
- 150% ድጐማ (16 ሰዓቶች በሳምንት) ይህ ድጐማ የሚሰጠው ሽማግሌውን/ባልቴቷ ለየቀን ኑሮና ጥበቃ የሰው ዕርዳታ ቀኑን ሙሉ እጅግ በጣም የሚያስፈልጋቸው እንደሆነ ነው። እስራኤላዊ ተንከባካቢ የቀጠሩ ሽማግሌ/ባልቴት ተጨማሪ 3 የእንክብካቤ ሰዓት ይሰጣቸዋል። ይህም የሚሆነው የውጭ ዜጋ ለመቅጠር የሚያስችል ፈቃድ ከሌላቸው ነው።
- 168% ድጐማ (18 ሰዓቶች በሳምንት) የቀን ቀን እንቅስቃሴውን ራሱን ችሎ ለማከናወን የማይችልና ይህን የዕለት ዕለት ተግባር ለማከናወን 24 ሰዓት የሰው እርዳታና ጥበቃ እጅግ በጣም የሚያስፈልጋቸው ሽማግሌ/ባልቴት ይህ እርዳታ ይሰጣቸዋል። እስራኤላዊ ተንከባካቢ የቀጠሩ ሽማግሌ/ባልቴት ተጨማሪ 4 የእንክብካቤ ሰዓት ይሰጣቸዋል። ይህም የሚሆነው የውጭ ዜጋ ለመቅጠር የሚያስችል ፈቃድ ከሌላቸው ወይም ፈቃዱ "በይደር የቆየ" ከሆነ ነው።

### ለሽማግሌዎች/ባልቴቶች እንክብካቤ ድጐማ እንዴት ማመልከት ይቻላል?

የጡረተኛን የእንክብካቤ ድጐማ ለመቀበል ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀውን ፎርም (2600/7ב) በትክክል መሙላትና በአቅራቢያ በሚገኘው ቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማመልከቻ ለሚቀበለው ሠራተኛ መስጠት ያስፈልጋል። ይህን ፎርም በማንኛውም የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ማግኘት ይቻላል። እንዲሁም በተጨማሪ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ በኢንተርኔት ማውረድና በፖስታ ቤትና በፋክስ መላክ ይቻላል።

ፎርሙን ለመሙላት የተቸገረ ሰው፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ማመልከቻ ተቀባይ ሠራተኛ አማካኝነት ወይም በሽማግሌ/ባልቴት ምክር ሰጭ መምሪያ ክፍል የሚሠሩ ሁሉ እርዳታ ሊያገኝ ይችላል። ከዚሁ ከማመልከቻው ፎርም ጋር የገቢውን መጠን የሚያረጋግጥ መረጃና ስለ ጤንነቱ የሚገልጽ ከግል የሕክምና ሰነዱ የተወሰደና ሐኪም የፈረመበት፣ ሆስፒታል ተኝቶ የነበር ከሆነ ይህንኑ የሚገልጽ፣ ማስረጃ ማያያዝ አለበት። ይህን ማመልከቻ አመልካቹ ከፈረመበት በኋላ አመልካቹን ሊወክል የሚችል ሌላ ሰው ሊያቀርበው ይችላል። (ቤተሰብ፣ “አፖትሮፑስ”፣ የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ፣ ነርስ)

## የእብክብካቤ ድጐማ የገንዘብ መጠን

የእንክብካቤ ዋስትና ባለመብት የሆነው፣ ሁልጊዜ አብሮት የሚውል ተንከባካቢ ቀጥሮ ከሆነ፣ ከ1.3.2014 ጀምሮ የእንክብካቤ ድጐማውን አገልግሎት በመቀበል ፋንታ ገንዘብ በመቀበል ሊለውጥ ይችላል። የእንክብካቤ ድጐማውን በገንዘብ መልክ መቀበል የሚቻለው አብሮት የሚውል ተንከባካቢ የቤተሰብ አባል ካልሆነ፣ እንክብካቤው በሳምንት ለ6 ቀን ሆኖ በቀን ውስጥ ለብዙ ሰዓቶች ከሆነና ቅጥሩ በጽሑፍ በተደገፈ ስምምነት ከሆነ ብቻ ነው።


### የገንዘቡ መጠን በጥር ወር 2016 (የውጭ አገር ሠራተኛ ለሚያሠራ)

| የተወሰነው የድጐማ መጠን | የድጐማው መጠን በገንዘብ |
|---|---|
| 91% | 1,594 ₪ |
| 45.5% | 797 ₪ |
| 150% | 2,627 ₪ |
| 75% | 1,314 ₪ |
| 168% | 2,942 ₪ |
| 84% | 1,471 ₪ |

### ለድጐማው ገንዘብ ማመልከት

በፎርሙ ጀርባ ላይ “የእንክብካቤ ድጐማውን በአገልግሎት ፋንታ በገንዘብ መቀበል (2655)” በማለት ማቅረብ ይቻላል። ይህን ፎርም ከሁሉም የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች መቀበል ወይም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል። ፎርሙን በፖስታ ቤትና በፋክስ መላክ ይቻላል።

# ለሽማግሌዎችና ባልቴቶች ምክር መስጠት



**ለሽማግሌዎችና ባልቴቶች ምክር መስጠት ሙያ ነክ የሆነ አገልግሎት ነው። ይህም የሚሰጠው ጡረታ በወጡ በጎ ፈቃደኞች ነው። እነሱም ለሽማግሌውና ባልቴቷ እንደዚሁም ለቤተሰባቸው ድጋፍ፣ ምክር፣ መረጃና አመራር ይሰጣሉ።**
**አገልግሎቱ የሚሰጠው ያለ ክፍያ ነው!**

የምክር አገልግሎት ለሽማግሌዎችና ባልቴቶች ለጡረተኞች የተቋቋመው፣ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች በሕብረተሰቡ ዘንድ የተሻሻለና ጥራት ያለው ሕይወት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። አገልግሎቱ የሚተዳደረው በባለሙያ የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኞች ሲሆን በውስጡ ወደ 5000 የሚሆኑ በጎ አድራጊዎች በአገሪቱ በሚገኙት የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ይገኛሉ።
በጎ አድራጊዎቹ በኮርስ መልክ ከፍተኛ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ይህም የሚሆነው ጥሩ አመራርና የምክር ዕርዳታ ለሽማግሌዎችና ባልቴቶች ለቤተሰቦቻቸው እንዲሰጡ ለማድረግ ነው።

## የሚሰጡት አገልግሎቶች፡

**መብቶችን ለመጠቀም ("ሚጹይ ዝሁዮት") የሚሰጥ የምክር ዕርዳታ፡** በጎ አድራጊው ለሽማግሌው/ባልቴቷ የሚረዳው በቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚያገኘውን መብት ስለማስከበር፣ እንደዚሁም በማኅረሰቡ ያሉትን የአግልግሎት ዓይነቶች ባለመብት መሆኑን፣ በማኅበረሰቡ የሚገኘ የሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ባለመብት መሆኑን ማሳወቅ ነው።

**ሥነ ልቡናዊ ድጋፍ፡** ይኸውም በዝውውር ወቅትና ወደ ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ ከተያያዙ ቀውሶች ጋር ነው። እንደዚሁም በዚህ ወቅት ለሚከሰቱ ግላዊ፣ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ለውጦች ጭምር ነው። ለምሳሌ ያህል፡ ጡረታ መውጣት፣ እንቅስቃሴን መቀነስ ወም የትዳር ጓደኛ መሞት

**ስለተለያዩ ጉዳዮች መረጃ መስጠት፡** በኅብረተሰቡ ውስጥ አብሮ የመኖር አማራጭ፣ በትርፍ ጊዜ የመማርና ልዩ ልዩ ድርጊቶችን የመፈጸም አማራጭ መኖሩን ማስረዳት።

## አገልግሎቱ የሚሰጠው ከታች በተዘረዘሩት መስኮች ነው፡

**በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ባለጉዳይን መቀበል፡** አገልግሎቱ የሚሰጠው ሞቅ ባለና በተመቸ ሁኔታ ነው። በጎ አድራጊው ለሽማግሌው/ባልቴቷ እንደ ጆሮ ሁኖ ያገለግለዋል፣ (ያዳምጠዋል)። እንደ ሁኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ መብቶቹን በትክክል እንዲጠቀም ይረዳዋል።

**የቴሌፎን ንግግር፡** በተለይ ይህን የምክር አገልግሎት በቴሌፎን ሽማግሌው/ባልቴቷ እና ቤተሰቦቹ ሽምግልናን በተመለከተ ሁኔታ ምክር እንዲያገኙ ይህ አገልግሎት ይረዳል፣
በየዓመቱ 160,000 የሚሆኑ ሽማግሌዎች/ባልቴቶች እና ቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ ይደረግላቸዋል።

**የመጀመሪያው የቤት ውስጥ ጉብኝት፡** ይህ ጉብኝት የሚደረገው በሽማግሌዎችና ባልቴቶች ቤት ሲሆን ዓላማው ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅና መብታቸውን የሚያስከብሩበትን ምክር ለመለገስ ነው።
እነዚህ በጎ አድራጊዎች በየዓመቱ ወደ 50,000 የሚሆኑ የመጀመሪያ የቤት ውስጥ ጉብኝት ያደርጋሉ።

**ቋሚ የሆነ ማኅበራዊ ጉብኝት** - በጐ አድራጊዎች፣ ብቸኛ የሆኑትንና ከቤታቸው የማይወጡትን ሽማግሌዎች/ባልቴቶች ይጎበኛሉ። ይህም የሚደረገው ብቸኝነታቸውን ለማስወገድና የኅብረተሰቡ አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ለማድረግ ነው።

**ለጡረተኞች የመረጃ ቀን፡** ይህ ቀን ለአዲስ ጡረተኞች በቢቱዋሕ ሌኡሚ ስለሚሰጠው መብት እንዲያውቁ የሚደረግበት፣ ኅብረተሰቡን ለማገልገል፣ የባሕል አማራጭ ማለትም ስለትምህርትና በጎ አድራጎት እንዲያውቁ የሚደረግበት ቀን ነው።

**ሚስት/ ባል ለሞተባቸው የመረጃ ቀን፡** በቅርብ ጊዜ ሚስት/ባል ለሞተባቸው የመረጃ ቀን፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ስለሚያገኙት መብት እንደሁኔታቸው መረጃ ይሰጣቸዋል።

**"ለሂትጋበር በያኻድ" የድጋፍ ቡድን፡** ሚስት/ባል ለሞተባቸው፣ እንክብካቤ የሚደረግላቸውን ሽማግሌ ባል/ሚስት የሚረዱ ቤተሰቦች።
የድጋፍ ቡድኖቹ የሚረዱት የዝውውር ወቅትን በመቋቋም ረገድና በተለያዩ የቀውስ ሁኔታዎች ነው።
ቡድኑ የሚመራው በባለሙያዎች ነው።

ግንኙነት ለመፍጠር ለኛ ደውሉልን፡

***9696 የድጋፍ ማዕከልና ብሐራዊ መረጃ – አዲስ አገልግሎት**

ቀጥተኛ የስልክ ምላሽ ከእሑድ እስከ ኀሙስ
ከ9 እስከ 12፡30

**በቋንቋዎች መሠረት ብሔራዊ የጥሪዎች ማሳለጫ**

- በዕብራይስጥ ቋንቋ – 02-6463400
- በዐረብኛ ቋንቋ – 02-6463401
- በራሽያንኛ ቋንቋ – 02-6463402
- በአማርኛ ቋንቋ – 02-6463403
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ – 02-6463404



# በቢቱዋሕ ሌኡሚ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ



**ቢቱዋሕ ሌኡሚ ማመልከቻህን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ይህንን የቢቱዋሕ ሌኡሚ ውሳኔ በመቃወም ለአካባቢ የሥራ ጉዳይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ መብት አለህ።**

## የማመልከቻ ይግባኝ ኮሚቴ – ቢቱዋሕ ሌኡሚ ያልተቀበላቸውን ማመልከቻዎች እንደገና መመርመር

ቢቱዋህ ሌኡሚ ተቆራጭ ለመቀበል ያቀረብከውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ውሳኔው በአካባቢው ይግባኝ ኮሚቴ እንደገና እንዲመረመር ልታመለክት ትችላለህ። የይግባኝ ኮሚቴው አባት ከሰፊው ሕዝብ የተውጣቱ ሆነው የቢቱዋሕ ሌኡሚ መማክርት የሚሾሟቸው ናቸው። የኮሚቴው ውሳኔ የይግባኝ ጸሐፊው ጉዳዩን እንደገና እንዲያየው የሚሰጡ አስተያየቶች ብቻ ናቸው።

ለዚህ ጉዳይ ስትል ለይግባኝ ኮሚቴው (910/בל) የተሰኘ የማመልከቻ ፎርም መሙላት አለብህ። ፎርሙን ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ አውርዶ በመሙላት መኖሪያ አካባቢህ ለሚገኝ ቅርንጫፍ ማቅረብ ወይም በሚከተለው አድራሻ መላክ ይቻላል፥ אגף חקיקה–גמלאות, המוסד לביטוח לאומי, שד' וייצמן 13, ירושלים 91909 ማመልከቻህን የይግባኝ ኮሚቴ ውሳኔን ከሰማህ በኋላ ከ6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለብህ።

ለይግባኝ ኮሚቴው የምታቀርበው ማመልከቻ ለሥራ ፍርድ ቤት የምታቀርበውን ማመልከቻ ጊዜ አያራዝምልህም። ይህን አቤቱታ ውሳኔውን ከሰማህበት ጊዜ ጀምሮ በ12 ወራት ውስጥ ማቅረብ አለብህ።

## በአካባቢው የሚገኙ የሥራ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች

ይህን አቤቱታ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ውሳኔን ከተቀበልክበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 12 ወራት ድረስ ማቅረብ ትችላለህ።

| ከተማ | አድራሻ | ስልክ |
|---|---|---|
| ኢየሩሳሌም | ረሖቭ ቤት ሀድፋስ 20 | 077-2703333 |
| ቴል አቪቭ | ረሖቭ ሾከን 25 | |
| ሐይፋ | ረሖቭ ፓል ያም 12፣ ሄኻል ሀሚሽፓት | |
| ናጼሬት ዒሊት | ኪርያት ይስሐቅ ራቢን፣ ሄኻል ሀሚሽፓት | |
| ቤኤርሼቫ | ረሖቭ ሀቱክቫ 5፣ ሄኻል ሀሚሽፓት | |

የአካባቢው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ኢየሩሳሌም ለሚገኘው አገር አቀፍ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።

## አገር አቀፍ የይግባኝ ፍርድ ቤት

| | | |
|---|---|---|
| ኢየሩሳሌም | ረሖቭ ኬሬን ሀየሶድ 20 | 077-2703333 |

## የፍርድን ሂደት በተመለከተ የሚሰጥ እርዳታ


የቢቱዋሕ ሌኡሚን ውሳኔ ባለመቀበል ለአካባቢ የሥራ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ወስነህ ከሆነ፣ ከፍርድ ቤቱ አጠገብ ከሚገኙት የእርዳታ ቢሮዎች ይግባኝ በማቅረብ የፍርድ እርዳታ በነፃ ለመቀበል መብት አለህ። ጥያቄህን ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ፎርም ላይ በመሙላት በመኖሪያ አካባቢህ በሚገኘው የእርዳታ ቢሮ ማቅረብ ይኖርብሀል።

## ለፍርድ ቤት እርዳታ የሚሰጡ ቢሮዎች

| ክልል | አድራሻ | ብሔራዊ የስልክ ማዕከል |
|---|---|---|
| *ኢየሩሳሌም | ረሆቭ ሀሶሬግ 1፣ ቤት ሚጽፔ | 1-700-70-60-44 |
| ቴል አቪቭና ማዕከላዊ ክፍል | ረሖቭ ሄንሪየታ ሶልድ 4 | |
| ሐይፋና ሰሜኑ ክፍል | ሽደሮት ፓል ያም 15 አ ኪርያት ሀሜምሻላ | |
| ቤኤር ሼቫ | ረሖቭ ክሬን ሀየሶድ፣ ባይት ካራሶ | |
| ናጼሬት | ረሆቭ ቶፊክ ዛይድ፣ ብንያን ቫፋ ሰንቴር፣ 5ኛ ፎቅ | |

*የኢየሩሳሌም ቢሮ የአሽቄሎን፣ የቅርያት ጋት፣ የአሽዶድና የኤይላት ዲሪዎችንም ጭምር ያገለግላል።

# የቢኡዋህ ሌኡሚ "ክራኖት"



**የቢኡዋህ ሌኡሚ "ክራኖት"የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማልማት ረገድ ይረዳሉ። እነዚህም ፕሮጀክቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ቡድኖች ነው። ይህም አካለ ስንኩላንን፣ አዛውንቶችንና ባልቴቶችን፣ አደጋ ላይ ያሉ ልጆችን፣ ችግር ላይ ያሉ ወጣቶችን፣ ወዘተ. የሚያጠቃልል ሲሆን ዓላማውም እነዚህ ቡድኖች በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲዋሃዱና በሥራ ላይ እንዲሳተፉ ማገዝ ነው።**

በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሥር የሚሠሩ 5 "ክራኖት" አሉ። እነሱም ለአካባቢ አስተዳደሮች፣ ኩባንያዎች ወይም በሕግ ለተመዘገቡ ድርጅቶች በቢቱዋሕ ሌኡሚ ፖሊሲ መሠረት ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያስፋፉ ለመርዳት ነው።

## የአካለ ስንኩላን አገልግሎት ማስፋፊያ "ኬሬን"

ይህ "ኬሬን" ሕዝባዊ አካላት ለአካለ ስንኩላንን ድጋፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማበርከት ይችሉ ዘንድ፣ ፊዚካላዊ መዋቅሮችን እንዲያቋቁሙ ለመርዳት ነው። ዓላማውም አካለ ስንኩላንን በኅብረተሰቡና በሥራ ውስጥ ለማዋሃድ ሲሆን ይህም ሕይወታቸውን ለማሻሻል በማሰብ ነው። ይህ "ኬሬን" በተለያዩ መስኮች ይሠራል። ይህም የሥራ ማገገሚያ፣ ማኅበራዊ መኖሪያ፣ መዝናኛን ስፖርት፣ ልዩ ትምህርት፣ የ"ቲፑል" ማዕከል፣ ከፍተኛ ትምህርትና ተደራሽነት ("ነጊሹት") ናቸው።

## የልዩ ተግባራት ማበልጸጊያ "ኬሬን"

ይህ "ኬሬን" የሚያግዘው ሕዝባዊና ግላዊ አካላት ለኅብረተሰቡ የበጐ አድራጎት አገልግሎቶችን እንዲያለሙ ሲሆን ትኩረት የሚሰጠው አደጋ ላይ ለሚገኙ ለኅብረተሰቡ ክፍልና ልዩ ግልጋሎት ለሚያስፈልጋቸው ነው። ይህም ችግር ላይ ያሉ ቤተሰቦችን፣ አካለ ስንኩላንን፣ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን፣ ወጣቶችንና አደጋ ላይ ያሉ ልጆችን ያጠቃልላል። እነዚህ ፕሮግራሞች በምርምር የሚታገዙ ሲሆን በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ለማሠራጨት እንደሞዴል ያገለግላሉ።

## የአረጋዊያን እንክብካቤ ማስቀደሚያ "ኬሬን"

ይህ "ኬሬን" በኅብረተሰቡና በተቋሞች ውስጥ ለሚገኙ አካለ ስንኩላን አረጋዊያን አገልግሎት የሚረዱ ፕሮጀክቶችን የሚደግፍ ነው። የዚህ "ኬሬን" እንስቃሴዎች የሚያጠቃልሉት የሽማግሌዎችንና የባልቴቶችን የቀን መዋያዎች ማቋቋምን፣ ለልዩ አገልግሎቶች መሣሪያዎች መግዛትን፣ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን የሚንከባከቡ ሠራተኞችን ማሠልጠንን፣ በማገገሚያ ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ አገልግሎቶችን ማጠናከርን፣ ለአካለ ስንኩላን ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ልዩ ፕሮግራም መንደፍን፣ ወዘተ. ያጠቃልላል።



## በአደጋ ላይ ላሉ ልጆችና ወጣቶች የአገልግሎት ማስፋፊያ "ኬሬን"

ይህ "ኬሬን" ገና 18 ዓመት ላልሞላቸው ልጆች ይረዳል። ይህም ከችላ ባይነት፣ በማጐሳቆል፣ ጠብ፣ ወሲብ ትንኮሳ ወይም የወጣት ወንጀለኝነት የተነሣ አደጋ ላይ የሚገኙ ልጆችን ለመርዳት የተቋቋመ "ኬሬን" ነው። ይህ "ኬሬን" ለነጻ ሕይወትንእ የሥራ ችሎታ የሚያሠለጥናቸው ሲሆን ዓላማውም ወደ ድኅነትና ጥገኝነት እንዳያሽቆለቁሉ ለመርዳት ነው።

## "ኬሬን ማኖፍ"

ይህ "ኬሬን" የሚያግዘው የሥራ ላይ አደጋዎችን የሚከላከሉ ፕሮጀክቶችን በገንዘብ በመርዳት ሲሆን በፋብሪካዎችና በሌሎች የሥራ ቦታዎች የሥራ ላይ ጥንቃቄዎችን በማዳበር ረገድ ይረዳል። ይህም የሚያጠቃልለው ተግባራዊ ምርምርን፣ የገለጻ ሥራዎችን፣ ሙያዊና የሥራ ላይ አደጋዎችን አፈላልጐ ማግኘትን፣ የደኅንነት መንገዶችን ማሻሻልን፣ አዳዲስ ዘዴዎችን ማበልጸግን፣ የገለጻ ዘመቻዎች ማዘጋጀትን ነው።

› **ለተጨማሪ መረጃዎች**

"ክራኖት" ሀቢቱዋሕ ሌኡሚ
ስደሮት ቫይትስማን 13፣ ኢየሩሳሌም 91909
ስልክ፡ 02-6709087
ፋክስ፡ 02-6463081
እንደዚሁም በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ – www.btl.gov.il

# ለብሔራዊ ዋስትና እና ለጤንነት ዋስትና ተብሎ የሚከፈል ገንዘብ



**ለአብዛኛው የቢቱዋሕ ሌኡሚ “ኺጽባዎች” ባለመብት መሆን የሚቻለው የቢቱዋሕ ሌኡሚን ክፍያ በመፈጸም ነው። ቢቱዋሕ ሌኡሚ በሁሉም እስራኤላዊ ኗሪ ላይ ተግባራዊ የሚሆን ግዴታዊ ዋስትና ነው። መንግሥታዊ የጤንነት ዋስትና ግዴታዊ ሲሆን ሁሉም የእስራኤል ኗሪ የጤንነት አገልግሎቶች እንዲያገኝ የሚያስችል ነው።**

## አስገዳጅ ቢቱዋሕ ሌኡሚና የጤንነት ዋስትና

› 18 ዓመት የሞላው ማንኛውም **የእስራኤል ኗሪ** የሆነ ለጤንነት ዋስትና የሚሆን ገንዘብ ለብሔራዊ ዋስትና ከሚከፍለው ገንዘብ ጋር ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የመክፈል ግዴታ አለበት። የቤት እመቤት የሆነች ሴት (ያገባች ሴት የማትሠራ ከሆነ እና ባሏ ዋስትና ያለው ከሆነ) ለጤና ዋስትና የሚከፈለውን ገንዘብ ከመክፈል ነፃ ናት። እንደዚሁም አንድ ሰው ከ62 ዓመት ዕድሜ በኋላ የእስራኤል ኗሪ ከሆነ ከክፍያው ነጻ ነው።

እያንዳንዱ የእስራኤል ኗሪና ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የጤንነት ዋስትና እንዲኖረው የሚያስፈልግ ሲሆን የጤንነት ዋስትና ገንዘቡን ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ከሚከፈለው ገንዘብ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መክፈል አለበት። የቤት እመቤት የሆነች ሴት (የእርጅና ድጎማ ከምትቀበል ሴት ውጭና ለባሏ ለእርጅና ድጎማው ጭማሪ የሚሰጠው ከሆነ) ለጤና ዋስትና የሚከፈለውን ገንዘብ ከመክፈል ነፃ ናት። እያንዳንዱ ባለዋስትና በአንዱ ኩፓት ሆሊም ውስጥ መመዝገብ ያለበት ሲሆን በሕጉ በተገለጸው መሠረት በኪሊኒኩ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት የመቀበል መብት አለው።

› **በዚህ ምዕራፍ ላይ የተሰጡ ብያኔዎች፥**
**ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚከፈል–** ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ተቆራጭ የሚከፈል።
**ለጤና ዋስትና የሚከፈል –** ለጤና አገልግሎት የሚከፈል።
**የዋስትና ገንዘብ –** ይህ ዋስትና የሚያጠቃልለው ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚከፈለውንና የጤና ዋስትናውን በአንድ ላይ ነው።
**አማካኙ ደመወዝ –** 9,464 ሼቄል በጥር ወር 2016።
**ለብሔራዊ ዋስናው የሚከፈለው ከፍተኛው ገቢ –** በጥር ወር 2016 ላይ 43240 ሼቄል ነው።

የብሔራዊ ዋስትና እና የጤና ዋስትና ክፍያ የሚታሰበው እንደሰውየው ከሥራ እንደሚያገኘው የገቢ መጠን፣ እንደተወሰነለት ደረጃ መጠን ነው። (ተቀጣሪ፣ ራሱን ችሎ የሚሠራ፣ የማይሠራ፣ ዩኒቨርስቲ ተማሪ እንዲሁም ሌሎች) ክፍያው በሕግ ከተወሰነው ከዝቅተኛው ክፍያ መቀነስ አይችልም፣ እንዲሁም በሕጉ መሠረት ከተወሰነው ከፍተኛ ክፍያ በላይ መሆን አይችልም።

ሥራ የማይሠራና ምንም ዓይነት ገቢ የሌለው የሚከፍለው ዝቅተኛው የክፍያ መጠን በወር 196 ሼቄል ነው።
ባለ ዋስትናው ለጊዜው እስራኤል አገር በማይኖርበት ጊዜ እንኳን ይህን የዋስትና ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት።

### የብሔራዊ ዋስትና እና የጤና ዋስትናን ክፍያ ላለመክፈል የሚፈቀድላቸው፥

- ወደ እስራኤል የመጡ አገር አዲስ ገቢዎችና፣ ከገቡ ጊዜ እስከ 12 ወር ድረስ ሥራ ያልሠሩ።
- ከ21 ዓመት ዕድሜ በፊት ለውትድርና ወይም ብሔራዊ አገልግሎት የሚሄዱ
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ (እስከ 12 ክፍል) ዕድሜው 19 ዓመት እስኪሆነው ድረስና ተማሪ እስከሆነ ድረስ
- እስረኞች፣ ከእስር የተፈቱ ወጣቶች ወይም ከ12 ወራት በላይ ተይዘው የቆዩ ከዚህ ክፍያ ነፃ ናቸው።

**በመደበኛ አግልግሎት ላይ ያለ ወታደር** የሕክምና አገልግሎት ከውትድርናው ስለሚቀበል በቢቱዋሕ ሌኡሚ በሚደረገው የጤና ዋስትና ውስጥ ዋስትና አይኖረውም፣ ስለዚህ የጤና ዋስትና ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለበትም።

**ቋሚ የውትድርና አገልግሎት የሚሰጥ** የጤንነት ዋስትና መክፈል አለበት።

**ውትድርና ላይ ሆኖ ዩኒቨርስቲ የሚማር** በሚማርበት ጊዜ የብሔራዊ ዋስትናውንና የጤና ዋስትናውን ክፍያ ራሱ ይከፍላል። ቢቱዋሕ ሌኡሚ የመክፈያ ሰነድ ይልክለታል። ይህን ክፍያ ማከናወን ያለበት በየአራት ወሩ ነው።

**ውትድርና እና በየሺቫ የሚማር** – የመከላከያ ሚኒስቴር የብሔራዊ ዋስትናውንና የጤና ዋስትናውን ክፍያ ውትድርና ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከተለቀቀበት ቀን ድረስ ያለውን ይከፍልለታል። በተጨማሪም በየሺቫ በሚማርበት ጊዜም ይህ ክፍያ በመከላከያ ሚኒስትር ይሸፈናል።

## ለኩፓት ሆሊም መመዝገብና ከአንድ ኩፓት ሆሊም ወደ ሌላው መዘዋወር

ለኩፓት ሆሊም ለመመዝገብና ከአንድ ኩፓት ሆሊም ወደሌላው ለመዘዋወር የቢቱዋሕ ሌኡሚን ድረ ገጽ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ምንም ክፍያ የለውም። እንደዚሁም ወደ አንዱ የፖስታ ቤት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በመሄድ ልዩ ፎርም መሙላት ይቻላል (ለዚህ ጉዳይ ግብር መክፈል ያስፈልጋል)።

› ምዝገባና ዝውውርን በተመለከተ ጥያቄ ካለ እና ማብራሪያ ካስፈለገ ፣ ከእሑድ ጀምሮ እስከ ኀሙስ ባሉት ቀናት ከ9፡00-13፡00 ሰዓት ቢቱዋሕ ሌኡሚ፣ የጤና ዘርፍ ምዝገባ ክፍል፣ ስዴሮት ቫይጽማን 13፣ ኢየሩሳሌም፣ ስልክ ቁጥር 02-6462000፣ ፋክስ 02-6462029 ማመልከት ይቻላል።

## ተቀጥሮ የሚሠራና ራሱን ችሎ የሚሠራ ልዩነቱ ምንድን ነው?

- **ተቀጥሮ የሚሠራ –** አሠሪው ስለ ደመወዙ ሪፖርት ማድረግና ዋስትና የመክፈል ኃላፊነት አለበት።
- **ራሱን ችሎ የሚሠራ –** በቢቱዋሕ ሌኡሚ የመመዝገብና የዋስትናውን ክፍያ የማከናወን ግዴታ አለበት።
- **ተቀጥሮ የሚሠራ –** የሥራ አጥ ዋስትና ይኖረዋል፣ የሠራተኞች የመብት ዋስትና ይኖረዋል፣ ድርጅቶች በሚከስሩበትና በሚፈርሱበት ጊዜም ዋስትና አለው።
- **ራሱን ችሎ የሚሠራ –** የሥራ አጥ ዋስትና የለውም፣ የሠራተኞች መብት ዋስትና የለውም፣ ድርጅቱ በሚከስርበትና በሚፈርስበት ጊዜ ዋስትና የለውም።
- **ተቀጥሮ የሚሠራ –** የዋስትናውን ክፍያ አሠሪው በውቅቱ ሳይከፍል በመቅረቱ ምክንያት መብቱ አይነካም።
- **ራሱን ችሎ የሚሠራ –** ካልተመዘገበና ክፍያውን በወቅቱ ካላሟላ መብቶቹ ሊጎዱ ይችላሉ።

## ራሱን ችሎ የሚሠራ

ራሱን ችሎ የሚሠራ ከሚከተሉት አንዱን የሚያሟላ ነው።

- ቢያንስ በሳምንት 20 ሰዓት በአማካኝ የግል ሥራ መሥራት
- ሠርቶ የሚያገኘው ገቢ ከአማካኝ ደመወዝ ገቢ ከ60% በላይ የሆነ (በጥር ወር 2016 – 5,678 ሼቄል)
- ቢያንስ በሳምንት 12 ሰዓት በአማካኝ በእጁ ሠርቶ የወር ገቢው ከአማካኝ ገቢ ከ15% በላይ ከሆነ (በጥር ወር 2016 ዓ.ም. 1,420 ሼቄል)

ራሱን ችሎ የሚሠራ ሰው ወዲያውኑ ሥራውን እንደጀመረ በቢቱዋሕ ሌኡሚ መመዝገብ አለበት። ራሱን ችሎ የሚሠራ ሰው በሥራ ጊዜ አደጋ ቢደርስበት ለዚህ አደጋ ካሳ ባለመብት መሆን የሚችለው በአደጋው ወቅት በቢቱዋሕ ሌኡሚ ተመዝግቦ የተገኘ እንደሆነና የዋስትናውን ክፍያ በወቅቱ ያከናወነ ሲሆን ብቻ ነው።

> በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ላይ የሚገኘውን (6101/ገב) የተሰኘውን የመመዝገቢያ ፎርም ሞልተህ "ኦንላይን" ለቢቱዋሕ ሀሌኡሚ መላክ ትችላለህ።

**ባለ ትዳር ሴት በባሏ ድርጅት ውስጥ ራሷን ችላ የምትሠራ ከሆነ** በቢቱዋሕ ሌኡሚ መመዝገብና የዋስትናውን ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባት።

**ባልና ሚስት በጋራ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ከሆነ** ገቢያቸውን ለሁለት ተከፋፍለው የሚደርስባቸውን የዋስትና ክፍያ እንደ ገቢያቸው መጠን መክፈል ይችላሉ። ይህም የሚሆነው የንብረት ክፍፍሉ ሁኔታ የገቢው 1/3 ወይም 2/3 የሆነ እንደሆነ ወይም እያንዳንዳቸው ግማሽ ግማሽ የደረሳቸው እንደሆነ ነው።

**ራሱን ችሎ የሚሠራ ሰው፣ በተጨማሪ ተቀጥሮ የሚሠራ ከሆነ** ይህ ሰው ከሁለቱም ገቢዎች እስከ ከፍተኛው ገቢ ዋስትና የመክፈል ግዴታ አለበት።

**ራሱን ችሎ የሚሠራ ሰው ከሥራ ሳይሆን ሌላ ገቢ ያለው ከሆነ** ከሥራም ባይሆን ከሌላ ገቢ ካለው የዋስትና ክፍያውን መክፈል አለበት፣ ይህም ክፍያ እስከ ከፍተኛው ገቢ መሆን አለበት። ከዚህ ገቢ ላይ የአማካኝ ደመወዝ ተመጣጣኝ ቅናሽ ከተደረገ በኋላ ነው።

**ከላይ እንደተጠቀሰው ራሱን ችሎ ያሚሠራ የሚለውን ትርጉም የማያሟላ፣** ራሱን ችሎ እንደሚሠራ ሰው አይቆጠርም ግን፣ ቀጥለው የሚዘረዘሩት ደንቦች ይመለከቱታል ("ተቀጥሮ የማይሠራ ሰው ራሱን ችሎ የሚሠራ አይደለም" የሚለውን ተመልከት)።

### ራሱን ችሎ የሚሠራ ሰው የሚከፍለው የዋስትና መጠን የሚከተሉት ናቸው (በጥር ወር 2016)

ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነና ለጡረታ ያልደረሰ ራሱን ችሎ የሚሠራ የሚከፍለው፡

- የገቢውን የተወሰነው ክፍል የአማካኝ ደመወዝ እስከ 60% (በጥር ወር 2016 ዓ.ም. 5,678 ሼቄል) የሚከፍለው የዋስትናው ክፍያ 6.72% ሲሆን የጤና ዋስትናው ደግሞ 3.1% ይሆናል።
- የገቢው የተወሰነ ክፍል፣ ከአማካኝ ደመወዝ ከ60% በላይ ከፍተኛ ከሆነ፣ (5,678 ሼቄል) የዋስትናው ክፍያ 11.23% ሲሆን የጤና ዋስትናው ክፍያ ደግሞ 5% ይሆናል።

ለጡረታ የደረሱና የጡረታ ገንዘብ የሚቀበሉ፡- ከገቢው መጠን የተወሰነውን ክፍልና የደመወዝ አማካኝ 60% ድረስ (5,678 ሼቄል) ብሔራዊ ዋስትና 0.39% ሲከፍሉ፣ ከገቢው መጠን የተወነው ክፍል እስከ ከፍተኛ ድረስ የብሔራዊ ዋስትና 0.68% ይከፍላሉ።
የጤና ዋስትናው ክፍያ ለጡረታ ከሚከፈላቸው ገንዘብ ላይ ይቀነሳል።

## ተቀጥሮም ሆነ የግል ሥራ የሌለው ባለ ዋስትና

ተቀጥሮም ሆነ በግሉ ሥራ የሌለ ሰው በቢቱዋሕ ሌኡሚ ተመዝግቦ የሚፈለግበትን የብሔራዊ ዋስትና እና የጤና ዋስትናውን ክፍያ እንደ ገቢው መጠን ራሱ መጥቶ መክፈል አለበት። ምንም ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ዝቅተኛውን **የዋስትና ክፍያ በወር 168 ሼቄል** መክፈል ይኖርበታል (በጥር ወር 2016)።
**በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የሚማር ተማሪ** ይህ ተማሪ ሥራ የማይሠራ ከሆነ የብሔራዊ ዋስትና እና የጤና ዋስትና ዝቅተኛውን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል። **በወር 125 ሼቄል** ይህ ክፍያ የሚከናወነው በየአራት ወሩ ሲሆን በጥር፣ ሚያዝያ፣ በሐምሌና በጥቅምት፣ በዓመት አንድ ጊዜ በሚላክለት የመክፈያ ሰነድ አማካኝነት ነው።

### ራሱን ችሎ የማይሠራና ተቀጥሮ የማይሠራ፣ ከሥራ ሳይሆን ከሌላ ምንጭ ገቢ ያለው የሚከፍለው የዋስትናው ገንዘብ መጠን (ጥር 2014)

ከከፊሉ ገቢ እስከ 60% አማካኝ ገቢ (5678 ሼቄል) የብሔራዊ ዋስናውን ክፍያ 4.61% ሲከፍል፣ የጤና ዋስትናውን ደግሞ 5% ይከፍላል። ከከፊሉ ገቢ ከአማካኝ ገቢው ደግሞ ከ60% በላይ እስከ ከፍተኛው ገቢ ከሆነ የዋስትናውን ክፍያ 7% እና የጤና ዋስትናውን ደግሞ 5% የመክፈል ግዴታ አለበት።

## የዋስትና ክፍያ በቅድሚያ መክፈል

**የግል ሥራ የሚሠራ እንዲሁም ሥራ የሌለው ግን ገቢ ያለው፣ የዋስትናውን ክፍያ በየወሩ፣ ወሩ በገባ በ15 ቀን አስቀድሞ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።**በየወሩ አስቀድሞ የሚከፈለው የዋስትና ክፍያ መጠን የሚወሰነው ግምታዊ በሆነ የገቢ መጠን ነው። ከገቢ ቀረጥ መሥሪያ ቤት ግምገማ ተቀብለህ ከሆነ፣ ቢቱዋሕ ሌኡሚ የግምገማውን ልዩነት ለመብትህም ለግዴታህም ግምት ውስጥ በማስገባት ሂሳብ ያደርጋል።
ቢቱዋሕ ሌኡሚ ተመልሶ ለባለዋስትናው በወቅቱ የተከፈሉትን ተቆራጮች ሂሳብ ያደርጋል። (ደመወዝን የሚቀይሩ ድጎማዎች፣ በወሊድ ወቅት የሚሰጥ ድጎማ፣ በተጠባባቂ ውትድርና ጊዜ የሚከፈል ድጎማ)።

### አስቀድሞ የሚከፈል የዋስትና ክፍያ መጨመርና መቀነስ፣

አስቀድሞ የሚከፈለው የዋስትና ክፍያ የተወሰነው እንደ ትክክለኛ የገቢው መጠን ካልሆነ፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሂሳብ ክፍል በመሄድ ትክክለኛውን የገቢ ሰነድ ማረጋገጫና ፎርም 672 ማሳየት ያስፈልጋል።
ይህ ማስተካከያ በዓመት 4 ጊዜ በየአራት ወሩ ሊሠራ ይቻላል፤ በጥር፣ በሚያዝያ፣ በሐምሌና በጥቅምት። ይህ ማስተካከያ የሚሠራው በሚቀርበው የገቢ ማረጋገጫ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ደንብ መሠረት ሲፈጸም ብቻ ነው።

በግል ሥራ የሚተዳደር ሠራተኛ አስቀድሞ የሚከፈለውን የዋስትና ክፍያ መጠን ማሳደግና መቀነስ ይቻላል። ይህም መሆን ያለበት ዓመታዊ የባጀት ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት ማመልከቻ በማቅረብ ሲሆን በሥራ ቦታው አደጋ ከደረሰበትም ይህንኑ ማድረግ ይችላል – ነገር ግን አደጋው ከደረሰበት በኋላ አይቻልም።

በዓመቱ የበጀት ዘመን ሥራ ቦታው አደጋ ያልደረሰበት በግል ሥራ የሚተዳደር ግለሰብ ዓመታዊ የገቢ ምንጩ ከአለፈው ከፍተኛ እንደሚሆን እርግጠኛ ከሆነ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚከፈለውን ግብር ከፍ ለማድረግ በአቅራቢያው ከሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በመምጣት የሚከፈለውን የዋስትና ክፍያ ከፍ እንዲያደርግ **ይመከራል**። በዓመታዊ የባጀት ዘመንም ከከፈለው ገንዘብ 52% የገቢ ግብር ከሚወራረደው ገንዘብ የሚታሰብ ይሆናል።

> በግል ሥራ የሚተዳደር ግለሰብ ወይም የማይሰራ የዋስትና ክፍያ ሳይከፍል ቀርቶ ዕዳ ካለበት ሕጉ በሚያዘው መሠረት ከነወለዱ ዕዳውን እንዲከፍል ይገደዳል።

## ተቀጥሮ የሚሠራ

> አሠሪው ቀጥሮ ለሚያሠራው ሠራተኛ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያና የጤና ዋስትና ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

አሠሪው በሥሩ ተቀጥረው ስለሚሠሩ ሠራተኞች የወር ደመወዛቸውን ሪፖርት ማድረግ እንዲሁም የቢቱዋሕ ሌኡሚና የጤና ዋስትና ግብር የግድ መክፈል ይኖርበታል።
አሠሪውም ለሠራተኞቹ ከሚከፍለው የወር ደመወዝ የቢቱዋሕ ሌኡሚና የጤና ግብሩን ክፍያ (ከጥር 2014 ጀምሮ በተወሰነው መሠረት) መክፈል ይችላል። ከአጠቃላይ የአገሪቱ ሠራተኛ አማካኝ ደመወዝ (በጥር 2016 5,678 ሼቄል) እስከ 60% ብቻ ለሚያገኙ ከአንድ ሠራተኛ የወር ደመወዝ 0.4% ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር 3.1% ደግሞ ለጤና ዋስትና ግብር ተቀንሶ ይከፈላል። ከአጠቃላይ የአገሪቱ የሠራተኛ አማካኝ ደመወዝ ከ60% በላይ ለሚከፈላቸው ከሠራተኛው 7% ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር እንዲሁም 5% ድግሞ ለጤና ዋስትና ግብር ተቀንሶ ይከፈላል።

> አሠሪው ለሠራተኛው የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ በወቅቱ ካልከፈለ የአንድ ዓመት እስራት ወይንም የገንዘብ ቅጣት ይወሰንበታል። አንድ ሠራተኛ የሆነ አደጋ ቢያጋጥመውና በዚህ ምክንያትም ከቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ድጐማ የሚቀበል ከሆነ የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ሠራተኛው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ይከፈለው የነበረውን ተቆራጭ ገንዘብ ከአሠሪው ዘንድ የመጠየቅ መብት አለው።

**አሠሪዎች በእስራኤል ግዛት ሠራተኞችን ከይሁዳ ሰማርያ ጋዛ አካባቢና ፍልስጤም ራስ ገዝ አስተዳደር፤** አስመጥተው የሚያሠሩ ከሆነ ለእነዚህ ሠራተኞች የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ መክፈል ይኖርባቸዋል (በቤት ውስጥ ሠራተኛነት ከሚሠሩት በስተቀር)። የሚከፈለውም በሀገር ውስጥ አስተዳደር መሥሪያ ቤት፣ የሕዝብ ባለሥልጣንና የድንበር መተላለፊያዎች የክፍያ ክፍል ባመቻቸው መንገድ ነው (የእናቶች፣ ኪሳራና በሥራ ጉዳት የደረሰባቸው ክፍል)።

**በእስራኤል የውጭ ሀገር ዜጎችን ለሚያሠሩ አሠሪዎች** ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ስለሠራተኞቻቸው ማንነት ማስታወቅና ወርኀዊዉን ክፍያ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መክፈል ይኖርባቸዋል።
ከእስራኤል ጋር ስምምነት ካላቸው ሀገሮች የመጡ የውጭ አገር ሰዎችን የሚያሠሩ፣ ለሠራተኞቹ ሙሉ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ መክፈል ያለባቸው ሲሆን የጤንነት ዋስትና ክፍያ ግን አይከፍሉም።።

**የእስራኤል ኗሪ ሆኖ በውጭ ሀገር ከእስራኤላዊ አሠሪ ዘንድ ተቀጥሮ የሚሠራ ከሆነ፣** የሥራ ስምምነታቸውን በእስራኤል ሀገር የቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግና ደንብ መሠረት ከሆነ አሠሪው ስለሠራተኛው ማንነት ማሳወቅ ያለበት ሲሆን በተጨማሪም እንደማንኛውም በእስራኤል የሚገኝ ሠራተኛ መሠረት የቢቱዋሕ ሌኡሚን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።
ሠራተኛው ውጭ ሀገር ሲሰራ 5 ዓመት ካለፈው አሠሪው ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የማራዘሚያ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል። የማመልከቻው ፈቃድ የሚሰጠውም ሠራተኛው የሚቀርቡለትን የተወሰኑ ጥያቄዎች ካለፈ ብቻ ነው።

**ተቀጥሮ የሚሠራ ቢሆንም የገቢ ምንጩ ግን ከሌላ ቦታ ከሆነ** ከአማካዩ ደመወዝ ላይ 25% ከተቀነሰ በኋላ ከሌላ ቦታ ለሚገኘው ማንኛውም ገቢ እስከ ከፍተኛ የገቢ መጠን ድረስ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ይከፍላል። ይህም ተቀጥሮ የሚሠራበትን ወደ ግምት በማስገባት ነው።

## ያለክፍያ ዕረፍት የወሰደ ቅጥር ሠራተኛ

ሠራተኛው ከሚሠራበት ቦታ ያለክፍያ ዕረፍት ከወሰደና በዚያ ጊዜም ሌላ ቦታ የማይሠራ ከሆነ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር የግድ ራሱ መክፈል ይኖርበታል።
የመጀመሪያዎቹን ሁለት ወራት የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር አሠሪው ይከፍላል።
ይህን ክፍያም አሠሪው ለሠራተኛው ይሰጠው ከነበረው ክፍያ ላይ ይወርዳል።
ያለክፍያ ዕረፍት የወሰደው ሠራተኛ ከሦስተኛው ወር ጀምሮ የሚከፍለው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር በጣም ዝቅተኛውን ሲሆን ይህም አሠሪው ሌላ የገቢ ምንጭ ከሌለው ነው።

## ከተለያዩ አሠሪዎች ጋር ተቀጥሮ ለሚሠራ ሠራተኛ

ከሠራተኛው ደሞዝ ላይ ሠራተኛው ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ዝቅተኛ ግብር የሚከፍልበት ፈቃድ እስካላመጣ ድረስ ሙሉ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ይወርዳል። እንዲህ ዓይነት ሠራተኛም ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ስለገቢዎቹ ሁኔታ ማስታወቅ አለበት።

ይህ ዝቅተኛ ግብር የሚከፍልበት ፈቃድ የሚሰጠው ሠራተኛው ከዋናው ሥራው የሚያገኘው ገቢ ከአጠቃላይ የገቢ አማካይ ቁጥር 60% እጅ ዝቅተኛ ከሆነ ነው (ከጥር 2016 አማካዩ 5,678 ሼቄል ነው)

ሠራተኛው መክፈል ከሚገባው በላይ የከፈለ ከሆነ ግን ትርፍ ገንዘብ ወለዱ ተጨምሮ ይመለስለታል። በዚያው መጠንም ሠራተኛው መክፈል ከሚገባው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ዝቅተኛ ከፍሎ ከነበረ ትርፍ ገንዘብ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መመለስ ይገባዋል።

> ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ልዩ ክፍያ ለመክፈል ፈቃድ የሚጠየቅበት እንዲሁም የቀረብን ወይንም የምንመልሰው ገንዘብ ካለ የምናስተካክልበት ሂደት በቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ ማለትም www.btl.gov.il ውስጥ ביטוח /תיאום דמי ביטוח והגביה በመግባት ማየት ይቻላል።

## በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚያገለግል ሠራተኛና መብቶቹ

ቤት ውስጥ የሚያገለግል ሠራተኛ ማለት በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚሠሩትን ማለት ነው። ይህም ሕፃናትን መንከባከብ፤ የቤቱን መኖሪያ ደረጃ ማፀዳት የመሳሰሉት ያካትታል።
በቤቱ ውስጥ ቀጥሮ የሚያሠራ ሠራተኛ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ማስታወቅ ይኖርበታል።በተጨማሪም ለሠራተኛው የዋስትና የጤና ግብር መክፈል አለበት። አሠሪውም ለሠራተኛው ከሚከፍለው ደሞዝ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚከፍለውን ግብር መቀነስ ይችላል።

> አሠሪው በቤት ውስጥ የሚያገለግለውን ሠራተኛ ሙሉ መረጃ በፎርሙ ላይ መሙላት ይኖርበታል። የሠራተኛውን ዝርዝር መረጃ በፍርሙ ላይ ያለመሙላት ወይም የትሳሳቱ መረጃዎችን መሙላት ሠራተኛው ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ማግኘት የነበረበት መብት ላይ ጉዳት ሊያደርስበት ይችላል።

በቤት ውስጥ የሚያገለግል ሠራተኛ አሠሪም የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ካልከፈለ የአንድ ዓመት እስራት ወይንም የገንዘብ ቅጣት ይጠብቀዋል። በተጨማሪም በደሞዙ ልክ የቢቱዋሕ ግብሩን እንዲከፍል ይደረጋል። አሠሪው ለሠራተኛው ሳይከፍለው የቀረውን ክፍያዎችንም ለሠራተኛው እንዲከፍል ያደርገዋል። በጊዜው ያልተመዘገበውን እንደዚሁም የዋስትና ገንዘቡን በጊዜው ያልከፈለውን አሠሪ ቢቱዋሕ ሌኡሚ የመክሰስ መብት አለው።

የውጭ ሀገር ዜጋ ሆኖ ቤት ውስጥ ካገለገለ ወይንም እስራኤላዊ ያልሆነን ዟሪነት ይዞ በይሁዳና ሰማሪያ በጋዛ አካባቢ ወይንም በፍልስጤም ራስ ገዝ አስተዳደር የሆነ ግለሰብም የሚያሰራ ከሆነ የግድ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር መክፈል ይኖርበታል። የነዚህ ሠራተኞች የግብር ክፍያም ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት በቀጥታ ይከፈላል።

## ቋሚ የውትድርና አገልግሎት ላይ ያለ ወታደር

በክፍያ የሚያገለግል መደበኛ ወታደር ከእስራኤል መከላከያ ኃይል ሙሉ የሕክምና አገልግሎት ቢያገኝም ከደሞዙ ግን የጤና ዋስትናና የቢቱዋሕ ሌኡሚ ዋስትና ግብር ይወርድበታል። የሚቀነስበት የግብር ክፍያዎችም ሌላ ቦታ ተቀጥረው ከሚሠሩ ሠራተኞች በሚወርድባቸው ደንብ መሠረት ነው።

## የሙያ ሥልጠና በመማር ላይ የሚገኝ ግለሰብ

በቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ሥር የሙያ ስልጠና የሚወስድ ግለሰብ የቢቱዋሕ ሌኡሚ የግብርና የጤና ዋስትና ክፍያ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይከፈልለታል። በሥራ ጉዳት ለደረሰባቸውና ለእናቶች የሚከፈለው ክፍያ (በተፈቀዱት ቦታዎች) የቢቱዋሕ ሌኡሚን የግብር ክፍያ የሚከፍለው ሥልጠናውን የሚሰጠው ድርጅት ነው። ከደመወዙ ላይ የሚቆረጠው የዋስትና ክፍያ ከተቀጣሪ ሠራተኞች ላይ ከሚቀነሰው መጠን ጋር እኩል ነው።

## ውጭ ሀገር እየኖረ የዋስትና ክፍያ ለሚከፍል

ውጭ ሀገር እየኖረ ነገር ግን እስራኤላዊ ያልሆነ አሠሪ ጋር የማይሠራ ያገኘው በነበረው ገቢ መሠረት የቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያውን ይፈጽማል። ዝቅተኛ የተባለውን ክፍያ ማለትም **ለወር 168 ሼቄል** (ለጥር 2016) ይከፍላል። ይህም እስራኤል ሀገር የማይሠራና በግል የሚተዳደር ዜጋ እንደሚከፍለው ማለት ነው።
በውጭ የሚኖር ባለዋስትና ከውጭ አገር ሥራዎቹ ገቢ ካለው፣ የዋስትናውን ክፍያ የሚከፍለው ለ“ማስ ሀክናሳ” ሪፖርት በሚያደርገው ገቢው መሠረት ነው።

> ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ግለሰብ ወደ ውጭ ከመሄዱ በፊት አቅራቢያው ወደሚገኘው የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት በመሄድ ውጭ ሀገር እንደሚሄድና ውጭ ሀገር ሊኖር ምን ያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት አመቻችቶ መሄድ ይኖርበታል።

እስራኤል የቢቱዋሕ ሌኡሚ ዋስትና የተፈራረመችባቸውን ሀገሮች (ኦስትሪያ፤ ኡራጓይ፤ ጣሊያን፤ ቡልጋሪያ፤ ቤልጂም፤ እንግሊዝ፤ ጀርመን፤ ዴንማርክ፤ ሆላንድ፤ ኖርዌይ፤ ፊንላንድ፤ ቼክ፤ ፈረንሳይ፤ ካናዳ፤ ሲዊድን፤ ስዊስ፣ ስሎቫኪያ እና ሩማኒያ) በእነዚህ ሀገራት የዋስትና ክፍያ ካደረገና መረጃዎች ካለው በእስራኤል ሀገር ከመክፈል ነፃ ይሆናል። **ነገር ግን የጤና ዋስትና ክፍያ ግን የግድ መክፈል ይኖርበታል። ምክንያቱም ስምምነቱ የጤና ዋስትናን ስለማይጨምር ነው።**

## ለሁለት ዓመት ወይንም ከዚያ በላይ በውጭ ሀገር ለሚቆይ የእስራኤል ዜጋ

ለተከታታይ ሁለት ዓመት ወይንም ከዚያ በላይ በውጭ ሀገር የቆየ እስራኤላዊ ዜጋ የጤና ዋስትና ያልከፈለ ወይንም ከ12 ወራት በላይ ክፍያውን ያዘገየ በእስራኤል ሀገር በህጉ መሠረት የሕክምና አገልግሎት አይቀበልም። በአዲስ መልክ መብቱን ለማስከበር የሚፈልግ ከሆነ ባልከፈለው ዓመት ልክ 1 ወር የመጠበቅ ግዴታ አለበት። ይህ የመጠባበቂያ ጊዜ የሚባለው አንድ ዜጋ አነሰ ቢባል ከ182 ቀን በላይ በተከታታይ ባይሆን ውጭ ሀገር ከተቀመጠ የመጠባበቂያ ጊዜውም ከዝቅተኛ 2 ወር ከፍተኛው ደግሞ 6 ወር ነው።

### ልዩ ክፍያ

**ዟሪነቱ በእስራኤል** የሆነ በሙሉ ይህን መጠባበቂያ ክፍያ ዕዳ መክፈል ከፈለገ ልዩ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል። ሕጉም **10,950 ሼቄል** ነው (ከጥር 2016 ጀምሮ)።

በቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ድረ ገጽ ወይም በባንክ ቼክ ቀጥታ ለቅርንጫፉ መክፈል ይቻላል። ለተጨማሪ መረጃም የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ድረ ገጽ አድራሻ www.btl.gov.il/תיאום דמי ביטוח/ביטוח וגביהה በመግባት ማያት ይቻላል።

## ውጭ ሀገር ኖረው ለተመለሱ ዜጎች

ውጭ ሀገር ኑሮውን መሥርቶ የነበረ እስራኤላዊ ወደ እስራኤል ሲመለስ ኑሮውን በዚህ ሀገር እንደጀመረ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ይታወቅለታል። ውጭ ሀገር በቆየባቸው ዓመታት ልክ የተወሰኑ ወራት ከጠበቀ በኋላ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናል። የሚጠብቅበትም ጊዜ ከ6 ወራት አይበልጥም። ይህ የመጠበቂያ ወራት ክፍያ ዕዳ መላቀቅ ከፈለገ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ልዩ ክፍያውን መክፈል ይገባዋል። (ልዩ ክፍያ የሚለውን ተመልከት)

## አስቀድሞ ጡረታ ለወጣ ግለሰብ

የጡረታ ዕድሜ ክልል ሳይደርስ እንዲሁም ያላገባች ሆና ለጡረታ ዕድሜ ክልል ሳትደርስ የጡረታ ክፍያ የሚሰጣቸው ከሆነ ከጡረታ ክፍያቸው የሚወርደው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር መክፈል ይኖርባቸዋል።

የጡረታ ክፍያ የሚከፍለው ድርጅት ከጡረታ ሂሳብ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ቀንሶ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል።

“የጡረታ ክፍያ” ማለት አንድ ሰው በሥራ ዓለም ላይ ቆይቶ ዕድሜው ለጡረታ መውጫ ሲደርስ ወይንም አስቀድሞ በስምምነት ሥራውን ሲለቅ የሚከፈል ገንዘብ ነው።

በሞት ለተለየ ግለሰብ ይከፈል የነበረው የጡረታ ክፍያ በሕይወት ላሉ የመጀመሪያ ቅርበት ቤተሰቦች ከተከፈለ፣ የጡረታ ክፍያ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ክፍያ ነፃ ይሆናል።

**አስቀድሞ ጡረታ የወጣ ግለሰብ በግል ሥራ የሚተዳደር ወይንም ተቀጥሮ ሌላ ቦታ የሚሠራ ከሆነ** ከሚያገኛቸው ገቢዎች የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር የግድ መክፈል ይኖርበታል። ሆኖም ግን ግለሰቡ ከተለያዩ ቦታዎች ከሚያገኘው ገቢ ለቢቱዋሕ ሌኡሚ የሚከፍለው ግብር ከተወሰነ ጣራ በላይ ከሆነ ይህ ትርፍ ክፍያ ተመላሽ ይሆንለታል ማለት ነው።

## ዕድሜው ለጡረታ ድጎማ ለደረሰ ግለሰብ

ዕድሜው ለጡረታ ክፍያ ደርሶ ቢሆንም ይህን የጡረታ ድጎማ የማይቀበል ከሆነ የቢቱዋሕ ሌኡሚና የጤና ዋስትና ክፍያውን ከሥራ ቦታው ከሚቀበለው ክፍያ ይወርዳል።

### ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ጡረተኞች የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር ከመክፈል ነፃ ናቸው።

1. ዕድሜው ለጡረታ የደረሰ ግለሰብ
2. ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ባሏ ስለሞተባት የድጎማ ገንዘብ ወይም የጥገኞች ገንዘብ የምትቀበል ከሆነ
3. ከቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት 75 ከመቶ እጅ የአካል ጉዳተኛ ተብሎ የገንዘብ ድጎማ የሚቀበል ወይንም ከሥራው 100 ከመቶ እጅ የአካል ጉዳተኛ ተብሎ ገንዘብ የሚቀበል ወይንም አነሰ ቢባል ላንድ ዓመት 75 ከመቶ እጅ አካል ጉዳተኛ ተብሎ የገንዘብ ድጎማ የሚቀበል ከሆነ ነው።
4. የእስራኤል ኗሪ ያልሆነ ጡረታ የሚቀበል ግለሰብ
5. ለባለዋስትናው ጥገኞች ጡረታ የሚከፈል ከሆነ ከዚህ የጡረታ ገንዘብ ላይ ለቢቱዋሕ ሌኡሚና ለጤንነት ዋስትና ተቀናሽ ገንዘብ አይወርድም።

**ለቤት እመቤት የሆነችና የማትሠራ ሴት ባሏ የጡረታና የ"ሺአሪም" ዋስትና ካለው** ጡረታ ለሚከፍለው ድርጅት ይህን መረጃ በማቅረብ ከዚህ ከጡረታው ገንዘብ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር አትከፍልም ማለት ነው።

## የጡረታ ደሞዝ ወይንም "ሻኢ.ሪም" ለሚቀበል ግለሰብ

**የጡረታ ደሞዝ ወይንም ባል ወይንም ሚስት በሞት ከተለየች የሚከፈል ተጨማሪ ገቢ ማሟያ** ተብሎ የሚከፈላቸው ግለሰቦች ዝቅተኛ የጤና ዋስትና ክፍያ ማለትም **በወር 103 ሼቄል** (ከጥር 2016 ጀምሮ) ይከፍላሉ።

**የጡረታ ክፍያ ያለ ተጨማሪ የገቢ ማሟያ ለሚቀበል ግለሰብ** ከሚቀበለው ክፍያ ለጤና ዋስትና ተብሎ ለአንድ ሰው 196 ሼቄል ለባልና ሚስት ደግሞ **በየወሩ 283 ሼቄል** (ከጥር 2016) ጀምሮ ይከፍላሉ። እነዚህ ጥንድ ባልና ሚስቶች ለየብቻቸው የገንዘብ ድጎማ የሚያገኙ ቢሆንም ነው በተጨማሪም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማለትም ከጡረታ ክፍያ ወይንም በግል ከሚተዳደሩበት ሥራ ወይንም ተቀጥረው ከሚሠሩበት ቦታ ገቢ ቢኖራቸው የጤና ዋስትና ግብር ከመክፈል ነፃ ናቸው።

ተቀጥሮ የሚሠራው ግለሰብ አሠሪ ባለቤት ለቢቱዋሕ ሌኡሚ ሥራ ቦታ ሊደርስ ለሚችል አደጋና መሥሪያ ቤቱ ኪሳራ ቢደርስበት የሚከፍለውን ዋስትና መክፈል ይኖርበታል። በግል የሚተዳደር ሠራተኛ ደግሞ ራሱ ሥራ ላይ ሊደርስ ለሚችል አደጋ ዋስትና ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።

**በግል ወይንም በሚስት ሞት ምክንያት ድጎማ የሚቀበሉ ቢሆንም ዕድሚያቸው ለጡረታ ደርሶ የጡረታ ድጎማ ለማይቀበሉ** ከሚቀበሉት ገንዘብ ለጤና ዋስትና ክፍያ **በወር 168 ሼቄል** ይወርድባቸዋል (ጥር 2016)። በሌላ ሥራ ተቀጥረው ወይንም በግል ሥራ የሚተዳደሩ ከሆነ በገቢያቸው መሠረት የቢቱዋሕ ዋስትናውን ይከፍላሉ። ከጡረታው ድጎማ ግን የቢቱዋሕ ዋስትና ክፍያ አይወርድም።

## የተለያዩ ድጎማዎች ለሚቀበሉ

የተለያዩ ድጎማዎች ለሚቀበሉ (ከጡረታ ድጎማና ባል ወይንም ሚስት ለሞተባቸው የሚሰጥ ድጎማ የሚቀበሉና ጡረታ መውጫ ዕድሜ ክልል ከደረሱት በስተቀር) ሌላ ቦታ ተቀጥረው የሚሠሩ ከሆነ ወይንም በግል ሥራ የሚተዳደሩ ከሆነ የጤና ዋስትና ግብር መክፈል ይኖርባቸዋል። ከጡረታ ደሞዛቸው ግን የሚወርደው የጤና ዋስትና ክፍያ ይቀራል።

ከታች የተጠቀሱት ከጤና ዋስትና ግብር ክፍያ ነፃ ናቸው። ከፍተኛ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው የሚሰጥ ድጎማ ከሚቀበሉ፤ ልዩ እንክብካቤ ለሚያገኙበት ቦታ ከሚሰጥ ድጎማ፤ ከቦታ ቦታ እንዲቀሳቀሱ ለአካል ጉዳተኞች መረጃ ተብሎ ከሚሰጥ ድጎማ፤ ለአካለ ስንኩል ልጅ ተብሎ ለሚረዳ ድጎማ፤ ለልጅ ማሳደጊያ ከሚሰጥ ድጎማ፤ ለ"ሐሲዴ ኡሞት ሀዖላም" ሚሰጥ ድጎማ

- ከጡረታ በሚያገኙት የገንዘብ ድጎማ ብቻ የሚኖሩ ግለሰቦች ዝቅተኛ የሆነውን የጤና ዋስትና ግብር **በወር 103 ሼቄል** (ከጥር 2016 ጀምሮ) ይከፍላሉ። ይህ ከሚሰጣቸው የጡረታ ድጎማ ይወርዳል።
- በደሞዝ ፋንታ ለሚሰጡ የገንዘብ ድጎማ (ጉዳት ላጋጠመው ግለሰብ፤ በወሊድ ዕረፍት የሚከፈል፤ ለሥራ አጥ የሚሰጥ ድጎማ፣ "ሚሉይም" (ውትድርና ለሄደ የሚሰጥ ድጎማ)፣ ተቀጥሮ እንደሚሠራ ግለሰብ ከተቀበሉት ገንዘብ የጤና ዋስትና ግብር ይከፍላሉ።

## ዕዳ ያለባቸው ግለሰቦች ዕዳቸውን እንዲከፍሉ የሚያመቻች ሁኔታ

አሠሪዎችና በግል የሚተዳደሩ ግለሰቦች ለቢቱዋሕ ሌኡሚ መክፈል ያለባቸውን ዕዳ በቀላሉ መንገድ መክፈል እንዲችሉ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ቅጣት ለማቅለልና በተመቻቸ ሁኔታ እንዲከፍሉ የማድረግ መብት ተሰጥቷቸዋል።

የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤትም አሠሪዎች ወይንም በግል ሥራ የሚተዳደሩ ግለሰቦች ዕዳቸውን እንዲከፍሉ የተለያዩ የመክፈያ ዘዴዎች አመቻችተዋል። ይህም በ"ካርቲስ አሽራይ" በኩል በቴሌፎን *6050 ወይንም በመ/ቤቱ ድረ ገጽ በመጠቀም መክፈል ወይንም በግል ባንካችን በየወሩ የሚከፈል ሁኔታ ("ሆራአት ኬቫ") በማስተካከል ወይንም በረጅም ጊዜ በሚከፈል ቼክ በማዘጋጀት ዕዳቸውን ማቃለል ይቻላል።


አሠሪዎች ሆኑ በግል ሥራ የሚተዳደሩ ግለሰቦች ያለባቸውን ዕዳ በ"ካርቲስ አሽራይ" ወይንም ከባንክ ብድር ወስደው ዕዳቸውን ከከፈሉ ለከፈሉት የሚሰጣቸውን ደረሰኝ በመያዝ ወጪያቸውን በዓመት መጨረሻ "ማስ ሀክናሳ" እንዲያወርድላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

> **ያለባቸውን ዕዳ በ"ክሬዲት ካርድ" ("ካርቲስ አሽራይ") ለሚከፍሉ "ኮምፒይቴራይዝድ" የሆነ የስልክ መስመር 08-6509911**
>
> **የማዕከሉ የሥራ ሰዓት**
> ከእሑድ እስከ ረቡዕ ጥዋት 6:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ 3:30 ከሌሊቱ
> ሐሙስ ከጥዋቱ 6:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 18:30
> ዓርብ ከጥዋቱ 6:00 ሰዓት እስከ ቀትር በኋላ 14:30 ድረስ



# ሁሉም መሥመሮች ክፍት ናቸው

## ለአገልግሎትና መረጃ ቀላሉ መንገድ



**የስልክ ማእከል፣ "ዔምዶት ሼሩት"፣ ሁሉንም መረጃዎችና አገልግሎቶች የሚያቀርብ የተሻሻለ የኢንቴርኔት ድረ ገጽ – ለቀላል፣ ቀልጣፉና ምቹ አገልግሎት**

## የተለያዩ አገልግሎቶች አጠር ባለ መንገድ ስልክ በመደወል

### ብሔራዊ የስልክ ማዕከል *6050

### ወይንም 04-8812345

ሰፉ ያሉና የተለያዩ አገልግሎቶችን በስልኩ ማዕከል አማካይነት ማግኘት ይቻላል።

እነዚህም፡- አጠቃላይ መረጃ መቀበልና ግላዊ ማጣራቶች፣ የዋስትና ክፍያ ዕዳዎችን በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካይነት መክፈል፣ ስለቀሪ ዕዳ መረጃ መቀበል፣ በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካይነት የቋሚነት ክፍያን መክፈት፣ ፈቃዶችና ማረጋገጫዎች ወደ ቤት በፖስታ እንዲላኩ መጠየቅ፣ የክፍያ ኩፖኖችን ማዘዝ፣ ቅጾችንና የማብራሪያ አጭር ጽሑፎችን ለመቀበል።

> **› ማወቅ የሚያስፈልገው!**
> ከአገልግሎት ወኪሉ የግል መረጃ ማግኘ የሚቻለው ምስጢራዊ ኮድና የመታወቂያ ቁጥር በመስጠት ነው። ምስጢራዊ ኮዱን ከስልክ ማዕከል ማዘዝ የሚቻል ሲሆን ኮዱ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ዝርዝር ላይ በሚገኝ አድራሻ አማካይነት ወደቤትህ ይላካል። እንደዚሁም ከግላዊ ድረ ገጽ ላይ ማውጣት ይቻላል።

አገልግሎቱ የሚሰጠው ከሑድ እስከ ኀሙስ ቀን ሲሆን ከ8፡00 እስከ 17፡00 ሰዓት ድረስ

በ4 ቋንቋዎች ይሰጣል፡- ዕብራይስጥ፣ ዓረብኛ፣ ራሽያንኛ እና አማርኛ።

ከሥራ ሰዓት ውጪ የመታወቂያ ቁጥርና ምስጢራዊ ኮድ በማስገባት “ኮፕምፒዩተራይዝድ” የሆነ የስልክ መልስ
ይሰጣል።

በስልክ ማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች፡

- አጠቃላይ መረጃ
- ማጣራት – ግላዊ መረጃ
- ፈቃድ ለማዘዝ – ፈቃድህ ወደቤት በፖስታ ወይም በኢ-ሜይል ይላክልሃል
- የዋስትናውን ዕዳ በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካየነት ለመክፈል፣ ስለቀሪ ዕዳ መረጃ መቀበል
- የመክፈያ ኩፖኖችን ለማዘዝ
- ባዶ ቅጾችንና የማብራሪያ ጽሑፎችን ለማዘዝ

### የዋስትና ክፍያ ዕዳዎች በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካይነት የሚከፈሉበት “ኮምፒዩተራይዝድ” የሆነ የመክፈያ ማዕከል 08-6509911

ይህ የስልክ መሥመር የግል ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና የማይሠሩ ሰዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት መንገድ ነው።

አገልግሎት የሚሰጥበት ጊዜም ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከጧቱ 7፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት፣ ዐርብና በበዓላት ቀናት መግቢያ ከጧቱ 7፡00 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 14፡30 ይሆናል።

### በተቆራጭ ነክ ጉዳዮች ዕዳዎችን በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካይነት ለመክፈል “ኮምፒዩተራይዝድ” የሆነ የመክፈያ ማዕከል 08-6509935

አገልግሎት የሚሰጥበት ጊዜ ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከጧቱ 7፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት፣ ዐርብና በበዓላት ቀናት መግቢያ ከጧቱ 7፡00 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 14፡30 ይሆናል።

### እርግዝናን ለመጠበቅ ሪፖርት ለማድረግ የስልክ ማዕከል 08-6509934

አንቺ እርግዝናን ለመጠበቅ ከቢቱዋሕ ሌኡሚ ድጎማ የምትቀበዩ ከሆነ በየወሩ አውቶማቲክ በሆነ የስልክ ምላሽ መቀበያ ሂደቱን ስለመቀጠልሽ ወይም ስለማቆምሽ ሪፖርት ማድረግ አለብሽ።

ይህ አገልግሎት የሚሰጠው ከእሑድ እስከ ረቡዕ ከጧቱ 6፡00 እስከ ሌሊቱ 3፡30 ድረስ ነው። ኀሙስ ቀን ከጧቱ 6፡00 እስከ ምሽቱ 18፡30 ድረስ ነው። ዐርብና በበዓላት ቀናት መግቢያ ከጧቱ 6፡00 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 14፡30 ይሆናል።

### ከውጪ ለሚደውሉ የስልክ ማዕከል

ከውጪ ለሚደውሉት 972-8-9369669 የስልክ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።

አገልግሎት የሚሰጥበት ጊዜም ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከጧቱ 8፡00 ሰዓት እስከ 15፡00 ሰዓት ሆኖ በ4 ቋንቋዎች ይሰጣል፡ ዕብራይስጥ፣ ዓረብኛ፣ ራሽያንኛ እና አማርኛ።

ከሥራ ሰዓት ውጪ የመታወቂያ ቁጥርና ምስጢራዊ ኮድ በማስገባት “ኮፕምፒዩተራይዝድ” የሆነ መልስ ይሰጣል።

### እርጅናን በተመለከተ የስልክ ማዕከል 08-6509934

የአረጋውያን/ባልቴቶች ምክር አገልግሎት ዕድሜያቸው ለገፉ ሰዎችና ለቤተሰቦቻቸው ከእርጅና ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩ የስልክ መሥመር ያንቀሳቅሳል። አገልግሎቱ የሚሰጠው ለዚህ ጉዳይ ተብሎ በሠለጠኑ በጐ ፈቃደኞች አማካይነት ነው። ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከጧቱ 8፡00 እስከ ቀኑ 12፡30 ድረስ

- በዕብራይስጥ ቋንቋ02-6463400
- በዓረብኛ ቋንቋ02-6463401
- በራሽያንኛ ቋንቋ02-6463402
- በአማርኛ ቋንቋ02-6463403
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ02-6463404

## ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት

### ራሳችንን ማስተናገድ የምንችልበት ቦታዎች (“ዔምዶት”)

እነዚህ ቦታዎች የተዘጋጁት ፈጣንና ቀልጠፋ አገልግሎት በአብዛኛው ሰዓታት መቀበል እንድንችል ለማድረግ ነው። እነዚህ ቦታዎች አብዛኛውን ጊዜ በቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት መግቢያዎች ላይ ይገኛሉ።

በነዚህ መሣሪያዎች አማካኝነት አገልግሎት የምናገኝባቸው ነገሮች፡

- “ኪጽባዎችን” በተመለከተ የተለያዩ ፈቃዶች መቀበል – ክፍያዎችንና ባለመብትነትን በተመለከተ የሚሰጡ ፈቃዶች
- የዋስትና ክፍያን በተመለከተ የሚሰጡ ፈቃዶች – የሒሳብ ዝርዝሮችና የ“ማስ ሀክናሳ” ፈቃዶች
- ለጡረታ የምትደርስበትን ዕድሜ ማሰቢያ መንገድ

የአገልግሎት ቦታ (“ዔምዳ”) ማንቀሳቀስ ቀላል ሲሆን እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚታጀበው ተገቢ በሆኑ መመሪያዎች ነው። መመሪያዎቹ የሚሰጡት በ3 ቋንቋዎች ነው፡ ዕብራይስጥ፣ ዓረብኛና ራሽያንኛ።

የአገልግሎት ቦታ (“ዔምዳ”) ለማንቀሳቀስ የመታወቂያ ቁጥርና የሚስጥር ኮድ ያስፈልጋል።

ምስጢራዊ ኮዱን ለስልክ ማዕከሉ በ*6050 በመደወል ማዘዝ ይቻላል። ኮዱም በቢቱዋሕ ሌኡሚ መዝገብ ላይ ወደሚገኘው አድራሻ አማካይነት ወደ ቤትህ ይላካል።

### የአገልግሎት ቦታ (“ዔምዳ”) የሥራ ሰዓቶች

| | |
|---|---|
| እሑድ – ረቡዕ | 23:00-7:00 |
| ኀሙስ | 18:00-7:00 |
| ዓርብና የበዓል መግቢያ | 14:30-7:00 |

## አድራሻ አላችሁ
## WWW.BTL.GOV.IL

የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ መሥሪያ ቤት ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ሰፋ ያለ መረጃ እንድናገኝ ይረዳናል። ይህ ድረ ገጽም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንድናደርግና ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ድረስ ከመምጣት ጊዜያችንን እንድንቆጥብ ይረዳናል። ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ራሳችን ችለን ግላዊ አገልግሎት ማግኘት እንችላለን።

መረጃዎቹ በድረ-ገጹ ላይ የሚቀርቡት በዐረብኛ፣ በእንግሊዝኛና በራሽያንኛ ነው።

### በድረ-ገጹ ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር፦

- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተመረኰዙ ማመልከቻዎችን ማቅረብና ሰነዶችን "ኦንላይን" ላይ ሆኖ መላክ
- ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ስለምንቀበላቸው ተቆራጮች ባለመብትነትና ስለ“ኪጽባው ”ከፍተኛ መጠን ማስሊያዎች
- ወደሚንከባከበን ቅርንጫፍ ቀጥታ ማመልከትና ግላዊ ማብራሪያዎችና አጠቃላይ ጥያቄዎች
- የተለያዩ ፈቃዶችንና ቅጾችን መጠየቅ
- የማመልከቻ ቅጾችንና ሌሎች ተጨማሪ ቅጾችን መጠየቅና ማተም
- ለስልክ ማዕከሉና የግል አገልግሎት ጣቢያዎች ምስጢራዊ ኮድ መጠየቅ እንዲሁም ለኢንቴርኔት ጥቅም የሚውል የተጠቃሚ ኮድና ፓስወርድ (“ሲስማ”) ጠይቆ መቀበል
- የዋስትና ክፍያ ማስተካከልብና
- የኩፓት ሆሊም ዝውውር
- ለሕጻናት መደጐሚያ የባንክ ሒሳብ ቁጥርን ማስተካከል
- ደብዳቤዎችን በኢሜይል ለመቀበል መመዝገብ

### ክፍያዎች

በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካኝነት እስከ 25,000 ሼቄል ክፍያ ማካሄድ ይቻላል። በባንክ በኩል የሚደረገው ክፍያ ከሆነ ግን እስከፈለግነው የገንዘብ መጠን ድረስ ነው። በባንክ በኩል ማስተላለፍ የሚቻለው ደንበኛው የባንክ ፈቃድ ካለው ብቻ ነው።

- ሪፖርትና የባለዋስትናው ክፍያ፡ የግል ሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ የማይሠሩ፣ በዕረፍት ያሉና ያለክፍያ ያሉ፣ የ“የሺቫ” ተማሪዎችና ውጭ አገር የሚኖሩ
- ሪፖርትና የአሠሪዎች ክፍያ፡ ፎርም 102፣ የውጭ አገር ኗሪዎች፣ በዕረፍት ያሉና ያለክፍያ ያሉ፣ የሙያ ሥልጠናዎች፣ አስቀድመው ጡረታ የወጡ
- ሪፖርትና የቤት ክፍያ፡ ሪፖርትና የቤት ሠራተኞች ክፍያ፣ የቤት ሥራ ፋይል መክፈትና መዝጋት
- የጤንነት ዋስትና፡ የመጠባበቂያ ጊዜ “ፒዳዮን”
- የጡረታ ዕዳ ክፍያና ተጨማሪ ክፍያዎች

### ግላዊ አገልግሎት

በግላዊ አገልግሎት በተቀላጠፈና ምቹ በሆነ መንገድ የራሳችንን መረጃ ከግል ፋይላችን ውስጥ ገብተን መመልከት እንችላለን። ወደዚህ አገልግሎት መግባት የሚቻለውም በኮድና “ፓስወርድ” (“ሲስማ”) አማካይነት ነው። በድረ-ገጹ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር፦

- ማመልከቻዎችንና ሰነዶችን "ኦንላይን" ሆኖ ማቅረብ
- ወዳንተ የተላኩልህ ደብዳቤዎችን መመልከት
- ወደ ቅርንጫፉ ያስተላለፍካቸውን የሰነዶች ዝርዝር መመልከት
- መብቶችህን ለማስጠበቅ ግላዊ የማስታወቂያ ሰሌዳ
- ያንተን ማመልከቻ በተመለከተ ምን አስተውሎት እንዳገኘ ማሳየትና የተከፈሉህ ክፍያዎች ዝርዝር
- “ኪጽባዎችን” ስለመቀበልህ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን/የክፍያ ማረጋገጫዎችንና ሌሎችንም ማተም
- የሒሳብ ወረቀትን፣ ቀሪ ዕዳዎችን/መብቶች፣ የቅድሚያ ክፍያዎች፣ የወደፊት ዕዳዎች፣ ወዘተ. ማሳየት

### አጠቃላይ መረጃ

ስለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ “ኪጽባኦት”፣ ስለዋስትና ክፍያዎች ግዴታ (የጤንነት ዋስትናን ጨምሮ) እና ስለቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ “ክራኖት” አጠቃላይ መረጃ


- ብዙ ሰው የሚጠይቃቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው
- በሕጉ ላይ ያሉ ለውጦችንና በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ነገሮች ዘገባ
- ስለቅርንጫፎች መረጃ – አድራሻዎች፣ የተገልጋይ መቀበያ ሰዓት፣ የስልክ ቁጥሮች፣ የመኪና ማቆሚያ ማብራሪያዎችና ወደቦታው እንዴት እንደሚደረስ የሚያሳይ ካርታ
- መረጃ ስለአገልግሎት ቦታዎች – የስልክ ማዕከሎችና የግል አጋእልግሎት ጣቢያዎች (“ዔምዶት”)
- ስለ”ኪጽባ” ክፍያዎችና ስለ”ኪጽባ” ተቀባዮች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች
- የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ፣ የቢ.ቱዋሕ ለኡሚ ደንቦች፣ ስምምነቶች እና ማኅበራዊ ዋስትናን በተመለከተ ዓለማቀፋዊ ውሎች
- ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚን አስመልክቶ ኦፊሴላዊ ኅትመቶች
- ጨረታዎችንና ክፍት የሥራ ቦታዎችን አስመልክቶ መረጃ
- በተቋሞችና ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ተቆራጭ ተቀባዮች መብቶችና ጥቅማጥቅሞች ዝርዝር
- ለብዙ ሕዝብ የሚላክ ማስታወቂያዎች (“ሐዝሪም”) እና ደንቦች

## ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ በእጅ ስልክ

ከአሁን ጀምሮ ወደተራቀቀው የእጅ ስልካችሁ (“ስማርትፎን”) የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት “አፕሊኬሽኖችን” ማውረድ ትችላላችሁ። ይህም በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ያላችሁን መብቶች እንድታውቁ ይረዳችኋል።

በ“አፕሊኬሽኑ” የምታገኟቸው አገልግሎቶች፦

- ፈቃዶችና ፎርሞች እንዲላኩ መጠየቅ
- ለልጆች የሚከፈሉ ድጐማዎች፣ ለጡረታ ባለመብት የምትሆኑበት ዕድሜና የሚደርሳችሁ የተጠባባቂ ወታደርነት ክፍያ ማስሊያዎች
- ከቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ስለሚደርሷችሁ “ኪጽባዎችና” ጥቅማጥቅሞች መመሪያዎች
- የምትሄዱበትን የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፍ የሚያሳይ ካርታ
- በ“ካርቲስ አሽራይ” አማካይነት የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚና የጤንነት ዋስትና ክፍያዎች (ለግል ሠራተኞችና ለማይሠሩ ሰዎች)




## የ"ያድ መካቬኔት" ማእከል ወደ ሕክምና ኮሚቴዎች ለሚቀርቡ ምክርና አመራር – ለሐይፋና ሰሜን ኗሪዎች፣ ለቤርሼቫና ደቡብ ኗሪዎች

በ"ያድ መካቬኔት" ማእከል ወደ ሕክምና ኮሚቴዎች ከመቅረብህ በፊት በመስካቸው በሳል ከሆኑ ሐኪሞች ምክርና አመራር እንደዚሁም ተገቢዎቹን ሰነዶች በማዘጋጀት ረገድ እርዳታ **ያለምንም ክፍያ** ትቀበላለህ። የ"ያድ መካቬኔት" ማእከል በቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ የተቋቋመ ሲሆን በግል ኩባንያ አማካይነት የሚንቀሳቀስ ነው።

**ሐይፋና ሰሜን፡**
**ስልክ፡** 04-9126885
**ፋክስ፡** 04-9126890
**ኢሜይል፡**
**አድራሻ፡** ረሖቭ ፓልያም 16 ብንያን ሻዓሬ ሚሽፓት፣ ሐይፋ

**ቤርሼቫና ደቡብ፡**
**ስልክ፡** 08-6831919
**ፋክስ፡** 08-6831918
**ኢሜይል፡** yadm@medition.co.il
**አድራሻ፡** ካንዮን ሀኔጌቭ፣ ሚግዳል ካንዮን፣ 5ኛ ፎቅ፣ ቤርሼቫ

## “ስኒፊት” – የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ተንቀሳቃሽ ቅርንጫፍ

አገልግሎት ለመቀበል ብዙ ጥያቄ ወዳለበት ነገር ግን የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት ወደማይገኙባቸው ቦታዎች የሚመጣ ቅርንጫፍ ነው። “ሀስኒፊት” በኮምፒዩቴሮችና የተራቀቁ መሥሪያዎች የሚታገዝ ሲሆን ሰፋ ያሉና የተለያዩ አገልግሎቶችን መቀበል ይቻላል። እነዚህም፡ - ቅጾችንና ፈቃዶችን መቀበል፣ አቤቱታን ወይም የፋይልን ሁኔታ አስመልክቶ የሚደረጉ ማጣሪያዎች፣ ክፍያዎችን መፈጸም፣ አቤቱታና ሰነዶችን ማቅረብ፣ ወዘተ. ናቸው።

**"ሀስኒፊት" ቋሚ በሆነ ሁኔታ ወደነዚህ ቦታዎች ይደርሳል፡**

- **ክሳይፌ** – ሰኞና ረቡዕ ከ8:30 እስከ 12:30፣ በመንደሩ መሐል ከኩፓት ሆሊም ማካቢ አጠገብ
- **ዓርዓራ** – እሑድና ማክሰኞ ከ8:30 እስከ 12:30፣ በ“ኤዞር ሀታዓስያ”፣ ከ“ማጌን ዳቪድ አዶም” አጠገብ
- **ሑራ** – እሑድና ማክሰኞ ከ8:30 እስከ 12:30፣ ከማኅበራዊ አገልግሎቶች ቢሮ አጠገብ
- **ሴጌቭ ሻሎም** – ሰኞ ከ8:30 እስከ 12:30፣ ከማኅበራዊ አገልግሎቶች ቢሮ አጠገብ



# በማኅበራዊ ደኅንነት ዋስትና ዘርፍ ዓለም አቀፍ ውል

ማኅበራዊ ደኅንነት ዋስትና ውል የሚባለው እስራኤል ከሌሎች ሀገሮች ጋር የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያዎች ከሀገር ሀገር እየተዘዋወሩ የሚሠሩ ግለሰቦች ማለትም ውጭ ሀገር የሚሠሩ እስራኤላውያን ሁለት ቦታ የማኅበራዊ ዋስትና ክፍያ እንዳይከፍሉ ለማድረግ ነው።

## የማኅበራዊ ዋስትና ውል እስራኤል የተፈራረመቻቸው ሀገሮች

እንግሊዝ፤ ሆላንድ፤ ፈረንሳይ፤ ቤልጂየም፤ ኦስትሪያ፤ ጀርመን፤ ሲዊድን፤ ስዊዘርላንድ፤ ዴንማርክ፤ ፊንላንድ፤ ኡራጓይ፤ ቼክ ሬፑብሊክ፤ ኖርዌይ፣ ቡልጋሪያ፣ ስሎቫኪያና ሩማኒያ እንዲሁም በተወሰነ መልኩ ጣልያንና ካናዳ የቢቱዋሕ ሌኡሚ ግብር በድጋሚ እንዳይከፈል ውል አላቸው።

## ይህ ውል ሥራ ላይ የሚውለው ማን ላይ ነው?

ይህ ውል ሥራ የሚውለው የእስራኤል ዜጎችና ከላይ የተዘረዘሩት ሀገሮች ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ነው።

በውሉ ላይም የትኛው የማኅበራዊ ዋስትና ዓይነት እንደሚካተት ተዘርዝሯል።

በአብዛኛው ይህ ዓለም አቀፍ የማኅበራዊ ዋስትና ውል የሚያካትተው ለሽማግሌዎች፤ ባል ወይንም ሚስት ለሞተባቸው፤ ለአካለ ጉዳተኞች፤ በሥራ ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው፤ ለልጆችና እናቶች የሚሰጡትን ድጎማዎች ያካትታል።

## ዓለም አቀፍ ማኅበራዊ ዋስትና ውል በውስጡ ምን ዓይነት መብቶችን ያካትታል?

1. ዓለም አቀፍ ማኅበራዊ ዋስትና ውል ከእስራኤል ጋር ወደ ተፈራረሙ ሀገሮች የሄደ የእስራኤል ዜጋ ከእስራኤል የተለያዩ የገንዘብ ድጎማዎች መቀበል ይችላል።
2. ዓለም አቀፍ ውል ከእስራኤል ጋር ከፈረሙ ሀገሮች ይኖር የነበረና ወደ እስራኤል ተመልሰው ኑሯቸውን የጀመሩ ከነበሩበት ሀገር የተለያዩ የገንዘብ ድጎማዎች መቀበል ይችላሉ።
3. የተለያዩ ድጎማዎችን ለመቀበል በሁለቱ ሀገሮች የነበረውን የዋስትና ክፍያ ዘመን ማቀናጀት
4. በሥራ ቦታ አደጋ ለደረሰበት – የሕክምና አገልግሎት ወዲያው የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲሁም የሕክምናውን ወጭ መሸፈን ይህም ውል ላይ በተደረገው ሕግ መሠረት ይሆናል።

## የብሔራዊ ዋስትና ግብር ተመሳሳይ ክፍያ ሁለት ጊዜ እንዳይከፍሉ ለማድረግ

ወደ ሌላ ሀገር በመሄድ ሥራ መሥራት የጀመረ የእስራኤል ዜጋ በሕጉ መሠረት በሄደበት ሀገር የብሔራዊ ዋስትና ግብር መክፈል ይኖርበታል። በዚያው መጠንም ምንም እንኳ ውጭ ሀገር ቢኖርም በእስራኤል የብሔራዊ ዋስትና ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት። ይህም ግለሰቡ ሁለት ጊዜ እንዲከፍል ይገደዳል ማለት ነው። ይህን ነገር ለማቆምም አንድ የእስራኤል ዜጋ ዓለም አቀፍ ውል ወደ ተፈራረመቻቸው ሀገሮች ከሄደ ከሁለት ሀገሮች በአንዱ ብቻ የብሔራዊ ዋስትና ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል።

**የጤና ዋስትና ክፍያ በዓለም አቀፍ ውል አይካተትም፡** በውጭ ሀገር የሚኖር እስራኤላዊ የጤና ዋስትና ክፍያ ለእስራኤል የቢቱዋሕ ሌኡሚ መሥሪያ ቤት መክፈሉን ይቀጥላል።

› ለተጨማሪ መረጃና አስፈላጊ ፎርም ለማግኘት (የተለያዩ ድጎማ ለመቀበል ወይም ሁለት ጊዜ ተመሳሳይ ክፍያ ላለመፈጸም) ለሚመለከተው ክፍል ያመልክቱ፡
የውጭ ሀገር ግንኙነት ክፍል፣ ሽዴሮት ቫይጽማን 13 ኢየሩሳሌም
**ፋክስ፡** 02-6512683
**የኢሜል አድራሻ፡** liaison@nioi.gov.il
**ለተጨማሪ ማብራሪያ፡** ሀገር አቀፍ የስልክ ጥሪ መቀበያ *6050
ወይንም 1-222-6050
**ከውጭ ደውለው መረጃ ለመቀበል፡**
972-8-936-9669







የቢቱዋሕ ሌኡሚ “ኪጽባዎችን” በሚከፍላቸው ሕጐች መሠረት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጦች ይኖራሉ። ስለሆነም መብትህን ተግባራዊ ለማድረግ በምትመጣበት ጊዜ ለስልክ ማዕከል *6050 በመደወል መብቶችህን አጣራ። እንደዚሁም በቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፎች በኩል ለማጣራት የምትችል ሲሆን አጠቃላይና ወቅታዊ መረጃ የያዘውን www.btl.gov.il የተሰኘውን የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ መጠቀም ትችላለህ።

# የቢቱዋሕ ሌኡሚ ቅርንጫፎች

## ዋና ቅርንጫፎች፡

**ዋናው መሥሪያ ቤት ሽዴሮት ቫይጽማን 13፣ ኢየሩሳሌም**
ፋክስ፡ 02-8305256

**አሽዶድ |** ረሖቭ ጻሐል 4
ፋክስ፡ 08-3066868

**አሽቄሎን |** ረሖቭ ሀናሲ 101
ፋክስ፡ 08-6710681

**ቤርሼቫ |** ረሖቭ ሻዛር 31א

**ብኔ ብራክ |** ረሖቭ አሃሮኖቪች 12
ፋክስ፡ 03-6152976

**ሐዴራ |** ረሖቭ ሂሌል ያፌ 7א
ፋክስ፡ 04-8018236

**ሖሎን |** ፒንሐስ ላቮን 26፣ ፒናት ባራካት
ፋክስ፡ 03-2242205

**ሐይፋ |**
ፋክስ፡ 04-0094318

**ቲቬሪያ |**
ፋክስ፡ 04-6738040

**ያፎ |**
ፋክስ፡ 03-9417215

**ኢየሩሳሌም |** ረሖቭ ቤን ሲራ 22 | ረሖቭ ሽምዖን ቤን ሼታሕ 4
ፋክስ፡ 02-6755447

**ክፋር ሳቫ |**
ፋክስ፡ 09-8861047

**ካርሚኤል |**
ፋክስ፡ 04-9907847

**ናሀሪያ |**
ፋክስ፡ 04-3018259

**ናጼሬት |**
ፋክስ፡ 04-8047206

**ናታንያ |**
ፋክስ፡ 09-8602804

**ዓፉላ |**
ፋክስ፡ 04-6806256

**ፔታሕ ቲክቫ |**

**ክራዮት |**
ፋክስ፡ 04-2491148

**ሪሾን ለጽዮን |**
ፋክስ፡ 03-4176249

**ረሖቮት |**
ፋክስ፡ 08-9450737

**ራምሌ |**
ፋክስ፡ 08-7514529

**ራማት ጋን |**
ፋክስ፡ 03-7512616

**ቴል አቪቭ |**
ፋክስ፡ 03-6250634

## ንኡስ ቅርንጫፎች፡

**ኤይላት |** ረሖቭ ማዲን 12
የተቆራጮች ፋክስ፡ 08-6341344
የክፍያ ፋክስ፡ **08-6024736**

**ባት ያም |** ረሖቭ ጃቦቲኒስኪ 2
ፋክስ፡ 03-0807215

**ዲሞና |** ረሖቭ ጃቦትኒስኪ 1
ፋክስ፡ 08-7773556

**ሔርጸሊያ |** ረሖቭ ቤን ጎሪዮን 22
ፋክስ 09-9312459

**ሚግዳል ዔሜክ |**
ፋክስ፡ 04-3225456

**ምሥራቅ ኢየሩሳሌም |**
ፋክስ፡ 02-7555666

**ማጃር |**
ፋክስ፡ 04-7380786

**ናጼሬት ዒሊት |**
ፋክስ፡ 04-6028186

**ዓኮ |**
ፋክስ፡ 04-0955599

**ጽፋት |**
ፋክስ፡ 04-6825153

**ቅርያት ጋት |**
ፋክስ፡ 08-9345688

**ቅርያት ማላኺ |**
ፋክስ፡ 08-9376627

**ቅርያት ሽሞኔ |**
ፋክስ፡ 04-6738061

**ሽዴሮት |**
ፋክስ፡ 08-6849432

**ሽፋርዓም |**
ፋክስ: 04-6028188

## የአገልግሎት ማእከሎች፡

ኡም ኤል ፋሕም | ኦፋኪም | ኦር ይሁዳ | ኦር አኪቫ | ኤልዓድ | አሪኤል | ቤት ኤል | ቤት ሸአን | ቤት ሼሜሽ | ቤታር ዒሊት | ዳልያት አል ካርሜል | ሐጾር ግሊሊት | ታይቤ | ቲራት ሀካርሜል | ያቭኔ | ይሁድ | ዮክኔዓም | የሩሐም | ያርካ | ክፋር ካና | ሞዲዒን | ሞዲዒን ዒሊት | ማዓሌ አዱሚም | ማዓሌ ኤፍራይም | ማዓሎት – ታርሺሐ | ሚጽፔ ራሞን | ኔቲቮት | ኦፍራ | ዔሊ | ዓማኑኤል | ዓራድ | ፓርዴስ ሐና | ካላንዲያ | ካጽሪን | ቅርያት አርባ | ቅርያት አታ | ካርኔይ ሾምሮን | ሮሽ ሀዓይን | ራሀት | ሾሀም | ታርዲዮን

**በአገልግሎት ማእከሉ የሕዝብ መቀበያ ሰዓቶችን ማወቅ ከፈለጋችሁ ወደ ቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ የቅርንጫፎች ክፍል ግቡ።**

### › የሕዝብ አቤቱታዎች ክፍል

ቅሬታዎችና የማሻሻያ አስተያየቶች ካሉ ወደ ሕዝብ አቤቱታዎች ክፍል፡ ሽዴሮት ቫይጽማን 13፣ ኢየሩሳሌም፣ 91909 ማመልከት ይቻላል።
ስልክ፡ 02-0709076
ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከ13፡00 እስከ 15፡00 ሰዓት ድረስ።
ፋክስ፡ 02-8305256

**ለግል ማብራሪያዎች በ...አማካይነት ማመልከት ይቻላል፡**

**› የስልክ ማእከል *6050 ወይም 1-222-6050** ከእሑድ እስከ ኀሙስ ከ8፡00 እስከ 15፡00 ሰዓት ድረስ።

**› የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ www.btl.gov.il "פנו אלינו" በተሰኘው ዓምድ ሥር**

### › በዋና እና በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ መቀበያ ቀናት

እሑድ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ከ8፡00-12፡30 ማንኛውንም ቢቱዋሕ ሌኡሚን በተመለከተ (ናጼሬት ቅርንጫፍ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ)

ሰኞና ረቡዕ ከ15፡00- 17፡00 ሰዓት፣ በሥራ ላይ ለደረሰ አካል ጉዳት፣ እናትነትን ፣ ልጆችን፣ ተጠባባቂ የውትድርና አልግሎትን፣ ዋስትናን እና ክፍያን በተመለከተ አገልግሎት ይሰጣል (ከቴል አቪቭ ቅርንጫፍ በስተቀር)።



ሀቢ.ቱዋሕ ሀሌኡሚ — በሕይወትህ ወሳኝ ወቅቶች ከጐንህ ነው

*6050•www.btl.gov.il

ቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ተቆራጭ የሚከፍልባቸው ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያየሩ ይችላሉ። በመሆኑም መብትህን ተግባራዊ ለማድረግ በምትመጣበት ጊዜ መብቶችህን ለስልክ ማእከሉ 6050 * በመደወል፣ ወይም አጠቃላይና የተሻሻለ መረጃዎች ወደያዘው የቢ.ቱዋሕ ሌኡሚ ድረ ገጽ በመግባት በማንበብ።

ይህ ትንሽ መጽሔት የተሻሻለ በניסן התשע"ו ወይም ሚያዚያ 2016 ነው።

በዚህ ትንሽ መጽሔት አጠቃላይ ማብራሪያዎች የቀረቡ ሲሆን እነሱንም የሕጉ ሙሉ ቀመርና የተረጋገጠ አድርጐ ማየት አያስፈልግም። በተባእታይ ጾታ የተጻፈው ለአንስታይ ጾታም ያለግላል።